

ማጣት መንጣትን በምስጋና

ገጽ 16

ገጽ 16

አፈጻጸሙ እየተሻሻለ የመጣው

ባለ 20 ወለሉ የትራንስፖርት ዘርፍ ዋና መስሪያ ቤት ሕንፃ ግንባታ



ገጽ 14


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 189 መጋቢት 9 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ




# በከተማዋ የገበያ ንረቱን ለማረጋጋት

## 300 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ ምርቶች ለገበያ ቀርበዋል

ታደሰ ብናልፈው

አዲስ አበባ ፡- ባለፉት ስምንት ወራት የገበያ ንረቱን ለማረጋጋት 300 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች በተመጣጠኝ ዋጋ ለገበያ መቅረባቸውን የአዲስ አበባ ሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር ኤጀንሲ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ጥላሁን ጌታቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኤጀንሲው በግብርናና በኢንዱስትሪ ምርቶች ላይ እያሻቀበ የመጣውን የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት ትኩረት በመስጠት ሲሠራ ቆይቷል፡፡ በዚህም ባለፉት ስምንት ወራት በከተማዋ 300 ሚሊዮን የሚያወጡ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለኅብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ ተችሏል፡፡ 100 ሚሊዮኑ የሚያወጣው በመደበኛ የኅብረት ሥራ ሱቆች አማካኝነት የተደረገ ግብይት መሆኑን አመልክተው፤ 200 ሚሊዮኑ ደግሞ በሰንበት ገበያ የተፈጸመ ግብይት መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ክልሎች ላይ ከሚገኙ የአምራችና የገበሬ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ጋርም የተቀላጠፈ የንግድ ትስስር በመፍጠር የተለያዩ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ በሰንበት ገበያ ተደራሽ የማድረግ ሥራ መሠራቱን ተናግረዋል፡፡

በመዲናዋ 137 የሰንበት ቀን ገበያና 800 የሸማች ማኅበራት ሱቆች እንደሚገኙ የገለጹት አቶ ጥላሁን፤

በከተማዋ የገበያ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል






ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ



## “የተከሰተው የዋጋ ንረት በምርት እጥረት ሳይሆን በፖለቲካዊ ሴራ ነው”

አቶ ኃይሉ አዱኛ
የኦሮሚያ ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ

ገጽ 4

## በሃገሪቱ 13 ሚሊዮን ዜጎች ለድርቅ አደጋ ተጋልጠዋል

-የድርቅ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ከአራት ሚሊዮን ኩንታል በላይ እህል ተሰራጭቷል

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ 13 ሚሊዮን ዜጎች ለድርቅ አደጋ መጋለጣቸውን የአደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽን አስታወቀ፡፡ ተጋላጭ ለሆኑ አካባቢዎች ከአራት ነጥብ

በሃገሪቱ 13 ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ፎቶ፡- ሃዲስ አብርሃ



## አባል ሃገራቱ ጠንካራ የፍልሰት አስተዳደርን በመዘርጋት በቅንጅት ሊሠሩ ይገባል

### ሃገራት በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን ስምምነት ተፈራርመዋል

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- የምስራቅ እና የአፍሪካ ቀንድ ሃገራት ጠንካራ የፍልሰት አስተዳደርን በመዘርጋት በቅንጅት ሊሠሩ እንደሚገባ ተገለጸ፡፡ 11 አባላት ያሉት የምሥራቅ እና የአፍሪካ ቀንድ ሃገራት በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን ስምምነት ተፈራርመዋል፡፡

አባል ሀገራቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የኢፕድ ሥልጠና ማዕከል ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አመራሮችና ባለሙያዎች የሰጠው ሥልጠና ተጠናቀቀ

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አመራሮችና ባለሙያዎች በሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን የክህሎትና የአቅም ግንባታ ዙሪያ ሲሰጥ የቆየውን ሥልጠና በትላንትናው ዕለት ተጠናቋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሥልጠና ማዕከሉ በፌዴራልና በክልል ደረጃ ለሚገኙ የመንግሥትና የግል ድርጅቶች የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያዎችን እያሰለጠነ

የኢፕድ ስልጠና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








ፎቶ፡ አዩብ ተፈሪ
ኢንጂነር ወንድሙ ሴታ

# የሀገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች የገበያ ድርሻ 75 በመቶ እንዲሆን እየተሠራ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣይ አሥር ዓመታት የሀገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች የገበያ ድርሻ 75 በመቶ እንዲሆን የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች እየተዘጋጁ መሆኑን የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጮች ማኅበር ጋር የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን እየፈተኑ ባሉ ተግዳሮቶች ላይ ውይይት አድርጓል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ኢንጂነር ወንድሙ ሴታ በመርሐ ግብሩ የመክፈቻ ንግግር ባደረጉበት ወቅት እንደገለጹት፣ መድረኩ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ያለበትን ችግር በመፍታት እንደ ሀገር የታቀዱ የልማት ግቦችን ለማሳካት ጉልህ ሚና ይኖረዋል። እንዲሁም ለኢኮኖሚው የሚያደርገውን አስተዋፅዖ ማሳደግ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴዔታው ገለጻ፤ አሁን የሚስተዋሉ ችግሮችን መፍታት የሚያስችል ዘመኑን የሚመጥን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ተዘጋጅቷል። በቀጣይ ከባለሙያዎች ጋር ውይይት በማድረግ በአጭርና በረጅም ጊዜ የሚመራበት ፖሊሲ ተግባራዊ ይሆናል። በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ውስጥ በተያዘው ዕቅድ መሠረት የሀገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች ተወዳዳሪነትና አቅም ይገነባል።

የሀገር ውስጥ ተቋራጮች አሁን ያላቸውን ከ50 በመቶ በታች የገበያ ድርሻ ወደ 75 በመቶ እንዲያድግ ይሠራል ያሉት ሚኒስትር ዴዔታው፤ የዘርፉን አቅም ለማሳደግ የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች እየወጡ መሆኑንና በቀጣናው 25 በመቶ የገበያ ድርሻ እንዲኖራቸው የሚያስችል አቅምን ለመፍጠር ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

የሀገር ውስጥ ተቋራጮችን ተሳታፊነት ለማሳደግ ጠንካራ ሥራ መሥራትን እንደሚጠይቅ ገልጸውም፤ አሁን ላይ ወደ 25 ሺህ የሚደርሱ የሥራ ተቋራጮችን መፍጠር መቻሉን አስረድተዋል።

ይሁን እንጂ አቅሙ የተገነባው ተቋራጭ ቁጥር በጣም አናሳ ነው ያሉት ኢንጂነር ወንድሙ፤ ይህም እንደ ሀገር የሚፈልገውን ልማት ለማሳካት ተግዳሮት ፈጥሯል ነው ያሉት።

አብዛኛው የገበያ ጉድለት በውጭ ተቋራጮች እየተሞላ መሆኑንና በቀጣይ በጥራትና ፕሮጀክቶችን በመፈጸም ረገድ ጠንካራ አቅም እንዲኖራቸው እየተደረገ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴዔታው ማብራሪያ፤ ከሕግ ማዕቀፍ አንጻር አጠቃላይ የኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚመራበት አዋጅ የለም። በተለያየ ጊዜ ተቋማት ባወጧቸው መመሪያዎች ነው ዘርፉ እየተመራ ያለው። ይህም ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለመቆጣጠርና ችግር ፈጥሯል። የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አዋጅ እየተዘጋጀ ነው። ሲጸድቅ የኢንዱስትሪው ዘርፍ በአግባቡ እንዲመራ በማድረግ ለሀገር ዕድገት ያለውን አስተዋፅዖ ያሳድጋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጮች ማኅበር ሰብሳቢ ኢንጂነር ግርማ ኃብተማርያም በበኩላቸው፤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለሃገር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ጠቁመው፤ ይሁን እንጂ ከ70 በመቶ በላይ ያለው የሥራ ድርሻ በውጭ ሀገር የሥራ ተቋራጮች የተያዘ መሆኑን ገልጸዋል።

ሥራ ተቋራጮች ባለፉት አራት ዓመታት የተጋረጠባቸው ፈተና በሥራቸው ላይ ከፍተኛ ችግር ፈጥሮባቸዋል ያሉት ሰብሳቢው፤ በግንባታ ግብዓቶች ላይ በተከታታይ የሚፈጠረው የዋጋ ንረት እና ለግንባታ የሚሆኑ ግብዓቶች በሚፈለገው ልክ በገበያ ላይ አለመገኘት ለሥራቸው ችግር እየፈጠረ መሆኑን አንስተዋል።

# ከእንስሳት ሃብት ተገቢውን ጥቅም ለማግኘት ሰፊ ጥረት ይጠይቃል

## - የኤክስፖርት ቄራዎች በዓመት የሚያመርቱት ከአቅማቸው ከ20 እስከ 30 በመቶ ብቻ ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**



ቢሾፍቱ፡- ኢትዮጵያ ካላት እምቅ የእንስሳት ሀብት አንጻር ተገቢውን ጥቅም ለማግኘት ሰፊ ጥረት እንደሚያስፈልግ ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

የግብርና ሚኒስትር ዶክተር ግርማ አመንቴ የእርድ እንስሳት አቅርቦትን ለማሻሻል ያለመ የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ ላይ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ እምቅ የእንስሳት ሀብት ቢኖራትም ዘርፉ ለሃገር ኢኮኖሚ እያበረከተ ያለው ድርሻ የሚፈለገውን ያክል አይደለም።

ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብት ቁጥር ከቀዳሚዎቹ ተርታ እንደምትሰለፍ ተደጋግሞ ይነሳል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ዘርፉ ባለመዘመኑና ገበያ ተኮር ባለመሆኑ የኤክስፖርት ቄራዎቻችን በዓመት እያመረቱ የሚገኙት ከአቅማቸው ከ20 እስከ 30 በመቶ ብቻ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በመሆኑም ዘርፉ ለአገር ኢኮኖሚ ማበርከት የሚገባውን ድርሻ እንዲያበረክትና የአርሶ-አርብቶ አደሮችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ርብርብ እንደሚጠይቅ ገልጸዋል።

ዘርፉን ለመቀየር በመንግሥት በኩል ቁርጠኝነት መኖሩን አመልክተው፤ ለዚህም በጠቅላይ ሚኒስትሩ አነሳሽነት የተጀመረው የሌማት ትሩፋት ዋና ትኩረቱን እንስሳት ሀብት ላይ አድርጎ እየተሠራበት መሆኑ ጥሩ ማሳያ ነው ብለዋል።

በዘርፉ የሕገወጥ ንግድ መበራከት ሃገሪቱ ከዘርፉ ተገቢውን ጥቅም እንዳታገኝ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ በዘርፉ ንግድ ፍቃድ ወስደው እየተንቀሳቀሱ ያሉ ባለሀብቶችም የገቡትን ቃል አክብረው በተገቢው መንገድ መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ተናግረዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ዘርፉን የመከታተል፣ የመደገፍና የመቆጣጠር ተግባሩን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።

የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሳሕሉ ሙሉ በበኩላቸው፤ ባለፉት ዓመታት ዘርፉን ለማዘመን ሥራዎች ቢሠሩም ካለው ሀብት አንጻር ለአገር የሚሰጠውን ጥቅም ለማሳደግ አሁንም በቅንጅት መሥራት ይገባል ብለዋል።

የኤክስፖርት ቄራዎች በዓመት 200 ቶን ሥጋ የማቀነባበር አቅም እንዳላቸው አስታውቀው፤ ዘርፉ በዘመናዊ መንገድ እንዲመራና ገበያ ተኮር እንዲሆን ሰፊ ጥረት ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

ዘርፉ ባለፉት ስምንት ወራት 65 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማግኘቱን ገልጸው፤ አፈጻጸሙ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ያነሰ መሆኑን አስታውቀዋል። በመሆኑም በሚቀጥሉት አራት ወራት ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ከ53 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ለማግኘት ታቅዷል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ባለፉት አስር ዓመታት ከሥጋ ኤክስፖርት ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘቷን አስታውሰው፤ ከ2013 እስከ 2023 ዓ.ም ባሉት 10 ዓመታት 7 ነጥብ 8 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ በ2014 በጀት ዓመት ከሥጋ ኤክስፖርት 119 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማግኘቷ የሚታወስ ነው።

# አገልግሎት ያቆሙ 18 ባቡሮች ወደ አገልግሎት ሲመለሱ ነው

## - ቀላል ባቡሩ በዓመት 41 ሚሊዮን ሰዎችን ያጓጉዛል

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- ቻይና ባቀረበችው የመለዋወጫ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት ያቆሙ 18 ባቡሮች ወደ አገልግሎት እንደሚመለሱ የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት ድርጅት አስታወቀ፡፡

የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኢንጂነር ሙሉ ቀን አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ቻይና የአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር የመለዋወጫ ድጋፍ በማድረጓ አገልግሎት መስጠት ያቆሙ 18 ባቡሮችን ሥራ ለማስጀመር እየተሠራ ይገኛል።

የአዲስ አበባ ቀላል ባቡሮች በመለዋወጫ እጥረት፣ በኃይል መቆራረጥና በተለያዩ ችግሮች ሥራ ሲያቆሙ መለዋወጫቸው ከውጭ ሃገራት ተገዝቶ የሚገባ በመሆኑ ለተወሰኑ ጊዜያት መዘግየት ተፈጥሮ እንደነበር አስታውሰዋል።

የኃይል መቆራረጥ ችግሮች እንዳይከሰቱ እንዲሁም በጥራት ጉድለት ምክንያት ለረጅም ጊዜ የቆዩ ኬብሎችን የመቀየር ሥራ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ጋር በመሆን እየተሠራ መሆኑን ኢንጂነር ሙሉቀን ጠቁመዋል፡፡

እንደ ኢንጂነር ሙሉቀን ገለጻ፤ ለባቡር የሚውለውን የኃይል ማቀባበያ ሲስተሞችን በየጊዜው መፈተሽ እንዲሁም የባቡር ሀዲዶችን ንቅለ ተከላ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በሚሠሩት ባቡሮች አማካኝነት በርካታ ሕዝብ በአዲስ አበባ የትራንስፖርት አገልግሎት እያገኘ ነው፡፡ አሁን ላይ በመዲናዋ ያሉት ባቡሮች በቀን 60ሺ እንዲሁም በዓመት 41 ሚሊዮን ሰዎችን ያጓጉዛሉ፡፡

ከፍተኛ የባቡር ትራንስፖርት ፍላጎት የሚስተዋልበት መስመር ከሃያት ተነስቶ ጦር ኃይሎች የሚደርሰው መስመር መሆኑን ገልጸው፤ የባቡር መለዋወጫ ድጋፉ በርካታ ተገልጋዮችን ለማስተናገድ እንደሚረዳ ተናግረዋል።

ኢንጂነር ሙሉ ቀን እንዳስታወቁት፤ ሥራ ያቆሙት ባቡሮች ተጠግነው ወደ ሥራ ሲመለሱ አሁን ላይ የሚሰጠውን አገልግሎት በእጥፍ የማሳደግ አቅም ይፈጠራል፡፡

የኅብረተሰቡን የትራንስፖርት እጥረት ከማቃለል ባለፈ የባቡር ትራንስፖርት ምልልሱን በማሳጠር ተገልጋዮች በአጭር የቆይታ ጊዜ ወደሚፈልጉት መስመር እንዲሳፈሩ የሚረዳ የተቀላጠፈ አገልግሎት ያገኛሉ ብለዋል።

ከዚህ ባለፈ የቀላል ባቡር መስመሩን ደህንነት በማስጠበቅ ረገድ ሰፊ ሥራ መሠራት አለበት ያሉት ኢንጂነር ሙሉቀን፤ ለባቡሩ መከለያ የተሠራውን አጥር የሚያፈርሱ ግለሰቦች በመኖራቸው ሊታረም እንደሚገባ ጠቁመዋል።

መንግሥትና የጸጥታ ኃይሎች የቀላል ባቡሩን ደህንነት ከማስጠበቅ አኳያ እየሠሩት ካለው ሥራ በተጨማሪ ኅብረተሰቡ የባለቤትነት ስሜት ተሰምቶት የሚስተዋሉ ወንጀሎችን ሊከላከል ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# በከተማዋ የገበያ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በእነዚህ የገበያ ቦታዎችም ባለፉት ስምንት ወራት በድምሩ የ300 ሚሊዮን ብር የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች ግብይት መፈጸሙን አብራርተዋል፡፡ ምርቶቹን ለሸማቹ ማኅበረሰብ በአቅራቢያው ተደራሽ በማድረግ በተመጣጣኝ ዋጋ ግብይት እንዲፈጸም መደረጉን ገልጸዋል፡፡

ማኅበሩ የገበያ ንረትን ለማረጋጋት የተለያዩ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ ተደራሽ አድርጓል፤ በአምራችና በሸማቾች መካከል ያለውን የገበያ ትስስር አጠናክሯል፤ ሕገወጥ ደላላዎችን በመቆጣጠር የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት መጠነ ሰፊ ሥራ ተሠርቷል፤ ይህም ተጠናክሮም ይቀጥላል ሲሉ አቶ ጥላሁን ጠቁመዋል፡፡

ኅብረተሰቡ በሰንበት ቀን ገበያ መገበያየት ፍላጎቱ እየጨመረ መጥቷል ያሉት አቶ ጥላሁን፤ የገበያ ትስስሩን በተለያዩ ክልሎች በማስፋፋት አቅርቦትና ፍላጎትን የማቀራረብ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት እየሠራበት መሆኑንም ነው የገለጹት ፡፡

በተጨማሪም አቅርቦትን አስተማማኝ በማድረግ የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ከክልል ሸማች ማኅበራትና አምራቾች ጋር ኤጀንሲው የተሳለጠ የገበያ ትስስር ለመፍጠር የጋራ መግባባት ላይ መድረሱንም ጠቅሰዋል ፡፡

በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ አምራቾች በቀጥታ ምርታቸውን ለገበያ እንዲያቀርቡ ሲደረግ መቆየቱን ጠቅሰው፤ በቀጣይም አምራቾች በቀጥታ ምርታቸውን ገበያ እንዲያቀርቡ የማድረግ ሥራው እንደሚቀጥል ነው የተናገሩት፡፡

ማኅበሩ ከከተማ አስተዳደሩ በተገኘ የአንድ ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ተዘዋዋሪ ብድር የግብርናና ኢንዱስትሪ ምርቶችን ከክልሎች ወደ መዲናዋ የማስገባትና በተለያዩ የገበያ አማራጮች ምርቶችን በመጠቀም ለኅብረተሰቡ ተደራሽ የማድረግ ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም አመልክተዋል፡፡

# በደቡብ ኦሞ ዞን የማሌ፣ የሐመር እና የበናፀማይ ወረዳዎች ለድርቅ ይበልጥ ተጋላጭ ሆነዋል

በኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን የማሌ፣ የሐመር እና የበናፀማይ ወረዳዎች ለድርቁ ይበልጥ ተጋላጭ መሆናቸውን የወረዳዎቹ ዋና አስተዳደር አስታውቀዋል።

በደቡብ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን የበናፀማይ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሙዳ ዋንጬ እንደገለጹት፣ በድርቁ ምክንያት 577 ሺህ 375 እንስሳት ወደ ማጎ ብሔራዊ ፓርክ ገብተዋል። የወይጦ ወንዝ በመድረቁ የተነሳ መኖ ማብቀልና ለእንስሳቱ ማቅረብ አልቻልንም ሲሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልጸዋል።

በወረዳው ከአንድ ሚሊዮን 200 ሺህ ብር በላይ የእንስሳት መድኃኒት በመግዛት ክትባት እንዲያገኙ በመደረጉ እንስሳቱ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቋቋም እያገዘ ነው ብለዋል።

በወረዳው የወይጦ ወንዝ መድረቁን ተከትሎ ከፍተኛ የውሃ እጥረት በመከሰቱ እስካሁን 407 ተማሪዎች ውሃ ለመፈለግ ሲሉ ከትምህርት ቤት ለመቅረት መገደዳቸውን ያስረዱት አቶ ሙዳ፣ በውሃ ችግር ምክንያት 18 ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ ሊዘጉ ይችላሉ። ይህ ከመሆኑ በፊት መንግሥት ውሃ ማቅረብ እንዳለበት አሳስበዋል።

የማሌ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ጳውሎስ ጉዳና በበኩላቸው፣ በድርቁ ምክንያት 50 በመቶ የወረዳው ነዋሪ ችግር ላይ ነው። ከ2012 ዓ.ም መጋቢት ወር ጀምሮ በወረዳው አርብቶ አደር አካባቢ በተከሰተው የዝናብ እጥረት እስካሁን 51 ሺህ 382 ያህል ዜጎች ለከፍተኛ የምግብ እጥረት መጋለጣቸውን ገልጸዋል።



አቶ ሙዳ ዋንጬ



አቶ ፎራ ገርሾ

በተከታታይ ለሦስት ዓመታት ዝናብ ባለመዝነቡ ድርቅ ተከስቶብናል ያሉት ደግሞ የሐመር ወረዳ ዋና አስተዳደር አቶ ፎራ ገርሾ ናቸው። ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ እንደ ወይጦ ያሉ ወንዞች ደርቀዋል፣ የመኖ እጥረትም አጋጥሟል። በዚህም ባለፉት ሁለት ወራት ብቻ በድርቁ ምክንያት ከ20 ሺህ በላይ እንስሳት መሞታቸውን ገልጸዋል።

# ኢትዮ አግሮ የበጋ መስኖ ስንዴና ቅመማ ቅመም ኤግዚቢሽን ተከፈተ

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ አግሮ የበጋ መስኖ ስንዴና ቅመማ ቅመም ኤግዚቢሽን በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ከትናንትና ጀምሮ መካሄድ ጀምሯል፡፡ የቅመማ ቅመም ምርትን በብዛት ለውጪ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ገለጸ።

በኤግዚቢሽኑ መክፈቻ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አዱኛ ደበላ እንደተናገሩት፣ የቅመማ ቅመም ምርትን ለውጪ ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሪን ለማሳደግ በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ ቀደም በቅመማ ቅመም ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ላይ የአሠራር ሥርዓት እንዳልነበር የጠቀሱት ዶክተር አዱኛ በዘንድሮ ዓመት ወደ 43 ሀገራት የሚላኩ 16 የተለያዩ የቅመማ ቅመም አይነቶች የኤክስቴንሽን አደረጃጀት መመሪያ፣ የቅመማ ቅመም ጥራት፣ የግብይትና አምራረት ፓኬጆች ተዘጋጅተዋል፡፡

ዶክተር አዱኛ አክለውም የቅመማ ቅመም ልማትን ለማሳደግ፣ የዘርፉን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ውጤታማ ለማድረግና አርሶ አደሮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በስፋት ይሠራል ነው ያሉት፡፡

በኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ምክትል ዳይሬክተርና የቅመማ ቅመም ግብይት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ሻፊ ዑመር በበኩላቸው እንደገለጹት፣ ኤግዚቢሽኑ የተዘጋጀበት ዓላማ ከተለያዩ ክልሎች ቅመማ ቅመምን በተመለከተ ያለውን ሀብት ለማስተዋወቅ፣ አርሶ አደሮችን፣ ዩኒየኖችንና ላኪዎችን ለማስተሳሰር ነው፡፡

በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና የተሻለ ቅመማ ቅመም ምርትን ለገበያ ማቅረብ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚረዳ ኤግዚቢሽን ነው ያሉት አቶ ሻፊ፣ ከኤግዚቢሽኑ ጎን ለጎን በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አማካኝነት ጥናታዊ ጽሑፎች እንደሚቀርቡ ጠቁመዋል።

ለቡና የተሰጠውን ትኩረት ያክል ለቅመማ ቅመም ምርትም ትኩረት ተሰጥቶት ሊሠራ እንደሚገባ አቶ ሻፊ አስረድተዋል፡፡

እንዲህ አይነት ኤግዚቢሽን መካሄዱ ለዘርፉ መነቃቃትን ከመፍጠር ባለፈ ዘርፉ በደንብ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሠራ ይረዳል ብለዋል፡፡

በቀጣይ ዓመታት የቅመማ ቅመም አመራረታችንን ጥራት ለማሻሻል የሚያስችል ለአብዛኛው ሰብሎች የጥራት ደረጃ የተዘጋጀ በመሆኑ ግብይቱ ከዘልማድ አሠራር ወጥቶ በሕግ የሚመራ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል።

# ዞኑ ከ563 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት መድቦ የመልሶ ግንባታ ሥራ እየሠራ ነው

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በሰሜኑ ጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን መልሶ ግንባታ ለማከናወን ከ563 ነጥብ 9 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት ተመድቦ ወደ ሥራ እንደተገባ የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር አስታወቀ።

የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ፋሲል አረጋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ከመንግሥትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የተገኘ ከ563 ሚሊዮን 907 ሺህ ብር በላይ ተመድቦ ጉዳት የደረሰባቸውን ተቋማት በተሻለ ደረጃ መልሶ ለመገንባት ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

ለዞኑ መልሶ ማቋቋም ግንባታ ከተገኘው 563 ሚሊዮን 907 ሺህ ብር ውስጥ የአማራ ክልል መንግሥት 267 ሚሊዮን ብር መበጀቱን የገለጹት አቶ ፋሲል፣ ተጨማሪውን ድጋፍ ከተለያዩ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች መገኘቱን አስታውቀዋል።

በተጨማሪ በዞን ደረጃ ከባለሀብቶች፣ ከኢንዱስትሪዎችና ከመንግሥት ሠራተኞች 150 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።

በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት በዞኑ የሚገኙ አንድ ሺህ 502 የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መውደማቸውን ኃላፊው አስታውሰው፣ በዞኑ ቀድሞ አገልግሎት ይሰጡ የነበሩን ሁሉንም የጤና፣ የትምህርት፣ የወጣት ማዕከላት፣ የውሃና የግብርና ተቋማትን የመልሶ ግንባታ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።



አቶ ፋሲል አረጋ

ካለፉት ስድስት ወራት ጀምሮ የመልሶ ግንባታ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፣ ከጥገናና መልሶ ግንባታ ሥራዎች ባለፈ ተቋማቱን በቁሳቁስ የማጠናከር ሥራ መሠራቱን ተናግረዋል።

በአሁኑ ጊዜ በመንግሥት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በማኅበረሰቡ የነቃ ተሳትፎ ተቋማቱ ጥገናቸው እየተካሄደ ጎን ለጎንም አገልግሎት እንዲሰጡ እየተደረገ መሆኑን አስረድተዋል።

በአካባቢው የተፈጠረውን ሰላም በመጠቀም የመልሶ ግንባታ ሥራዎች በስፋት መከናወናቸው ማኅበረሰቡ አስፈላጊውን አገልግሎት እንዲያገኝ የጎላ ፋይዳ አለው ብለዋል።

ከተቋማት መልሶ ግንባታ በተጨማሪ ቤታቸው ለፈረሰባቸው 800 አርሶ አደሮች ለቤት ግንባታ የሚውል ለእያንዳንዳቸው 50 ቆርቆሮና የሚስማር ድጋፍ ተደርጓል። በተጨማሪ ለ652 ሴቶች የሥነልቦና እና የመቋቋሚያ ስልጠና በመስጠት ለእያንዳንዳቸው የ30 ሺህ ብር ድጋፍ እንደተደረገላቸው አስታውቀዋል።

በዞኑ መልሶ የማቋቋም ሥራ በሁሉም ዘርፍ እየተከናወነ ቢሆንም የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ሁሉም ባለድርሻ አካላት እገዛ በማድረግ ማኅበረሰቡ ከደረሰበት የኢኮኖሚ እና የሥነልቦና ጉዳት መልሶ እንዲቋቋም የማድረግ ሥራ በተጠናከረ ሁኔታ ሊቀጥል እንደሚገባ አቶ ፋሲል አሳስበዋል።

# በከተማዋ ከ214 ሺህ በላይ ተገልጋዮች ዘመናዊ የፍሳሽ ማስወገጃን እየተጠቀሙ ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ከ214 ሺህ በላይ ተገልጋዮች ዘመናዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ተሠርቶላቸው ተጠቃሚ መሆናቸውን የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን አስታወቀ። ዘመናዊ የፍሳሽ መስመሩ ወጪንና ጊዜን የሚቆጥብ በመሆኑ ኅብረተሰቡ በአግባቡ መጠቀም እንዳለበት ባለስልጣኑ አሳስቧል።

የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የፍሳሽ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር አለማየሁ መንግሥቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ከሚሠራቸው ሥራዎች መካከል ፍሳሾችን ከኅብረተሰቡ ሰብስቦ በማጣራት መልሶ የመጠቀም ሥራ አንዱ ነው። በዚህም ከ214 ሺህ በላይ አባወራዎች ዘመናዊ የፍሳሽ ማስወገጃን እየተጠቀሙ ይገኛሉ።

በአዲስ አበባ ከሚኖረው አባወራ 32 በመቶው ዘመናዊ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ተጠቃሚ ነው ያሉት ኢንጂነር አለማየሁ፤ ቤንዚን፣ ናፍጣ፣ የሞተር ዘይት እና የተለያዩ ኬሚካሎችን ወደ ፍሳሽ ማስወገጃ ጣቢያው የሚለቁ ግለሰቦች በጣቢያው ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠሩ መሆኑን ገልጸዋል።

በከተማዋ የሚገኙ የተለያዩ ፋብሪካዎችም በድብቅ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመራቸውን ወደ ማጣሪያ ጣቢያው ከሚሄዱ መስመሮች ጋር እንደሚያገናኙ አስረድተው። እንዲህ ባሉት ተቋማት ላይ በተለያዩ ጊዜያት ርምጃ መወሰዱን ተናግረዋል።

እንደ ኢንጂነር አለማየሁ ገለፃ፣ ባለሥልጣኑ ፍሳሽን በመኪና ወይም በዘመናዊ መንገድ በፍሳሽ መስመር የማስወገድ ሥራ የሚያከናውን ቢሆንም ሙሉ ለሙሉ ሥርዓቱን በዘመናዊ አሠራር ለመተካት እየሠራ ነው። በአሁን ወቅትም በከተማዋ አንድ ሺህ 638 ኪሎ ሜትር የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች አሉ። የፍሳሽ መስመር ተደራሽ በሆነባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ነዋሪዎች መስመሩን አገናኝተው ዘመናዊ የፍሳሽ አወጋገድ ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና ኅብረተሰቡ መፀዳጃ ቤቶች ውስጥ ባዕድ ነገሮችን ባለመጨመር የፍሳሽ መሠረተ ልማቶችን ከጉዳት መጠበቅ አለበት ብለዋል።

የፍሳሽ ቆሻሻ የኅብረተሰብ ጤና ጠንቅ እንደመሆኑ መጠን በዘመናዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ሥርዓት መወገድ እንዳለበት የገለጹት ምክትል ሥራ አስፈፃሚው፣ ከከተማዋ የሚመጣውን ፍሳሽ ተቀብለው በቀን ከአራት መቶ እስከ 100 ሺ. ሜትር ኪዩብ ማጣራት የሚችሉ ትሪትመንቶች እንዳሉ ጠቅሰው እስከ አሁን ከተሠሩት የጋራ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ 12 የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያዎች ለዚህ ተብሎ የተሠሩ ናቸው ብለዋል።

ይሁንና ስለፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ኅብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ የሌለው በመሆኑ ግንዛቤ በማስጨበጥ ረገድ ከፍተኛ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ ተናግረው፣ ዘመናዊ የፍሳሽ መስመሩን በአብዛኛው የሚጠቀሙት የጋራ መኖሪያ ቤቶች መሆናቸውን ገልጸዋል።

ዜና

# "የተከሰተው የዋጋ ንረት በምርት እጥረት ሳይሆን በፖለቲካዊ ሴራ ነው"

- አቶ ኃይሉ አዱኛ የኦሮሚያ ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ

ማሕሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ ፡-በቅርቡ በእህል ምርቶች ላይ የተከሰተው የዋጋ ንረት በምርት እጥረት ሳይሆን የፖለቲካዊ ዓላማ ባላቸው ግለሰቦች በገበያው ላይ በፈጠሩት ሴራ ምክንያት መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ ገለጸ።

የኦሮሚያ ክልል ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይሉ አዱኛ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ትናንት በጽሕፈት ቤታቸው በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ በቅርቡ በእህል ምርቶች ላይ የተከሰተው የዋጋ ንረት የምርት አቅርቦት እጥረት ተፈጥሮ ሳይሆን ፖለቲካዊ ዓላማ ባላቸው ግለሰቦች ሆን ተብሎ የተሸረበ ፖለቲካዊ ሴራ ነው። ድርጊቱ የመንግሥትን ተቀባይነት ለማሳጣትና መንግሥት የጀመረውን ስንዴን ወደ ውጭ የመላክ ተግባር እንዲሰረዝ ለማድረግ ታስቦ የተደረገም ነው።

በአሁኑ ጊዜ በኦሮሚያ ከተሞችም ሆነ በአዲስ አበባ ከተማ የፖለቲካ ዓላማ ያላቸው ግለሰቦች ምርትን በመደበቅ የዋጋ ንረት እንዲከሰት በማድረግ መንግሥት ላይ ጫና ለመፍጠር እየሞከሩ ነው ያሉት አቶ ኃይሉ የክልሉ መንግሥት ችግሩን ለመፍታት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር በመተባበር በኅብረት ሥራ ማኅበራት አማካኝነት ምርቶችን በቀጥታ ለኅብረተሰቡ በማቅረብ የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት እየሠራ እንደሆነ ገልጸዋል።

ኅብረት ሥራ ማኅበራት አሁን ላይ 10 ቦታዎች ላይ የእህል ምርቶቻቸውን እያቀረቡ እንደሆነ ጠቁመው፤ በሕገወጦች ላይም ርምጃ እየተወሰደ እንደሆነ ተናግረዋል።

በ2015ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል በበጋ መስኖ ስንዴ ከአንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በዘር የተሸፈነ ሲሆን እስካሁንም ከሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን በላይ ኩንታል ምርት መሰብሰብ መቻሉን አመልክተዋል።

በአጠቃላይ በ2014/15 ዓ.ም የመኸር የምርት ዘመን ስድስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር በመሸፈን ከ202 ነጥብ 9 ሚሊዮን ኩንታል የተለያዩ የምርት አይነቶች መሰብሰቡን አስታወቀዋል። ይህም የክልሉ ምርታማነት ሁለት ነጥብ 7 በመቶ እያደገ መሆኑን የሚያሳይ ነው ብለዋል።

አቶ ኃይሉ በተጨማሪም በኦሮሚያ ክልል ቦረናን ጨምሮ በአስር የኦሮሚያ ክልል ዞኖች ላይ የተከሰተውን ድርቅ በዘላቂነት ለመፍታት የአጭር እና ረጅም ጊዜ እቅድ በመንደፍ እየተሠራ እንደሆነ ገልጸው፤ ለድርቅ ተጎጂዎች የሚሆን የዕለት ደራሽ የሰብዓዊ ርዳታ በሁለት ዙር አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር የሚገመት የድጋፍ አይነቶች ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ማሰባሰብ መቻሉን አብራርተዋል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍም በቦረና ዞን ውሃ የማቆር እና 14 የውሃ ፕሮጀክቶችን የማልማት ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ከዚህ ባለፈ በድርቅ ለተጎዱ የኅብረተሰብ ክፍሎች መልሶ ለማቋቋም እንዲሁም ጥሪት የሚያፈሩበትን ሁኔታ ለመፍጠር ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

## አባል ሃገራቱ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በምሥራቅና በአፍሪካ ቀንድ የሚስተዋለውን የሠራተኞች ፍልሰትን ለመከላከልና መብታቸውን ለማስጠበቅ ዓላማ ባደረገው የሚኒስትሮች ፎረም የማጠቃለያ መድረክ ላይ የሥራና ክህሎት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል ባደረጉት ንግግር፣ ፎረሙ የክልላዊ ውሕደትና የነጻ ንግድን አስፈላጊነት ያጎላል። በቀጣናው ውስጥና በመላው አፍሪካ የጉልበት ሠራተኞች እንቅስቃሴ፣ በስደት አስተዳደርና በክልላዊ ውሕደት ዙሪያ የቁልፍ ባለድርሻ አካላት ትብብር አስፈላጊ ነው።

ሚኒስትሯ አክለውም፣ አህጉራዊና ቀጣናዊ ሁኔታዎች የሠራተኛ እንቅስቃሴ ጉዳይ፣ የሥርዓተ ፆታ እና የሠራተኛ ፍልሰት አስተዳደር በትኩረት ሊሠራበት ይገባል። ሕጋዊ የሥራ ስምሪትና የማኅበራዊ ጥበቃ ጉዳዮች ተያያዥነት ያላቸው ስለሆነ ለአፍሪካ 2063 አጀንዳ መሳካት በሥራ ዕድል ፈጠራና በመሰል ጉዳዮች በትብብር መሥራትን ይጠይቃል ነው ያሉት።

የአባል ሀገራት የቀጣናዊ ፎረም በሠራተኞች እንቅስቃሴ ዙሪያ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ መሠራት እንዳለበት የጠቆሙት ወይዘሮ ሙፈሪያት፤ ኢትዮጵያ የሠራተኞችን ፍልሰት ለመቆጣጠር አካታች የሆነ ፖሊሲ በመንደፍ እየሠራች ነው፡፡ በዚህም አበረታች ውጤት አስመዝግባለች፡፡ የዲያስፖራውን አቅም በመጠቀም በመዳረሻ ሃገራት የቆንስላ አገልግሎቶች እንዲጠናከሩ ተደርጓል፡፡ አንዳንድ አባል ሀገራት የብሔራዊ የፍልሰትና የዲያስፖራ ፖሊሲ የማጽደቅና የመከለስ ሥራዎችን ማከናወናቸውን ገልጸዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በሊቀመንበርነት የምትመራው ፎረሙ አባል አገራቱ በፍልሰተኞች መረጃ አያያዝና አስተዳደር ሥርዓታቸውን ያዘመኑ አገራት እንዳሉ በመጥቀስ፤ የገበያ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የአቅም ማጎልበት ሥራ ማሳደግ፤ ከስደት ተመላሾችን ለማቋቋም ሥርዓተ ፆታን መሠረት ያደረገ ተቋማዊ ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል፡፡ አንዳንድ አባል አገራት የብሔራዊ የስደት ፖሊሲን፣ የዲያስፖራ ፖሊሲን ያረቀቁ ሲሆን ሌሎች ደግሞ የስደትና የስደት ጉዞን ገምግመዋል። በቀጣይም የጎደሉትን በመሙላት ሊሠሩ ይገባል ብለዋል፡፡

በዓለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ ዳይሬክተር ሞሐመድ አበዲኬር በበኩላቸው፤ የዓለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት (አይኦኤም) የቀጣናው መረጃ እንደሚያመላክተው በምሥራቅና አፍሪካ ቀንድ ፍልሰተኞችን በብዛት የሚይዙት 50 ነጥብ 4 በመቶ ሴቶች ናቸው፡፡ በቀጣናው የሠራተኞችን ደህንነት፣ ፍልሰትና የሥራ ዕድል ፈጠራን ለማሳደግ አባል ሃገራቱ ተናበው ሊሠሩ ይገባል፡፡ ድርጅቱ ይህን ሥራ ለመደገፍ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ እየሠራችው ያለው የፍልሰተኞች አስተዳደር ፖሊሲ ውጤት እያሳየ ነው፡፡ ፖሊሲዎች በመንደፍ አባል ሃገራቱ በስደት መረጃ አስተዳደር ውስጥ እድገት አሳይተዋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በቀጣይም ዲያስፖራውንና ኤምባሲዎችን በማስተሳሰር የበለጠ መሥራት እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

ላለፉት አምስት ቀናት ሲካሄድ የቆየው የምሥራቅና አፍሪካ ቀንድ አባል ሃገራት የሚኒስቴሮች ፎረም በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን 17 ነጥቦች ያቀፈ ሰነድ በመፈራረም ኢትዮጵያን በሊቀመንበርነት በማስቀጠል ተጠናቋል፡፡

## የኢፕድ ስልጠና ማዕከል...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ይገኛል፡፡ በትላንትናው ዕለትም ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሠራተኞች የተሰጠው ሥልጠና 21ኛው ዙር ነው።

በሥልጠናው ማጠናቀቂያ የተገኙት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የይዘት ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ፍቃዱ ከተማ እንደተናገሩት፤ የሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን የክህሎትና የአቅም ግንባታ ስልጠና የተቋምን አቅም ለመገንባትና ለችግሮች አዳዲስ መፍትሔ ለማግኘት ያስችላል። ኢፕድ በዘርፉ ለ82 ዓመት ያካበተውን ልምድ መሠረት በማድረግ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያዎች ሥልጠና መስጠቱ በሁለቱ ተቋማት መካከል ያለውን ግንኙነት ያጠናክራል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሥልጠና ማዕከሉ በፌዴራልና በክልል ደረጃ ለሚገኙ የመንግሥትና የግል ድርጅቶች የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያዎችን በማሰልጠን ላይ ነው ያሉት ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚው፤ ዓለም የደረሰችበት የሚዲያና የቴክኖሎጂ ደረጃ ለመድረስ እንደሃገር እንደዚህ አይነት ሥልጠናዎች መለመድ አለባቸው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በዘርፉ ካለው የካበተ ልምድ በመነሳት የሀገሪቱን የሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን ክህሎትን ከፍ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ፍቃዱ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለተቋሙ ዕድገት እና ለሠራተኞች አቅም ግንባታ የሚያደርገውን ጥረት አድንቀዋል።

ከዚህ በኋላ የሚሰለጥኑ ሠልጣኞችም የሰማኒያ ሁለት ዓመት ሰነድና ልምድ እየጎበኙ በተግባር የሚሰለጥኑበት ሁኔታ እየተመቻቸ እንደሆነም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሕዝብ ግንኙነትና ሚዲያ ማኔጅመንት ሥራ አስኪያጅ አቶ ደረጄ አሰግደው በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሀገሪቱን ዕድገት ወሳኝ በሆነ መልኩ ለማራመድ በሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን ዘርፍ ስኬታማ ሥራዎችን መሥራት ይኖርበታል። ለዚህም በዘርፉ የ82 ዓመት ልምድ ያለውን የኢትዮጵያ ፕሬስ



ፎቶ - በፀሐይ ንጉሴ

ድርጅት መርጠን ሠልጥነናል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ82 ዓመት አንጋፋ ተቋም ጋር የፈጠረው ግንኙነት በባንኩ ዘርፍ የተለየ ችሎታና አቅም እንዲኖረው ያደርጋል ያሉት አቶ ደረጄ፤ በዘርፉ ልምድ ባለው ተቋም መሠልጠን የሚያስገኘውን ጥቅም መረዳት ችያለሁ። በተቋሙ ሥልጠና ስንወስድ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። ነገር ግን ከዚህ በኋላ ቀጣይነት ያለው ሥልጠና ለመውሰድ ሁኔታዎችን እናመቻቻለን ነው ያሉት።

በሥልጠናው ባንኮች በሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን ዘርፍ ብቁ ባለሙያ ሊኖራቸው እንደሚገባ ከመረዳት ባለፈ ባለሁበት ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን ምን ማድረግ እንዳለብኝ ከሥልጠናው ተረድቻለሁ ያለው ደግሞ የባንኩ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ምንተስኖት አስቻለው ነው።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አሠልጣኞች በዘርፉ ልምድ ያካበቱ በመሆናቸው በሥልጠናው የሚነሱት ጉዳዮች ለተግባር የሚያነሳሱና ለውጥ ለማምጣት የሚረዱ ናቸው። በዘርፉ ልምድ ባለው ተቋም መሠልጠኔም አስደስቶኛል ብሏል።

የባንኩ ኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ አቶ ደረጀ ጌታሁን በበኩሉ፤ በኢፕድ የተሰጠው ሥልጠና አብዛኛውን የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያና ጋዜጠኛ ብቁ እንዲሆን የሚያደርግ ነው። ስለዚህ ሌሎች በቢዝነስና በተለያዩ መስኮች ያሉ ባለሙያዎች እንዲሁም ድርጅቶች ሥልጠናውን ቢወስዱ ተጠቃሚ ይሆናሉ ብሏል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሥልጠና ማዕከል ከዚህ በፊት በተለያዩ የሥልጠና ርዕሶች ዙሪያ ለፌዴራልና ለክልል ተቋማትና የግል ድርጅቶች በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ውጭ ተመሳሳይ ሥልጠናዎችን በመስጠት ማስመረቁ ይታወሳል።

## በሃገሪቱ 13 ሚሊዮን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ሰባት ሚሊዮን በላይ ኩንታል እህል ማሰራጨት እንደተቻለም ተገልጿል።

የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ደበበ ዘውዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ የሃገሪቱ ክፍል በሚገኙ ሰብል አብቃይ አካባቢዎች፣ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር በሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ የድርቅ አደጋ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል። በዚህም በአሁኑ ወቅት 13 ሚሊዮን ዜጎች የድርቅ አደጋ ተጋላጭና የዕለት ድጋፍ የሚሹ ሆነዋል። የዝናብ መዘግየት፣ በመጠን አነስተኛና በስርጭት የተቆራረጥ መሆን፣ በሰብል ምርትና በእንስሳት ግጦሽ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ ጉዳቱን የከፋ አድርጎታል ነው ያሉት።

እንደ አቶ ደበበ ገለጻ፤ ድርቁ ከፍተኛ ጉዳት ካደረሰባቸው አካባቢዎች በኦሮሚያ ክልል ቆላማ በሆኑና አርብቶ አደር ማኅበረሰብ በሚኖርባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ዞኖች ላይ ማለትም፤ ቦረና፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ ዞኖች በሚገኙ ወረዳዎች ላይ ነው። በሱማሌ ክልል ደግሞ ከ11 ዞኖች ዘጠኙ ተጋላጭ ሆነዋል። እነዚህም ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ዶሎ፣ ኤረር፣ ጀረር፣ ሞጎትና ቆራሂ ናቸው። በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ውስጥም፣ ደቡብ ኦሞ፣ ወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞ፣ ኮንሶ፣ ደራሼ፣ አማሮ እና ቡርጂ ዞኖች በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች ድርቅ ተከስቷል።

በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር በሆኑ አካባቢዎች ላይ በዋናነት ዝናብ የሚያገኙባቸው ወቅቶች ላይ ዝናብ አለማግኘታቸው ድርቁን እንዳባባሰው አቶ ደበበ ጠቅሰዋል።

በአፋር ክልል ዞን 1፣2፣3፣ እና 4፤ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን ወሎና የኦሮሞ ብሔረሰብ ዞኖች፤ በትግራይ ክልል በምሥራቃዊ፣ ደቡባዊና ደቡብ ምሥራቅ ዞኖች ከፍተኛ የሆነ የኅብረተሰብ ክፍል የተፈናቀለበትና ጉዳት የደረሰበት መሆኑ በየአካባቢው ያለውን የድርቅ ሁኔታ አባብሶታል ነው ያሉት።

በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች በብዛት ዝናብ የሚያገኙባቸው አምስት ተከታታይ ወቅቶች አለመዝነቡ፤ እንዲሁም በመጠን አነስተኛ የሆነበትና በስርጭት መጠንም የቀነሰ መሆኑ ድርቁን የከፋ ካደረጉት ምክንያቶች ውስጥ ተጠቃሽ መሆናቸውን አቶ ደበበ አንስተዋል። ዝናቡ በአገባብ የሚዘገይበትና ፈጥኖ የሚያበቃበት ሁኔታ መኖር ለድርቁ ተጨማሪ መንስኤ እንደሆነም አብራርተዋል። የተራዘመ ደረቃማ አየር መፈጠሩና የአፈር እርጥበት የመያዝ አቅም የተሟጠጠበትና በሰብል ምርትና በግጦሽ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማድረሱ ድርቁን ካባባሱ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ እንደሆነም አመላክተዋል።

በመንግሥት፣ በዓለም ምግብ ፕሮግራም እንዲሁም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ጥምረት ድጋፎች እየተደረጉ ነው ያሉት አቶ ደበበ፤ በዚሁ መሠረት በአሁን ወቅት ለድርቅ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች እስካሁን አራት ሚሊዮን 753ሺህ 949 ኩንታል እህል መሠራጨቱን ገልጻዋል።

የሰብዓዊ ድጋፍ ፍላጎትን ለማሟላት ሁሉም ሴክተር መሥሪያ ቤቶች መረባረብ እንዳለባቸው፣ ኅብረተሰቡም የጀመረውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል።

አቶ ደበበ እንዳሉት፤ እ.ኤ.አ. በ2020 መገባደጃ ላይ የጀመረውና በምሥራቅ አፍሪካ የተከሰተው ተከታታይነት ያለው የድርቅ አደጋ በአፍሪካ ቀንድ ባለፉት 70 ዓመታት ከተከሰቱት ሁሉ የከፋ ነው። ድርቁ በተለይም በኢትዮጵያ፣ በኬንያና በሶማሊያ ከ36 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ዜጎችን ለከፋ ጉዳት የዳረገ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በ2023 ሊቀጥል እንደሚችል የቅድመ ማስጠንቀቂያ ትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ ብለዋል።

# አገልግል

## የቅዳሜ መጽሔት



## "ኢትዮጵያ ውሃን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራቴጂ ያስፈልጋታል"

**ዶክተር በለጠ ብርሃኑ**
**በህዳሴ ግድብ የቴክኒክ ባለሙያ ቡድን አባል**

ገጽ 6



አፈጻጸሙ እየተሻሻለ የመጣው

**ባለ 20 ወለሉ የትራንስፖርት ዘርፍ ዋና መስሪያ ቤት ሕንፃ ግንባታ**

ገጽ 14



**ማጣት መንጣትን በምስጋና**

ገጽ 16

የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን
HOUSING DEVELOPMENT CORPORATION

**ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም**

# የ20/80 እና 40/60 የቤት ዕድለኞች የውል አፈጻጸም በወፍ በረር ሲቃኝ

በአዲስ አበባ ቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን በ20/80 የቤት ልማት ፕሮግራም ለ14ኛ ዙር እና በ40/60 የቤት ልማት ፕሮግራም ለ3ኛ ዙር ባለፈው ኅዳር ወር 2015 ዓ.ም የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ዕጣ ማውጣቱ ይታወቃል። በዚህም መሠረት ከጥር 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ መገናኛ በሚገኘው የቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ቅጥር ግቢ ውስጥ በኮርፖሬሽኑ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ የጋራ መኖሪያ ቤት የቤት ባለ ዕድለኞች ውል በመዋዋል ላይ ይገኛሉ። በመሆኑም የቤት ዕድለኞች ውል መዋዋል ከጀመሩ ጀምሮ እስካሁን ያለው ውል የመዋዋል ሂደቱ ምን እንደሚመስል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ጋሻው ተፈራ የሰጡንን መረጃ እንደሚከተለው ይዘንላችሁ ቀርበናል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በ14ኛው ዙር የ20/80 እና 3ኛ ዙር 40/60 የቤት ልማት ፕሮግራም ዕጣ የወጣላቸው ነዋሪዎች ብዛት 25 ሺ 773 ሲሆን፤ ከነዚህ መካከል እስከ መጋቢት 6/2015 ዓ.ም ድረስ ወደ አንድ ማዕከል ቀርበው ተመዝግበው ቅፅ 09 የወሰዱት 25 ሺ 412 ሰዎች ናቸው። ከተያዘው እቅድ አንጻር 98 ነጥብ 60 በመቶ ተከናውኗል።

እንዲሁም በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በ40/60 የቤት ልማት ፕሮግራም 851 እንዲሁም በ20/80 የቤት ልማት መርሐ ግብር ደግሞ 12 ሺ 618 በአጠቃላይ 13 ሺ 469 ፋይል ተመዝግቦ ተናቧል። ቅፅ 09 ወስደው ከቀበሌ አስፈላጊውን ሂደት አጠናቀው ሪፖርት ካደረጉ በኋላ ከባንክ ጋር ያለውን የኦዲት ቅፅ 03 ወስደው አስጨርሰው ካርታ



**አቶ ጋሻው ተፈራ**

እንዲሠራላቸው 12 ሺ 618 ፋይሎች ተልከዋል። በዚህም ከተላኩ ፋይሎች ውስጥ የ11 ሺ 174 የቤት ዕድለኞች ካርታ ታትሞላቸዋል።

ውል ለመዋዋል ከመጡ በኋላ አስፈላጊውን መስፈርት ሳያሟሉ ተመላሽ የተደረጉ ፋይል ብዛት 775 የቤት ዕድለኞች ሲሆኑ፤ ከነዚህ ውስጥ ማስተካከል የሚገባቸውን አስተካክለው በመምጣት ፋይላቸው የተመዘገበው 454 ናቸው። በተጨማሪም የሚጠበቅባቸውን የባንክ ክፍያና ሂደት ባለመፈጸማቸው ባንክ እንዲታገዱ የእግድ ደብዳቤ ወደ ቤቶች ኮርፖሬሽን የላከው የሁለት ሺ 343 የቤት እድለኞች ዝርዝር ነው። ከዚህ ውስጥ የሚጠበቅባቸውን የባንክ ክፍያ በመፈጸም እግድ የተነሳላቸው 761 ሲሆኑ፤ ቀሪ እግድ ያልተነሳላቸው ደግሞ አንድ ሺ 582 ናቸው።

ሌላው እስከ መጋቢት 6/2015 ዓ.ም ወደ አንድ ማዕከል መጥተው ተመዝግበው ቅፅ 09 ወስደው ወደ መኖሪያ ቀበሌያቸው ወስደው ለማስመራት ቅፁን የወሰዱ ተዋዋዮች ብዛት 25 ሺ 323 ነው። በአንጻሩ እስከ መጋቢት 7/2015 ዓ.ም ድረስ 19 ሺ 579 ቤት እድለኞች ቅፅ 03 ወስደው ከባንክ ጋር ያለውን ሂደት (ፕሮሲጀር) ጨርሰው ቅፁን እንዲያመጡ ታቅዶ ነበር። ከዚህ አንጻር ቅፅ 03 ወስደው ከባንክ ጋር የሚጠበቅባቸውን ሂደት (procedure) ጨርሰው ቅፁን ያመጡ 17 ሺ 114 ናቸው። በአንጻሩ ቅፅ 03 ወስደው ከባንክ ጋር መዋዋል ሲገባቸው ያልተዋዋሉ የቤት እድለኞች 2465 ናቸው። ይህም አፈጻጸሙ 87 ነጥብ 45 በመቶ ነው።

በጥቅሉ እስከ መጋቢት 7/2015 ዓ.ም 19 ሺ 570 የቤት እድለኞች ውል ይዋዋላሉ ተብሎ ታቅዶ ነበር። በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በ40/60 የቤት ልማት መርሐ ግብር 162 እንዲሁም በ20/80 የቤት ልማት ፕሮግራም ደግሞ 14 ሺ 267 በድምሩ 14 ሺ 429 የቤት እድለኞች ውል ፈጽመዋል። አፈጻጸሙ 73 ነጥብ 73 በመቶ ነው። ይህም የሚያሳየው የቤት እድለኞች ቅፅ 09 እና 03 ከወሰዱ በኋላ ወደ አንድ ማዕከል ፈጥነው መጥተው መዋዋል ላይ ክፍተት እንዳለ ነው። ስለዚህ ቅፅ 09 እና 03 የወሰዱ የቤት እድለኞች አጠናቀው ወደ አንድ ማዕከል ቀርበው በአስቸኳይ መዋዋል ይጠበቅባቸዋል።

ከዚህ ባሻገር ከባንክ በደረሰን ሪፖርት መሠረት እስከ መጋቢት 6 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በ20/80 የቤት ልማት መርሐ ግብር ቅድመ ክፍያቸውን ያጠናቀቁ የቤት ዕድለኞች አንድ ቢሊዮን 856 ሚሊዮን 108 ሺ 838 ብር ለባንክ ገቢ አድርገዋል። በዚህ የቤት ፕሮግራም ሙሉ ክፍያ የከፈሉ ባለዕድለኞች ደግሞ 637 ቢሊዮን 367 ሚሊዮን 657 ሺ ብር ለባንክ ገቢ አድርገዋል።

በ40/60 የቤት መርሐ ግብር ቅድመ ክፍያቸውን ያጠናቀቁ የቤት ዕድለኞች 51 ሚሊዮን 498 ሺ 381 ብር ለባንክ ገቢ አድርገዋል። እንዲሁም በዚህ የቤት ልማት ፕሮግራም ደግሞ ሙሉ ክፍያ የከፈሉ የቤት ዕድለኞች 33 ሚሊዮን 268 ሺ 470 ብር ለባንክ ገቢ አድርገዋል። በጥቅሉ በሁለቱም የቤት ልማት መርሐ ግብር ሙሉ ክፍያ የከፈሉ 793 የቤት ዕድለኞች ናቸው።

በአጠቃላይ የቤት ዕድለኞች ቦሌ ክፍለ ከተማ ወደ ሚገኘው የኮርፖሬሽኑ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ መጥተው ለደረሳቸው የጋራ መኖሪያ ቤት ውል መዋዋል ሲገባቸው እስካሁን ያልተዋዋሉ ሰዎች እስከ መጋቢት 26 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በወጣው ውል የመዋዋያ መርሐ ግብር መሠረት እንዲዋዋሉ ኮርፖሬሽኑ ጥሪ ያቀርባል። ሆኖም በወጣው ውል የመዋዋያ መርሐ ግብር መሠረት ዕድለኞች ቀርበው ውል የማይፈጽሙ ከሆነ ቤቱን እንዳልፈለጉት ተቆጥሮ ተመላሽ እንደሚሆን ሊያውቁት ይገባል። ይህንንም በተደጋጋሚ በመገናኛ ብዙኃን ያሳወቅን በመሆኑ ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ የሚመጡ ባለዕድለኞች ተቀባይነት እንደማይኖረው ተረድተው በወቅቱ ውላቸውን እንዲፈጽሙ በድጋሚ ተቋሙ ጥሪውን ያቀርባል። ነገር ግን ጉዳያቸው በፍርድ ቤት የተያዘ፣ በሀገራዊ ጉዳይ ግዳጅ ላይ ያሉ ወ.ዘ.ተ ባለዕድለኞች በሚያቀርቡት ማስረጃ መሠረት እንደሚስተናገዱ ዳይሬክተሩ አቶ ጋሻው ተፈራ ተናግረዋል።

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹ኢትዮጵያ ውሃን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራቴጂ ያስፈልጋታል››

ዶክተር በለጠ ብርሃኑ
በህዳሴ ግድብ የቴክኒክ ባለሙያ ቡድን አባል

አስቴር ኤልያስ



**ትውልዳቸውም ሆነ እድገታቸው አዲስ አበባ ልዩ መጠሪያ ሰፈሩ ኮልፌ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን የተማሩት በሁለት የተለያዩ ትምህርት ቤቶች ነው፤ አንደኛው በቀድሞ አጠራሩ «እውቀት ወገኔ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት» ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በቀድሞው አጠራሩ «ሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት ቤት» ነው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በኮልፌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተምረው አጠናቀዋል። የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በእርሻ ምህንድስና ትምህርት በሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ተከታትለው በ1987 ዓ.ም ተመርቀዋል፤ የእርሻ ምህንድስና ትምህርት ሰፋ ያለ ዘርፍ ያለው ሲሆን፣ አንዱ ዘርፍ ውሃን ከመስኖ ጋር በተያያዘ ማልማት ላይ የሚያተኩር ነው። በመሆኑም እርሳቸው ከተመረቁ በኋላ አነስተኛ ግድቦችን ሰርቶ ለመስኖ ልማት ማዋል ላይ ሰርተዋል። ዲግሪያቸውን እንደያዙም በአማራ ክልል በዘርፉ የጥናትና ዲዛይን ባለሙያ ሆነው አገልግለዋል። በስምንት አነስተኛ ግድቦች ጥናት ላይ ተሳትፈዋል። በዛው በአማራ ክልል በወሎ የሲሪንቃ ምርምር ማዕከል በውሃ መስኖ ልማት ምርምር ላይ ለሶስት ዓመት ያህል ሰርተዋል። ለሁለተኛ ዲግሪያቸው ደግሞ ወደ ሕንድ አቅንተው ከውሃ ጋር በተያያዘ ሩርኪ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በውሃ ፍሰት ምህንድስና (በሃይድሮሎጂካል ኢንጂነሪንግ) ተምረዋል። ከሕንድ ከተመለሱ በኋላ በወቅቱ በውሃ ልማት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ገብተው ለሁለት ዓመት ያህል አገልግለዋል። ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ የመስኖ ጥናቶችና የልማት ስራዎች ላይ ከሰሩ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማቅናት በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በሲቪል ምህንድስና ትምህርት ክፍል የማስተማር ስራን ተቀላቅለው እስካሁንም በማስተማር ላይ ናቸው። ዩኒቨርሲቲ የመምጣታቸው ምስጢር ሶስተኛ ዲግሪያቸውን ለመስራት ጭምር በመሆኑ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በውሃ ኢንጂነሪንግ ምህንድስና ሶስተኛ ዲግሪያቸውን ሰሩ - የዛሬው የዘመን እንግዳችን ዶክተር በለጠ ብርሃኑ።**

**ዶክተር በለጠ፣ በተለይ ከአባይ ግድብ ጋር ተያይዞ ገለልተኛ የሆነ የሳይንሳዊ ቡድን በየሀገራቱ ሲቋቋም የዚያ ቡድን መሪ ሆነው ስራ የጀመሩ ናቸው። እኤአ ከ2017 ጀምሮ እስካሁን ሙሉ ተሳትፎ በማድረግ ላይ ሲሆኑ፣ የድርድሩም አባል ሆነው ቀጥለዋል። የግድቡ የቴክኒክ ቡድን አባልም ከሆኑት እንግዳችን ጋር ያደረግነውን ቆይታ ይዘን ቀርበናል።**

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በቂ የዝናብ ውሃ መጠን ያላት ሀገር እንደመሆኗ ውሃ ማጠራቀም የሚያስችላት እስከ ምን ያህል ሜትር ኪዩብ ነው?**

**ዶክተር በለጠ፡-** ይሄ ጥያቄ ወደ ውሃ ፍሰት ጥናት ይወስደናል። በአሁኑ ወቅት በዝናብ የምናገኘው አማካይ የውሃ መጠን በዓመት ወደ አንድ ሺ ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ ነው። ይህ በገጸ ምድር ዝናብ በምናገኝባቸው ቦታዎች የሚዘንበው የውሃ መጠን ስንገምተው ማለት ነው። ይህንን ሁሉ በቀጥታ ወደማጠራቀሚያ መቀየር አይቻልም። ሳይንሱ አብዛኛውን ጊዜ የሚያየው ከዚህ ውስጥ ከ60 እስከ 70 በመቶ አካባቢ የትነት አካል ነው። ከዚህ በኋላ ነው ወደገጸ ምድር ወይም ደግሞ ወደከርሰ ምድር ውሃ የሚቀየረው። በዚህ መነሻነት ስናየው 30 በመቶውን ወደታች እናገኛለን ብለን ብናስብ እስከ 300 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ የማጠራቀም አቅም አለን ማለት ነው። ጥሩ ጂኦጆሎጂ ያለው የመሬት ቦታ ካገኘን በከርሰ ምድርም ማጠራቀም ይቻላል።

ትልቁ ችግር የሆነው የገጸ ምድር ማጠራቀሚያ ከውሃ ትነት ውጭ ያለውን መቆጣጠር ይቻላል፤ የከርሰ ምድር ማጠራቀሚያውን ግን መቆጣጠር አይቻልም። መሬት ለመሬት ሰርጎ ሊባክን ይችላል። ስለዚህም ነው ብዙ ጊዜ የገጸ ምድር ማጠራቀሚያን የምንመርጠው። ይህ እንዳለ ሆኖ እኛ በገጸ ምድር ላይ ያለንን አቅም አሳድገን በትንሹ ወደ 300 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ ብናጠራቅም አሁን ላለን የሕዝብ ብዛት እና ወደፊትም እያደገ ለሚመጣው የሕዝብ ቁጥር ብናካፍለው በትንሹ በአንድ ሰው ከአንድ ሺ በላይ ሜትር ኪዩብ ውሃ በዓመት እናገኛለን። ስለዚህ የማጠራቀም አቅማችን ከአንድ ሺ ፐር ካፒታል ከሆነ ከውሃ እጥረት እንወጣለን። ነገር ግን እዛ ላይ አልደረስንም።

**አዲስ ዘመን፡- የሚገኘውን የውሃ ሀብት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም በቀጣይ ከሁሉም በላይ ትኩረት ሰጥተን ልንሰራ የሚገባው ምን ላይ ነው?**

**ዶክተር በለጠ፡-** ውሃን በአግባቡ ይዞ ለመጠቀም ሰላሙም ሆነ የፖለቲካ መረጋጋቱ ፋይዳቸው ከፍ ያለ ነው። ነገር ግን ኢትዮጵያ በዋናነት ውሃ ተኮር ስትራቴጂ ያስፈልጋታል። ኢትዮጵያ በትክክል ማመን ያለባት ነገር ያልተጠቀመችው ሀብት የት ዘንድ ነው ያለው የሚለው ሲታይ ውሃዋን መሆኑን ማወቅ ነው። በእርግጥ በሌሎችም የተፈጥሮ ሀብት የበለጸገች ሀገር ናት። ነገር ግን በቀላሉ የሚገኝ በተለይ በዝናብ ሀብቷ የምትታወቅ መሆኗን ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያ ውሃን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራቴጂ ያስፈልጋታል። ውሃን ማዕከል ስናደርግ ሁሉ ነገር ይነሳል። ከተሞቻችን፣ ኢንዱስትሪዎቻችን ሁሉ እዛ ማዕከል ላይ ሆነው ማደግ ይችላሉ።

ለአብነት የሕዳሴ ግድባችንን ወስደን ብንመለከት በሕዳሴ ግድብ ሐይቅ ዙሪያ የሚመጡት ብዙ የልማት አይነቶች ናቸው። ለምሳሌ ግብጽን ለንጽጽር ብንወስድ የግብጽ ልማትና እድገት፣ የከተሞቿ አሰፋፈር ሁሉ ያለው የናይልን ወንዝ ተከትሎ ነው። ማስፋት ሲፈልጉ ደግሞ ውሃ ማከፋፈያ ይፈጥሩና በሰው ሰራሽ ቦይ ውሃውን ወደሚፈልጉበት ቦታ ያደርሱታል። ስለዚህ የመጀመሪያው የእድገት ስትራቴጂ መሆን የሚገባው ውሃን ማዕከል ያደረገ ልማት ላይ ነው።

ለዚህ ጥሩ ማሳያ የምትሆነው ሕንድ ናት፤ ሕንድ ቀደም ሲል በችግር ውስጥ የነበረች ሀገር ናት። በወቅቱ ኢትዮጵያ ለዚህች ሀገር እርዳታ አድርሳለች። ከዚህም የተነሳ በሀገራቸው በአጼ ኃይለስላሴ የተሰየመ አንድ ቤተ ክርስትያንና አንድ አዳራሽ አላቸው። በዚህ ሁኔታ ያለፈችው ሕንድ ዛሬ ላይ ተቀይራለች። ለመቀየሯ ትልቁ ምክንያት ደግሞ በልማት ስትራቴጂያቸው ላይ አንድ ባህል ያደረጉት ነገር በመኖሩ ነው። እርሱም ቀደም ብዬ የጠቀስኩልሽ አረንጓዴው አብዮት ነው። የዚህ መሪ ሃሳብ ትልቁ ማዕከሉ ደግሞ ውሃቸውን ሁሉ በቻሉት መጠን መገደብና ማጠራቀም ነው። ያጠራቀሙትን ውሃ ወደመስኖና ወደ ኃይል በመቀየር ምግብና ኢነርጂ ማምረት ነው። እኤአ ከ2000 ጀምሮ በአብዛኛው የቴክኖሎጂ ልማታቸው ያመጡበት የአይቲ ሪቮሉሽን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ እየታየ ያለው ነገር አሳሳቢ ነው፤ በተለይም ከድርቅ ጋር በተያያዘ እያጋጠመን ያለውን ችግር በዘለቄታ ለመፍታት የውሃ ሀብታችን በአግባቡ መጠቀም ወሳኝ እንደሆነ ይታመናል፤ በዚህ ዙሪያ ያለው እውነታስ እንዴት ይገለጻል?**

**ዶክተር በለጠ፡-**በእርግጥ ዝናብ ትልቁ ችግሩ ተለዋዋጭ መሆኑ ነው። ደግሞም በእኛ እጅ ላይ ያለ ጉዳይ አይደለም። ስለዚህ የእኛ አቅም እንደ ሰው የሚሆነው ዛሬ የመጣውን ውሃ እንደ ችግር አለማየት ነው። ልክ ዝናቡ ሲመጣ እንደ ችግር እያየነው ቶሎ በወጣልን ማለቱ ተገቢ አይደለም። ጎርፍን እንደ ችግር ማየት ሳይሆን ተቆጣጥሮ ለቁም ነገር ማዋል ነው።

አሁን የምናያቸው የድርቅ ችግሮቻችን መነሻው ልማቶቻችን፣ ኑሯችንና ሁለመናችን ዝናብ ላይ የተንጠለጠለ ስለሆነ ነው። ከዚህ የተነሳ ሁሌም ወደሰማይ እናንጋጥጣለን። እኛ አለን የምንለው ሀብት ዝናብ ላይ የተንጠለጠለ በመሆኑ አንዳንዴም በድርቅ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በጎርፍ እንጎዳበታለን። በሁለቱም የጥፋት በትሮች እንመታለን። መቀየር ያለብን ይህንን ነው። ይህንን ለመቀየር በዋናነት የውሃ መሰብሰብን እድገትን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራቴጂ መከተል አለብን። እሱን ይዘን ከተነሳን ሌሎቹን ሁሉ ልማቶች ማምጣት እንችላለን። ይህን ስናደርግ የምናተርፈው በርካታ ነገር አለ። ግድቡ ሲገደብ ኢንዱስትሪ፣ ቱሪዝም፣ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ሁሉ ይፈጠራል። ይህ ደግሞ የሚይዘው ሰራተኛ ብዙ ነው። ከዚህ የተነሳ የእድገት ማነቆዎች ሁሉ ይፈታሉ። ውሃን ማዕከል ያደረገ እድገት ሀገርን መለወጥ የሚያስችል ነው።

ድርቅ የሚመጣው ዝናብ ጠባቂ በመሆናችን ነው። ይህ ሲሆን ደግሞ እርዳታ ጠያቂዎች እንሆናለን። እርዳታ ደግሞ የሚመጣው ዝም ብሎ አይደለም። ሌላ የፖለቲካ ጥያቄ ይዞ ነው። እስካሁን ያለው ግብርናችን የተመሰረተው በዝናብ ላይ ነው። ይህ ካልተለወጠ አሁንም ቢሆን ከድርቅ አንወጣም። ከድርቅ የምንወጣው በዝናብ ላይ ጥገኛ የሆነ ግብርናችንን ወደ መስኖ ግብርና ማምጣት ስንችል ነው።

በቅርቡ በበጋ መስኖ ማልማት ጀምረናል። በዚህ በሁለትና ሶስት ዓመት ሒደታችን እንኳ የስንዴ ፍላጎታችንን ማሟላት እንችላለን ወደሚል ቁርጠኝነት ነው የተመጣው፤ ከዚህ ባለፈ ደግሞ ወደ ውጭ ገበያ ልንመጣ እንችላለን በሚል ርምጃው ተጀምሯል፤ ስለዚህ በቁርጠኝነት ከሰራን ውጤቱን ማየት ቀላል ነገር ነው። ትልቁ ነገር ውሃን ሰብስበን ይዘን ወደመስኖ ማምጣት ላይ ማተኮር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- መስኖዎችን በማስፋፋት የግብርናውን ዘርፍ ማሳደግ እንደ ሀገር ለጀመርነው በምግብ እህል እራስን የመቻል ስትራቴጂ አቅም እንደሆነ ይነገራል፤ ይህን ማድረግ አለመቻልም ድርቅና ድርቅ ከሚፈጥረው ፈተና ጋር አብሮ መኖርን እንደመፍቀድ ይቆጠራል የሚሉ አሉ፤ ይህን እንዴት ያዩታል?**

**ዶክተር በለጠ፡-**ይህ በጣም ትክክል ነው። የግብርና ሥርዓታችንን ወደመስኖ ልማት መቀየር እስካልቻልን ድረስ ሁሌ እየተጓዝን ያለነው ከድርቅ ጋር ስምምነት ፈጥረን ወስነን ነው። የዝናብ ግብርናን

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

መሰረት አድርገን በተለይ አሁን እያደገ የሚሄደውን ሕዝባችንን መግበን እንኖራለን ማለት አይቻልም። ይህን መቀየር የምንችለው የግብርና ስልታችንን ከዝናብ መንጠልጠል አውጥተን ወደመስኖ ስንቀይር ነው። ወደ መስኖ ካልቀየርንና አሁንም በዝናብ ግብርና ላይ የምንቆይ ከሆነ ሁሌም የድርቅ ደንበኞች እንሆናለን።

ምክንያቱም የዝናብ ትልቁ ችግር ማጠሩ ብቻ ሳይሆን የበዛ ጊዜም የሚሄደው እርሻችንን አበላሽቶት መሆኑ ነው። ዝናብ በበዛ ዓመት ጎርፉ ስለሚበዛ የእርሻ መሬታችን ይበላሻል። በበዛ ጊዜ ውሃውን መቆጣጠር ካልቻልን የሚያጠፋ ጭምር ነው። ከዛሬ 40 እና 50 ዓመት በፊት አምራች የነበሩ ቦታዎች ዛሬ በጎርፍ ተጠርገዋል። ከዚህም የተነሳ አካባቢዎቹ የሴፍትኔት ማዕከል ሆነዋል። ስለዚህ ግብርናችንን በዝናብ ላይ እንደተንተራሰ እንተወው የምንል ከሆነ የሚቀጠረው ከድርቅ ጋር ተስማምተን እንደመኖር ነው። ከድርቅ ጋር ብቻ አይደለም፤ ድርቅ እየሰፋ ሲሄድ ወደረሃብ ይቀየርና የከፋ ችግር ይፈጠራል። ከድርቅ ጋር ተስማምተን ስንኖር የሚወለደውም ትውልድ እየቀነጨረ ይመጣል። የቀነጨረ ትውልድ ደግሞ በተገቢው ልክ ማሰብ ይሳነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- የድርቁ እየሰፋ መምጣት ከሚያስከትለው የከፋ ረሃብ ጎን ለጎን እርዳታ ሰጪዎች እጅ የሚጥል ይሆናል፤ ይህ እንደ ሀገር ነጻነትን አያሳጣም?**

**ዶክተር በለጠ፡-**በሚገባ ያሳጣል። ራሳችንን በምግብና በኢነርጂ ካለመቻላችን የተነሳ ልንሆን የምንችለው ነገር ቢኖር በሁሉ ነገር ተመሪዎች መሆን ነው። ረጂ አካላት እንደፈለጉ የሚቆጣጠሩንና እንድንከተላቸው የሚያስገድዱን ይሆናሉ። ስለዚህ በተፈጥሮ የተቸርነው ሀብት ብሎም እውቀት እያለ የሚስተዋለው ግን ያለመስራት ክፍተት ነው። ስለዚህ ስትራቴጂያችንም ሆነ አመለካከታችን ጭምር መቀየር አለበት ባይ ነኝ። በቂ ዝናብ ስላለኝ እያመረትኩ እኖራለሁ ማለት ከድርቅ ጋር እኖራለሁ እንደማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የውሃ ሀብታችንን ስመጠቀም በምናደርገው ጥረት በግብጽ በኩል የሚያጋጥሙን ተግዳሮቶች ዓለም አቀፍ ይዘት እንዲኖራቸው ቀን ከለሌት ግብጽ እየሰራች ነው፤ ይህ በሀገራቱ መካከል በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ፍትሀዊ አሰራር እንዳይሰፍን እያደረገ አይደለም ?**

**ዶክተር በለጠ፡-**በግልጽ በሀገራቱ መካከል በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ፍትሀዊ አሰራር እንዳይሰፍን እያደረገ ነው። ፍትሃዊ አጠቃቀም ብቻ ሳይሆን እኛ ላለመልማታችን እንደ አመክንዮ የምንወስደው ሁሌም ግብጽን ነው። ሁሌም መሰናከል የሚሆኑት እነርሱ ናቸው። በተለይ ውሃን ለመስኖ እየተጠቀምን በሄድን ቁጥር ትልቁን ውሃ የሚያገኙት ከእኛ ነው።

የአባይ ውሃ የተፋሰሱ ሀገራት ቢሆኑም ትልቁ አስተዋጽኦ ያለው ኢትዮጵያ ዘንድ ነው። ኢትዮጵያ በሁሉም ተፋሰሶቿ እስከ 86 በመቶ ድርሻ ያላት ናት። ስለዚህ ኢትዮጵያ ይህን ውሃ ልጠቀም ብላ ከተነሳች ግብጽ ትጎዳለች። ስለዚህ በእነርሱ አተያይ ኢትዮጵያ መጠቀም የለባትም።

በእርግጥ ትክክለኛ የሚሆነው አመለካከት እንደማንኛውም የታችኛው ሀገር እኔ ብቻ ልጠቀም የሚለውን ግብጽ ትታ ፍትሃዊ የሆነ የውሃ አጠቃቀም ላይ ማተኮር ይገባታል። እንደታችኛው ሀገር ፍትሃዊ አጠቃቀም ይኑረኝ ብላ ብትነሳና ኢትዮጵያን በዚህ አግባብ ብትጠይቅ ጥሩ ነበር። እኛ እንደ ማንኛውም ማኅበረሰብ ግብጽ ያለውም ማኅብረሰብ የዚህ ምድር ሰው ነው። ስለሆነም ውሃ ያስፈልገዋል። የእነርሱ ከእኛ የሚለየው እነርሱ ከዝናብ የሚያገኙት ነገር አለመኖሩ ነው። ስለዚህ እኛ ውሃውን ባላለማን ቁጥር ከዝናብ የምናገኘው ውሃ ሁሉ የሚሄደው ወደእነርሱ ነው። እነርሱ ወደለውጥ የመጡት የአስዋንን ግድብ በመስራታቸው ነው። ግድቡ ባይኖራቸው ኖሮ በጣም ችግር ውስጥ ይወድቁ ነበር። ግብጽ ለረጅም ጊዜ በጎርፍ የምትጠቃ፣ ሰው ለመኖር የሚቸገርባት ምድር ነበረች። ይህን ሁሉ ቀይሮ የግብጽን የእድገት መርህ የፈጠረው የአስዋን ግድብ ነው። ስለዚህ የአስዋን ግድብ መጀመሪያ የታችኛው አስዋን የምንለው የድሮው ግድብ በ1904 አካባቢ የሰሩት ነው፤ የግድቡን ጥቅም ሲያዩ ደግሞ ከፍ አደረጉና መጠኑን አሳድገው ትልቁን አስዋን ግድብ ገነቡት። ቀጥለውም ውሃ ወደተለያየ ቦታ የሚያሰራጩበት፣ የሚያከፋፍሉበት እና እየቀነሱ የሚያደርሱበትንም ሰሩ። ከዚህም የተነሳ



ፎቶ ፀሐይ ንጉሤ

ሙሉ የእድገታቸው መሰረት አስዋን ሆነ። እስከቅርብ ጊዜ ድረስም የምግብም የኢነርጂም ምንጭ አድርገው እየተጠቀሙበት ነው።

ከዚያ በኋላ ግን አማራጮች እየፈለጉ ሲሆን፣ በአሁኑ ሰዓት ኢነርጂውን ወደሌላ ብዙ ነገር ቀይረውታል። አሁን ውሃው ላይ የኢነርጂ ጥገኝነታቸው በጣም ቀንሷል። ውሃውን ሙሉ ለሙሉ የምግብ አቅም መፍጠሪያ እንዲሆን ለመስኖ አውለውታል። ኢነርጃቸውን በሁለት የተለያዩ ዘርፎች ላይ አተኩረው ሄደዋል። ለምሳሌ፣ በሶላር ኃይል ማመንጨት አንዱ ትኩረታቸው ሲሆን፤ ሶላር ላይ ትላልቅ ፕሮጀክቶች እየገነቡ ነው። የባዮ ጋዝ ልማትም ሌላው የኃይል አማራጭ የትኩረት መስካቸው ነው። የአቶሚክ ኢነርጂም አላቸው። ጂኦ ተርማል እና ሌሎችም የኢነርጂው አማራጮቻቸው ሆነዋል።

በከፍተኛ መጠን ውሃውን ለመስኖ ከማዋላቸው የተነሳም፣ አሁን እያሉ ያሉት ‹‹መልሰን እየተጠቀምንም አልቻልንም›› የሚል ነው። ውሃውን እየተጠቀሙ ያለው ለመስኖ፣ ለመጠጥ እና ለኢንዱስትሪ ነው። እናም ኢነርጂውን በተወሰነ መልኩ እየተኩት መጥተዋል። መነሻቸው ግን በሱ ነበር።

ለምንድን ነው ኢነርጂውን የሚለውጡት ሲባል የመሬት አቀማመጣቸው አድካሚ ስለሆነ ነው። ይሄን ያህል ውሃ ይዘው እና ትንሽ ውሃ ይዘን የምናመነጨውን/የምናመርተውን ያህል ኢነርጂ አያመርቱም። ብዙ ጊዜ አስዋን ግድብ እና የህዳሴ ግድብን በተመለከተ በሰዎች ዘንድ የአገላለጽ ስህተት ይስተዋላል። ህዳሴ ግድብ በስትራክቸሩ/በቁመቱ ትልቅ ነው። በሚይዘው አቅም ግን ከአስዋን አይደርስበትም። ይህ ማለት ውሃን በማጠራቀም አቅም አስዋን ግድብ ይበልጠናል። የአስዋን ግድብ ውሃ የሚያጠራቅመው ከእጥፍ በላይ ነው። እስከ 160 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ ያጠራቅማል። ህዳሴን ትልቅ የሚያደርገው ግን ከአስዋን ያነሰ ውሃም ይዞ ከፍ ያለ ሃይል ማምረት መቻሉ ነው። ስለዚህ የተለወጡት ይህንን ውሃ በማጠራቀማቸው ነው።

ሁሌም እንደምንለው የአስዋን ግድብ ባይኖር ኖሮ እና ቀድሞ የተሰራው የህዳሴ ግድብ ቢሆን የህዳሴን ግድብ በጣም ወድደውት ነበር የሚኖሩት። ምክንያቱም ግድቡ ለሃይድሮ ፓወር የምናውለው እንደመሆኑ ውሃው ተጠብቆ የሚለቀቅላቸውና የሚደርሳቸው በመሆኑ ነው። ለዚህ ነው ሱዳን መሃል ላይ ያለች አገር ትልቅ አቅም የተፈጠረላት፤ በህዳሴው ግድብ የተጠበቀ ውሃ እየደረሳት ሜዳ የሆነ መሬቷን በሙሉ አቅም ወደ ማልማት የሚያስገባት ነው። ይህ ትልቅ እምርታ ነው።

ስለዚህ ግብጾች አስቀድመው የአስዋን ግድብ አጠቃላይ የውሃውን ፍሰት መጠቀም የሚያስችል አቅም ስለፈጠሩ ይህ አቅም እንዳይስተጓጎልባቸው ይፈልጋሉ። እንዳይስተጓጎልባቸው ምንድን ነው ፍላጎታቸው ቢባል ደግሞ ኢትዮጵያን ከውሃ ልማት ውጪ ማድረግ ነው። በየትኛውም መንገድ፣ በየትኛውም ፖለቲካ ጫና ውስጥም መክተት ነው። ስለዚህ ዓለምአቀፍ ጫናዎችን ይፈጥራሉ፤ ዓለምአቀፍ ተቋሞችን ይጠቀማሉ፤ ጉዳዩን የፖለቲካ ጨዋታ ያደርጋሉ። ሚዲያዎቻቸው ላይ አጠንክረው ይሰራሉ። ሕዝባቸው ላይ ከፍ ያለ የሥነ ልቦና ጫና በመፍጠር አመለካከታቸው እንዲቀየር ያደርጋሉ። በተለይም ‹‹ኢትዮጵያ የምትባል አገር የእኛ ትልቅ እንቅፋት ናት፤ የውሃችን ማነቆ ናት፣ ውሃችንን ልታስቀርብን ነው፤ እኛ ደግሞ ለዚህ ለናይል ውሃ ነው የተፈጠርነው፤ ያለ ናይል እኛ የለንም፤ ይህንን እየቀማችን ያለችው ኢትዮጵያ ናት።›› በሚል ለሕዝባቸው ያልተገባ ትርክት ይናገራሉ። ከዚህም የተነሳ ዝመት ቢባል የግብጽ ሕዝብ በሙሉ አቅሙ ይዘምታል። ዘምቶ ያዋጣዋል አያዋጣውም የሚለው ሌላ ችግር ይሆናል እንጂ። ምክንያቱም የግብጽ ልሂቃኑ አዕምሮው ላይ ሁሉን ነገር ፈጥረውበታል።

ወደዓለምአቀፉ ማኅበረሰብም ስንሄድ ግብጻውያኑ የሚያደርጉት እንደዛው ነው። ከሌሎቹ ሃያላን ሀገራት ጋር ያላቸውን ፖለቲካ የሚሰሩት በናይል ውሃ ላይ ነው። እናንተ ናይል ውሃ ላይ እንደዚህ አግዙን እኛ ለእናንተ እንደዚህ እናደርግላችኋለን የሚል ነው። የሁሌም የዲፕሎማሲያቸው ምንጭ ይህ ነው። ባላቸው እና በገቡበት ቦታ ሁሉ የሚጠይቁት ያ ተቋም የናይል ውሃ አጠቃቀም ላይ በተለይም ኢትዮጵያ ላይ ተጽዕኖ እንዲፈጥርላቸው ነው። ጥማታቸው ኢትዮጵያ በተለይ የዓባይን ውሃ እንዳትጠቀም ማድረግ ላይ ነው።

አስቀድሜ እንደጠቀስኩት ውሃ ወደ ናይል ከሚገቡ ወንዞች መካከል ትልቁ የዓባይ ውሃ ነው። እዛ ዓባይ ላይ የሚሰራ ነገር በእነሱ ፖለቲካ ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል። አሁን በታሪክ የሚታወቅ ነገር አለ። የአስዋንን ግድብ ሲሰሩ የረዳቻቸው ራሽያ ነበረች። ልክ ያንን ርዳታ ሲያዩ ነው አሜሪካኖቹ መጥተው ኢትዮጵያን እነዚህ ትንንሽ ግድቦች የምንላቸውን ጥናቶች የመጀመሪያውን ጥናት ያጠኑት። አሜሪካ ያንን ያደረገችው ግብጽ የፖለቲካ ለውጥ አደረገችብን በሚል እሳቤ ሲሆን፣ ግብጾችን ለመቆጣጠር ፈልጋ ነው። ልክ አሜሪካኖቹ ይህን ጥናት ማጥናታቸውን ሲያዩ ግብጾቹ ቶሎ ነው አቅጣጫቸውን የቀየሩት። ያን ያህል ግድብ እንኳን እየገደበችላቸው ከራሺያ ጋር ለመቆየት አልወሰኑም። ምክንያቱም አሜሪካ ጥናቱን ጀምራ ጥናቱን ወደ ግድብነት የምትለውጠው ከሆነ ፖለቲካው ከባድ ይሆናል። እናም የተውት ጥናቱን ካጠኑ በኋላ ነው።

ጥናቱን አፄ ኃይለስላሴ የጠየቁት ገና እንግሊዞቹ ሙሉ ለሙሉ ከግብጽ እና ከሱዳን ለቅቀው ሳይወጡ በነበረ ጊዜ ሁሉ ነው። የዚያን ጊዜ በፖለቲካው ዙሪያ ጤናማ ስለነበሩ ግን አልመጡላቸውም ነበር። ልክ ግብጽ የፖለቲካ አቅጣጫዋ ወደ ሶሻሊስቱ ካምፕ ተቀየረብን ብለው ሲያስቡ ግን ቶሎ መጥተው ለኢትዮጵያ ጥናት ማጥናት ጀመሩ። ልክ ይህን ጥናት ማጥናታቸውን ሲጀምሩ ግብጾቹ ደግሞ ተሰበሰቡና ‹‹አደጋ ውስጥ ነን፤ ስለዚህ እንመለስ›› ብለው እንደገና የፖለቲካ አቅጣጫቸውን ማስተካከል ጀመሩ።

አሁን ባለንበት ነባራዊ ሁኔታ አሁንም ትልቁን የዓለምን ፖለቲካ የሚዘውሩበት ነው። ከአረብ ሊግ ጋርም አረቦች ከኢትዮጵያ ጋር ህብረት እንዳይኖራቸው ለማድረግ የሚሰሩት ለዚሁ ለናይል ውሃ ሲሉ ነው። ስለዚህ የትኛውም የውሃ ልማት ተግዳሮታችን የሚነሳው ከግብጽ ጋር ነው። ግብጽም ይህን ስላሰበች ፍትሃዊ እና ርትዕ የሆነው አጠቃቀም እኔን ይጎዳኛል፤ እኔ አስቀድሜ ስለለማሁ፣ አብዛኛውንም ውሃ እኔ ስለተቆጣጠርኩት እንደተቆጣጠርኩት ልኑር ብላ ስለምታስብ ነው እንጂ እንዲያውም በመሰረተ ሃሳቡ ቢታይ አሁን ኢትዮጵያ እየጠየቀች ያለችው መሰረታዊው ሐሳብ ይህ ፍትሃዊና ምክንያታዊ አጠቃቀም የሚጠቅመው የታችኞቹን ሀገሮች ነው። የላይኞቹን ሀገሮች ማሰሪያ ነው።

ስለዚህ እኛንም የተሻለ የሚያደርገው ግብጾች አመለካከታቸውን አስተካክለው ቢጠይቁ ነበር ። ከዚህ ውጭ መንገዳቸው ፍትሃዊና ርትእ አካሄድን አይፈጥርም። ምክንያቱም አስዋን ግድብ አላቸው፤ እስካሁን ባለው ፍሰት አብዛኛውን (ሙሉውን ማለትም ይቻላል፣ የተወሰነ ያህል መቶኛ በሱዳን ጥቅም ላይ ከመዋሉ ውጪ) የውሃውን ፍሰት እነሱ መጠቀም የሚችሉበት እድል ነው የፈጠሩት።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ ግብጽ፣ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ጉዳይን የአረብ ሊግ ምክር ቤት ቋሚ አጀንዳ እንዲሆን ጥሪ አቅርባለች፤ ይህ ያልተገባ ጣልቃ ገብነት አይሆንም?**

**ዶክተር በለጠ፡-** የአረብ ሊግ ጉዳይ ያልተገባ ጣልቃ ገብነት ነው። ምክንያቱም ጣልቃ እየገቡ ያሉት ባልተገባቸው ጉዳይ ላይ ነውና። የአረብ ሊግ የሕዳሴ ግድብን አጀንዳ ለማድረግ የሚያስችል ምንም ምክንያት የለውም። ራሳቸው ሱዳኖች ጉዳዩ የአረብ ሊግ አጀንዳ እንዲሆን አይፈልጉትም። ግብጾች ግን የትኛውም ዓለም አቀፍ ተቋም ሕዳሴን አጀንዳው እንዲያደርግላቸው ይሻሉ።

አብዛኛውን ጊዜ ደግሞ እንደሚታወቀው የአረብ ሊግ በግብጾች ተጽዕኖ ውስጥ ያለ ነው። ወደኋላ መልስ ብለን ከታሪክ ማህደር ማየት ብንችል አብዛኛዎቹ የአረብ ሊግ ምክር ቤት ቋሚ ጸሐፊዎች ዋና ሆነው ሲሰሩ የቆዩት ግብጻውያን ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ግብጾች የሕዳሴ ግድቡን በአረብ ሊግ ቋሚ አጀንዳ ማድረጋቸው በሕዳሴ ግድቡ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ይኖራል?**

**ዶክተር በለጠ፡-** የተለየ ተጽዕኖ አያመጣም። የእነርሱ ፍላጎት የፖለቲካ መልክ እንዲይዝ ነው። የውሃ ሳይንስ መሆኑ ቀርቶ የፖለቲካ መጠቀሚያ ይሆናል። እሱ ሲሆን ደግሞ ለሌላ መጠቀሚያ ለማዋል ይረዳቸዋል። እኛ ደግሞ ከአረብ ሀገራት ጋር በብዙ መልኩ ትብብር አለን። አብረን የምናከናውናቸው የልማት አጀንዳዎች አሉ። ብዙዎቹ ዜጎቻችን አረብ ሀገራት ሔደው ስራ ይሰራሉ። ይህ ስለሆነ ግብጾች ቋሚ አጀንዳ እንዲሆን ማድረጋቸው አረብ ሀገራት የኢትዮጵያ ጉዳይን ሲመለከቱ በአንዳንድ ትብብሮቻችን ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ ያስችላቸው ዘንድ እንደመነሻ ሊጠቀሙበት ይችሉ ይሆናል።


በነገራችን ላይ ግብጾች የሕዳሴ ግድቡን ጉዳይ የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ቢሮ ድረስ ወስደው ነበር፣ ኢትዮጵያ በሰጠችው ተገቢ መልስ ግን

ወደ 15ኛው ገጽ ዞሯል

# ማህደረ ጤና

# አሁን አየ ዓይኔ!






**እፀገነት አክሊሉ**

“አሁን ላያችሁ እችላለሁ ፤ አንድ ሕይወታቸው ያለፈ ሰው የዓይን ብሌናቸውን ለግሰውኛልና ”፤ ይላል የኢትዮጵያ አይን ባንክ በራፍ ላይ የተለጠፈው ስቲከር።“ብርሃን ይስጡ ብርሃን አይቅበሩ” በማለት ባንኩ ከበጎ ፈቃደኞች የአይን ብሌን ልገሳን ከጀመረ ዓመታትን አስቆጥሯል። በጎ ፈቃደኛ ኢትዮጵያውያንም ከሞቱ በኋላ የአይን ብሌናቸው ለሌላው ይጠቅም ዘንድ እየተናዘዙ ብዙዎችን ባለ ብርሃን ስለማድረጋቸው መረጃዎች ያሳያሉ።

በበርካታ የትወና ስራዎቹ የምናውቀው የምንወደውና የምናደንቀው ወጣቱ አርቲስ ታሪኩ ብርሃኑ (ባባ ) ብዙዎቻችን ያላደረግነውን ወይም ችላ ያልነው ከሞትን በኋላ የዓይን ብሌኑን ለመለገስ ቃል በገባው መሰረት የዓይን ብሌኑን ለግሷል። የህክምና ባለሙያዎች የዓይን ብሌኑ በክብር ተቀብለውም ለሌላ ብርሃን ላጣ ሰው ብርሃን ሰጥተውበታል።

ሲስተር ሜላት አንዳርጋቸው በኢትዮጵያ ዓይን ባንክ ውስጥ የምትሰራ ባለሙያ ናት ፤ የአይን ብሌን ንቅለ ተከላ እንደሌሎቹ ለምሳሌ እንደ ኩላሊት ንቅለ ተከላ የቅርብ ቤተሰብ ወይም በደም የመመሳሰል ነገርን የሚጠይቅ አይደለም፤ ይህ የሆነው ደግሞ ዓይን ከደም ጋር የተያያዘ ንክኪ ያለው አለመሆኑና የመጠንም ችግር ባለመኖሩ የአንዱ ለአንዱ ስለሚሆን ነው። ዋናው ነገር የሴሎቹ መጠን ከ 1 ሺ 5 መቶ በላይ መሆናቸው ብቻ ነው የሚፈለገው ትላለች።

ሲስተር ሜላት አንድ ሰው የዓይን ብሌኑን ለወገኖቹ ሲናዘዝ የምንሰጠው መታወቂያ አለ። ይህንን መታወቂያ ደግሞ ለቤተሰቦቹ ማሳየት ቃል መግባቱንም ማሳወቅ ለስራችን ምቹ ሁኔታን ይፈጥርልናል። ሰዎች የዓይን ብሌናችሁን ቃል ግቡ ሲባሉ ይፈራሉ ለዚህ ደግሞ ዋናው ምክንያት የዓይን ብሌኑ ሲወሰድ የገጽታ መበላሸት እንዲሁም የአስከሬን መጉላላት የሚያጋጥም ስለሚመስላቸው ነው። ግን ይሄ ፍጹም የተሳሳተ አረዳድ ነው ብላለች።

አንድ ሰው ሕይወቱ ካለፈ በኋላ የዓይን ብሌኑ የሚወሰደው በስምንት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ነው። ይህም የሚከናወነው አስከሬኑ ባለበት ቦታ ሆስፒታል አልያም መኖሪያ ቤት ድረስ የባንኩ ባለሙያዎች በመሄድ የሚያከናውኑት ተግባር ነው። የዓይን ብሌኑ ከተወሰደ በኋላም በግለሰቡ ስም ሳይሆን በሚሰጠው መለያ ቁጥር (ኮድ) ነው የሚታወቀው። ከዚያም የሞተበት ቀን ሰዓት ይመዘገባል። ግለሰቡ የሚታይበት የተለየ የአካል ጉዳት ምን አለ የሚለውን የሰውነት ዳሰሳ ይሰራል። ጉዳት ካለም ይመዘገባል። በምንድን ነው የሞተው? እድሜው ስንት ነው? ጾታው ? እነዚህ ሁሉ ተለይተው ይመዘገባሉ።

አንድ የዓይን ብሌን ከሞተ ሰው ላይ መነሳት ያለበት እስከ ስምንት ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው የምትለው ሲስተር ሜላት ስምንት ሰዓት ያለፈው አስከሬን የአይን ብሌኑ መነሳት አይችልም። ቢነሳም ሴሎቹ ስለሚሞቱ አገልግሎት አይሰጥም።

ሲስተር ሜላት እንደምትለው አሁን ላይ በህብረተሰቡ ዘንድ ያለው ግንዛቤ ያን ያህል ያደገ ነው ባይባልም መሻሻሎች ግን አሉ። ሰዎች በአካል ወደባንኩ መጥተው ቃል ይገባሉ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በጥቁር አንበሳ ፣ ጳውሎስና ራስ ደስታ ሆስፒታሎች ላይ የአይን ብሌን ልገሳ አማካሪዎች ስላሉ በሆስፒታሎች ውስጥ ቤተሰብን እያስታመሙ ሞት ቢከሰት የዓይን ብሌናቸውን ለባንኩ እንዲለግሱ ያማክራሉ ፤ እነሱ የሚሰጡትን ትምህርት ተገንዝቦ ቤተሰቡ የአይን ብሌኑን መውሰድ ትችላላችሁ ካለ ይወስዳል፤ ሌላው ደግሞ ቃል የገቡም ይሁኑ ያልገቡ ሰዎች በመኖሪያ ቤታቸው ሞት ሲያጋጥማቸው ቤተሰቦቻቸው ደውለው የዓይን ብሌን ውሰዱ ካሉም ባንኩ በፍጥነት ያሉበት ቦታ ድረስ በመሄድ ብሌኑን ይረከባል በማለት ታብራራለች።

የዓይን ባንኩ ቴክኒካል ስራ አስኪያጅ ሲስተር ሊያ ትካቦ እንዳሉትም ባንኩ ህብረተሰቡ የዓይን ብሌን ልገሳ ምንድነው የሚለውን እንዲያውቅ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ይሰራል፤ ሰዎች በራሳቸው ተነሳሽነት የአይን ብሌናቸውን ለመስጠት ቃል የሚገቡትን ያህል ከቅርብ ቤተሰባቸው አንዱ ህልፈት ሲገጥመው ደግሞ ወደባንኩ ደውለው ብሌን ውሰዱ ይሉናል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ አስከሬኑ ባለበት ቦታ ድረስ በመሄድ የዓይን ብሌኑን እናነሳለን ይላሉ።

ህብረተሰቡ ሊያውቀው የሚገባው ነገር የአይን ብሌን ከሞቱ ሰዎች ላይ ስናነሳ ሙሉ አይናቸውን አንወስድም፤ ይልቁንም የዓይናቸውን ጥቁሩን ክፍል ከሱም ላይ ስሷን ቦታ ብቻ ነው። በዚህ ሁኔታ ደግሞ የሰዎች የፊት ገጽታ ሳይበላሽ አስከሬን ሳይጉላላ የቀብር ሰዓት ሳይዛባ የሚሰራ ስራ ነው የሚሉት ሲስተር ሊያ ሌላው ባንኩ ሆስፒታሎችን መሰረት ያደረገ የዓይን ብሌን የማሰባሰብ ስራንም ይሰራል። ይህም የሚሆነው በየሆስፒታሉ ባስቀመጥናቸው የልገሳ አማካሪዎች አማካይነት ሞት በሚከሰትበት ጊዜ አማካሪዎቹ የሟችን ቤተሰቦች በማናገር ፍቃደኝነታቸውን በመጠየቅ የዓይን ብሌኑን የመውሰድ ስራ ይሰራል።

የኢትዮጵያ የዓይን ባንክ እኤአ በ 2003 የተመሰረተ ሲሆን ከዛ ጊዜ ጀምሮም የተለያዩ ስራዎችን ቢሰራም እስከ አሁን ድረስ ማህበረሰቡ ዘንድ ግንዛቤ መፍጠር አልቻለም የሚሉት ሲስተር ሊያ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ራሱን ችሎ ህልውናውን አስጠብቆ መቀጠል የማይችልበት ከባድ የገንዘብ እጥረት ያለበት ተቋም ስለነበረ ነው።

ለባንኩ የሚመደቡት ባለሙያዎችም ቢሆኑ ከተለያዩ ሆስፒታሎች በምደባ የሚመጡና ደመወዛቸውንም የሚከፍሏቸው ይሰሩባቸው የነበሩ ተቋማት ነበሩ፤ ሥልጠናዎችን የሚሰጡልን ደግሞ እንደ ኦርቢስ ኢንተርናሽናል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ሳይት ላይፍ የሚባሉ ድርጅቶች ናቸው። ነገር ግን ባንኩ ከመንግሥት ቀጥታ በጀት ተመድቦለት የሚሰራ ስላልነበር ህብረተሰቡ ጋር መድረስ ሳይችል መቆየቱን ያብራራሉ።

ጤና ሚኒስቴር የባንኩን አስፈላጊነት ያሉበትንም ውስንነቶች በመረዳቱ አሁን ላይ ወደመንግሥት አሰራር እንዲገባ በአዋጅ ደም ባንክ፣ የኩላሊት ንቅለ ተከላና ዓይን ባንክ ተደምረው የኢትዮጵያ ደምና ቲሹ አገልግሎት ተብለው እንዲቋቋሙ ሆኗል ፤ በዚህም በአሁኑ ዓመት በጀት ተመድቦለታል። ከዚህ በኋላም ባንኩ አብረውት ካሉ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ሰፊ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በመስራት ህብረተሰቡ ላይ ለውጥ ያመጣል እንደ ሲስተር ሊያ ገለጻ።

ባንኩ 20 ዓመታትን በስራ ላይ የቆየ ቢሆንም ከላይ በጠቀስኳቸው ምክንያቶች በሚፈለገው ልክ ህብረተሰቡ ጋር መድረስ ባይችልም በተቻለ መጠን ግን ወጪ የማይጠይቁ ቦታዎች ላይ በመሄድ የማስተማር ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል፤ አሁን ግን በጀትም ስላለው እቅድ አውጥቶ ህብረተሰቡ ዘንድ በመድረስ ላቅ ያለ ግንዛቤ ይፈጥራል ይላሉ።

በአገራችን በዘርፉ የተከናወኑ ጥናቶች ሰፊ ባይሆኑም እኤአ በ 2005 በተጠና ጥናት ከ 3 መቶ ሺ በላይ ሁለቱም የዓይን ብሌናቸው ጠባሳ ያለበት ዜጎች ይኖራሉ። አሁን ላይ ይህ ቁጥር የት ሊደርስ እንደሚችል መገመት ቀላል ነው። እነዚህ ሰዎች ሁሉም የዓይን ብሌን ንቅለ ተከላ ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን ባንኩ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ አገልግሎት የሰጣቸው ሰዎች ቁጥር 2 ሺ 957 ብቻ ናቸው።

ሲስተር ሊያ እንደሚሉት በስራው ላይ ሌላው ፈታኝ ችግር የዓይን ብሌን ንቅለ ተከላ ሀኪሞች ቁጥር ውስን መሆን ነው፤ አሁን ላይ በዚህ የሙያ መስክ ስፔሻላይዝድ ያደረጉት ሀኪሞች ቁጥር 10 ብቻ ናቸው፤ እነዚህም በጎንደር፣ አዋሳ፣ መቀሌ፣ ጅማ ፣ አርባ ምንጭ ና ከአዲስ አበባ ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ ፣ ዳግማዊ ምኒልክና በተወሰኑ የግል የዓይን ህክምና መስጫዎች ተቋማት ላይ የሚሰሩ ናቸው። በመሆኑም የዓይን ብሌን ብዙ ቢሰበሰብ እንኳን በዘርፉ ስፔሻላይዝድ ያደረጉት ሃኪሞች በበቂ ሁኔታ የማይገኙ ከሆነ ችግሩ እዛው መመለሱ ስለማይቀር የዓይን ብሌን ከማሰባሰቡ ጎን ለጎን የሀኪሞችን መጠን የመጨመሩ ስራም ሊሰራ እንደሚገባው አብራርተዋል።

እንደ ሲስተር ሊያ እምነት ጤና ሚኒስቴር የዓይን ሀኪም የሆኑ ባለሙያዎችን በዓይን ብሌን ንቅለ ተከላ ህክምና አሰልጥኖ በገጠርም በከተማም እንዲመደቡ በማድረግ እገዛውን ሊያሳይ ይገባል። ምክንያቱም በአገራችን ይህንን አይነቱን አገልግሎት ማስፋት ካልቻልን ገንዘብ ያላቸው ሰዎች ይህንን አገልግሎት ለማግኘት ወደተለያዩ የዓለም አገራት በሚሄዱበት ጊዜ ይዘውት የሚሄዱት የውጭ ምንዛሪ አገር ላይም የሚያደርሰው ጉዳት ቀላል አይደለም በመሆኑም ባንኩ ትልቅ አገራዊ ችግርን የሚቀርፍ መሆኑ ታምኖ ማንኛውም የመንግሥት አካል ድጋፉን ሊያደርግ እንደሚገባውም አብራርተዋል።

አሁን ላይ ጎንደር ሆስፒታል ፣ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል፣ አርባ ምንጭ፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ፣ አዲስ አበባ ቅዱስ ጳውሎስ፣ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታሎች የዓይን ብሌን ንቅለ ተከላ የሚሰሩ ሲሆን የግሎቹም ላይ በተመሳሳይ አገልግሎቱ ይሰጣል። እዚህ ላይ ግን ልብ ሊባል የሚገባው በተለይም በግል ሆስፒታሎች ላይ የዓይን ብሌን ንቅለ ተከላው የሚሰራው በመንግሥት ሆስፒታሎች ላይ በበቂ ሁኔታ ማቅረብ ተችሎ ትርፍ በሚኖርበት ጊዜ ነው።

"የዓይን ብሌን ማስቀመጫዎቹ እንኳን በውጭ ምንዛሪ በውድ ዋጋ ተገዝተው የሚገቡ ናቸው፤ ከዚህ ቀደም የዓይን ባንኩ በቦርድ የሚተዳደር የራሱ የሆነ የገቢ ምንጭም የሌለው ነበር፤ ለጋሾች ደግሞ የዓይን ብሌናቸውን በነጻ ነው ለባንኩ የሚሰጡት ነገር ግን ባንኩ ብሌኑን ከተረከበ በኋላ ለንቅለ ተከላው ለማዘጋጀት የሚታለፍበት ሂደት በትንሹ 25 ሺ ብር ይፈጃል፤ በመሆኑም የዓይን ብሌኑን የሚፈልጉ የመንግሥት ሆስፒታሎች በ 3ሺ 863 ብር የግሎች ላይ ደግሞ 6 ሺ 999ብር የወጪ መጋራት አድርገው እንዲወስዱ ይሆናል ፤ ነገር ግን በተለይም በመንግሥት ሆስፒታሎች ላይ ታካሚው ምንም የገቢ ምንጭ የሌለውና መክፈል የማይችል መሆኑ ከተረጋገጠ በነጻ እንልካለን፤ " ይላሉ።


የዓይን ባንኩን በተለያየ መንገድ የሚያግዙ ግለሰቦችና ተቋማት አሉ የሚሉት ሲስተር ሊያ ከዚህም መካከል የኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ የልገሳ ሳጥኖች በማስቀመጥ ሰዎች የሚችሉትን እንዲሰጡ ይደረጋል፤ ባንኮች የስራው ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ በዓመት የተወሰነ ገንዘብ ይሰጣሉ ፤ለምሳሌ አዋሽ ባንክ 24 ሰዓት የሚሰራ 4 መቶ ሺ ብር የሚያወጣ ጀነሬተር በመግዛት ድጋፍ አደርጓል። ኢትዮ ቴሌ ኮም ፣ ኦርቢስ ኢንተርናሽናልና ሌሎችም በዓመት የተወሰነ ድጋፋቸውን ያደርጋሉ።

የንቅለ ተከላ ተቋማቱ ላይ ተመዝግበው ወረፋ በመጠበቅ ላይ ያሉ በርካታ የአይን ጠባሳ ያለባቸው ሰዎች አሉ፤ እኛ ደግሞ ለእነዚህ አካላት ተደራሽ ለመሆን የአይን ብሌን ለመሰብሰብ ለጋሾች መኖር አለባቸው፤ እነሱ እንዲኖሩ ደግሞ ማህበረሰቡ ስለ ዓይን ብሌን ንቅለ ተከላ በቂ እውቀት ያስፈልገዋል። በመሆኑም ሰዎች ግንዛቤያቸው አድጎ የዓይን ብሌናቸውን ለመለገስ ቃል መግባት መቻል አለባቸው። በመሆኑም ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋቸዋል እንደ ሲስተር ሊያ ገለጻ።

"...ማን መቼ ዓይነ ስውር እንደሚሆን አይታወቅም በመሆኑም የወገኖቻችን ችግር የእኛም ነው ፤ያገባናል ይመለከተናል፤ ብለን መነሳት አለብን ዓይን ባንኩንም ማገዝ ያስፈልጋል፤ ግንዛቤው ያለንም ሰዎች ቀና በመሆን ሰዎች ሲሞቱብን ደውለን የዓይን ብሌን ውሰዱ ማለትን መልመድና ለወገኖቻችን ብርሃን መሆን ያስፈልጋል" እንደ ሲስተር ሊያ ገለጻ።

ማንኛውም ሰው ለወገኔ የዓይን ብርሃኔን ከሞት በኋላ እሰጣለሁ ብሎ ወደተቋማችን እየመጣ እንደሰለጠነ ሰው ቃል መግባት አለበት። "እኔ ለወገኔ ብርሃኔን ሰጥቻለሁ" ማለት በራሱ በጎ አመለካከት ነው። ይህንን ቃል ገባን ማለት ደግሞ እንሞታለን ማለት አይደለም። ሰው በሕይወቱ እያለ ለሌሎች መዳን ደም ይለግሳል ፤ከሞተ በኋላ ደግሞ የዓይን ብሌኑን ቢለግስ ለወገኑ ትልቅ ስራ ሰርቶ ማለፍ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)

gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# የሽግግር ፍትሕ - «ባይተዋሩ ቤተኛ»

**መተከዣ፤**

ይህ አምደኛ ምስኪኗንና አይተኬ አገሩን ሁሌም የሚመስላት በትራዡዲ ታሪኮችና ድርሰቶች ምንጭነት ነው። አገላለጹ «ሀሰት!» ተብሎ የመከራከሪያ አጀንዳ ይከፈትለት የማይባል እውነታ ስለመሆኑም ማስተባበል አይቻልም። ማሳያዎቹ ደግሞ ባለፉት ረጂም ዓመታት በዚሁ አንጋፋ ጋዜጣ ላይ ጥቂት በጥቂት ከመራር አገራዊ አሳሮቻችን ውስጥ እየቆነጠርን ስንቆዝምባቸው የከረምንባቸውን ርዕሰ ጉዳዮች ማስታወሱ ብቻ በቂና ከበቂ በላይ ስለሆነ በማስረጃነት ለመጥቀስ አይገድም።

ጸሐፊው በሕይወት ዘመኑ ስሜቱ እጅግ ተጎድቶ ካነበባቸው የግል ገጠመኞቹ መካከል ሁለቱ መሪር ኀዘኖች ከቶም በቀላሉ የሚረሱ አይመስሉም። አንዱ የሩቅ ሌላኛው የቅርብ ጊዜ ሊባሉ የሚችሉ ገጠመኞች ናቸው። ሕወሓት/ኢህአዴግ አዲስ አበባን በተቆጣጠረበት ዕለት ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም በሸጎሌ የጦር መሣሪያ ማከማቻ መጋዘን (ዴፖ) ላይ በተፈጠረው ፍንዳታ ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ዜጎች በሚዘገንን አሟሟት አካላቸው እንደ ጨርቅ ተበታትኖ ያለቁትንና ለማይሽር አካላዊ ጉዳት ሰለባ የሆኑትን ወገኖች ሲያስታውስ እምባው ከከረጢቱ እስኪሟጠጥ ድረስ ቢያነባም መሪሩ ኀዘን ከውስጡ ታጥቦ ሊወጣለት አልቻለም።

መኖሪያ ቤቱ ከፍንዳታው ቦታ በመቶ ሜትሮች ርቀት ላይ ይገኝ ስለነበር ትራጄዲው በተፈጸመበት ቦታ ቀድሞ በመገኘት የዐይን እማኝ መሆኑ ይበልጥ ኀዘኑ እንዳይረሳ ምክንያት ሆኗል። የፍንጥርጣሪው ዳፋም ደጃፉ ድረስ ደርሶ ስለነበር ለአስከፊነቱ ተቀዳሚ ምስክር ነው። በሣምንቱ ግንቦት 27 ቀን በበቅሎ ቤት የጦር መሣሪያ ግምጃ ቤት ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ በተፈጠረው አደጋ መከራው ወድቆባቸው ቤተሰቦቻቸውንና ወዳጆቻቸውን ያጡ ወገኖችን ለማጽናናት የተቻለው ከተሰበረው ልባችን ውስጥ የሚንጠባጠበው ደም ቁለቁል ወደ ውስጣችን እየፈሰሰ ነበር እንጂ እምባችንማ ተሟጦ አልቆ የጠብታ ያህል እንኳን እያዋጣን ልናስተዛዝናቸው ከቶውንም አልቻልንም። «እንዳያልፉት የለም» እንዲሉ እነዚያ ክፉ ቀናት ትተውብን ያለፉት ቁስሎች ዛሬም ሆነ ወደፊት ማመርቀዛቸው በቀላሉ ፈጥኖ የሚጠግግ አይመስልም።

የአጋጣሚ ጉዳይ ይሁን ወይንም ከሰው ልጆች መረዳት አቅም በላይ በሆነ የግጥምጥሞሽ ምሥጢር ብቻ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን አዲሱ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኢቲቪ) አዲሱ የሕንፃ ኮምፕሌክስ የተገነባው በፍንዳታው በወደመው የቀድሞ የሸጎሌ ዴፖ ላይ ነው። ተቋሙ ያንን መራር የታሪካችንን ጥቁር ምዕራፍ በአግባቡ የሚያስታውስ አንድ ቋሚ መዘክር ወይንም መታሰቢያ በግቢው ውስጥ ቢያቆም አንድም የሙያ ሥነምግባሩ ግድ ይለዋል፤ አንድም የአካባቢው ወራሽ ከመሆኑ አኳያ በእምባ አባሽነት ክሬዲቱ ሊያዝለት ይችል ይመስለናል።

የሁለተኛው መራራ ኀዘን ምክንያት በቅርቡ በሚባል ሰሞን ለመዲናችን አዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ላይ በሚገኘው በደብረ ብርሃን አካባቢ በሚገኝ መጠለያ ጣቢያ ተፈጽሞ የተሰማው ታሪክ ነው። በዚያ ጊዜያዊ ማረፊያ ውስጥ የተጠለለው ወገን በጦርነት ተሰዶ፤ በሸማቂዎች ከአካባቢው ተፈናቅሎና ኑሮ የአቀበት ያህል ከብዶት ከቀዬው ተነቅሎ የተከማቸ የምንዱባን ስብስብ ነው።

በዚያ መጠለያ ጣቢያ ውስጥ አንድ አባት ገና ጥርሱን ነቅሎ ካልጨረሰ ታዳጊ ልጃቸው ጋር ፈንጠር ብለው ተቀምጠው ይወያያሉ። ልጅ አባቱን ይጠይቃል፡-

«አባባ ለምን ወደ አገራችን አንመለስም?»፤

አባት፡- «ልጄ ምን አገር አለንና ወዴት እንመለሳለን»፤

«እንዴት አገር የለንም አባባ?»፤

«አገር አልባ እንድንሆን ተፈርዶብን»፤

«ማነው የፈረደብን አባባ?»፤

«እግዜሩና ጉልበተኞች»፤

«ታዲያ ሁልጊዜ እዚሁ ነው የምንኖረው?»፤

«አይ ልጄ ከዚህ ቦታም ልንሰደድ እንችላለን»፤

«ለመንግሥት ለምን አንነግርም?»፤

«አገር ቢኖረንም አይደል መንግሥትን የምንጠይቀው፤ አገር አልባ እኮ ነን ልጄ። በቅርቡ ከዚህም ተነሱ ተብለን ልንባረር እንችላለን»፤

«ደግሞ ወዴት?»፤

«እግር ወዳደረሰን»፤

«እናስ አባባ መጨረሻችን ምንድን ነው?»፤

«መሰናበት! ለዚያውም መቀበሪያ ካገኘን።»

ያ ሕፃን ልጅ ምርር ብሎ ለምን ያለቅስ እንደነበር ለመጠየቅ ወደ አባትዬው ጠጋ ሲባል ነበር ይህንን ልብ ሰባሪ ታሪክ ማድመጥ የተቻለው። የልጁ እምባ ለጊዜውም ቆሞ ሊሆን ይቻላል፤ አባትዬውም ከልጁ ጋር ያደረገውን ያንን ውይይት ሁለቱም ምንዱባን ሊዘነጉት ይችሉ ይሆናል። እኔና ይህንን ታሪክ ያደመጡ ወዳጆቼ ግን ታሪኩ ትዝ ባለን ቁጥር እስከ ዕለተ ፍጻሜያችን ድረስ እምባችን ከዐይናችን ላይ መመንጨቱ የሚቆም አይመስለንም።

ኢትዮጵያ ሆይ! እንደነዚያ አባትና ልጅ በአገሩ አገር አልባ ያደረግሽውን «የምስለ ዜጋሽን» ቁጥር በእውነቱ ታውቂው ይሆን? የገመናሽ ጉድ እንኳን የሩቅ ባዕዳንን ቀርቶ እኛን ዜጎችና ራስሽንም ቢሆን ሀፍረት የሚያከናንብ ስለሆነ ድምጻችንን አስተባብረን «ኤሎሄ! ኤሎሄ! ላማሰበቅታኒ!» እያልን በጋራ ልንቃትት ይገባል። የሃይማኖት መምህራኖቻችን «ከመጥምቁ ዮሐንስ» ሕይወት እንዳስተማሩንም «የፍትሕ ያለህ!» እያልን በምድረ በዳ ልንጮኽ ይገባል። በጽንስ ደረጃ ላይ የሚገኘው የሽግግር ፍትሕ እንቅስቃሴም በይሉኝታ ሳይሸኮረመም በእኛ መልክና አምሳል ተቀርጾ ወደ ትግበራ እንዲገባና ችግሮቻችን ላያዳግሙ ፍርጥርጥ ተደርገው እንዲፈቱ ከወዲሁ የአደራ ቃላችንን ለሚመለከተው ሁሉ ይድረስልን እንላለን።

**ባጉራህ ጠናኝ መረታታችን ይብቃ፤**

በአየራችን ላይ እየናኙ ካሉት የሰሞኑ አገራዊ የመወያያ አጀንዳዎች መካከል አንዱ የሽግግር ፍትሕ (Transitional Justice) የሚባለው በቀዳሚነት ይጠቀሳል። ስለ ጽንሰ ሃሳቡ፤ ስለ አካሄዱና አተገባበሩ «የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች» በሚል ርዕስ ከባለ ድርሻ አካላት ግብአት ለመሰብሰብ በጥር ወር 2015 ዓ.ም ተዘጋጀ የተባለውን ረቂቅ ሰነድ ይህ ጸሐፊ በሚገባ አንብቦታል።

ከሰነዱም በተጨማሪ በዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተዘጋጁ በርካታ ዓለም አቀፍ የጥናት ውጤቶችንና ተሞክሮው ያላቸው አገራት እነማን እንደሆኑም ጊዜ ወስዶ ለመመርመር ሞክሯል። የሽግግር ፍትሕ የሚለው ጽንሰ ሃሳብ የተዋወቀው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጠናቀቅ በኋላ የናዚዎችን ወረራና ግፍ እንዲመረምር (እ.ኤ.አ ከ1945 - 1946) በተቋቋመው የኑረምበርግ ወታደራዊ ችሎት አማካይነት ነበር። ለችሎቱ መቋቋም መንስዔ የነበረው መሠረታዊ ጉዳይ «የጦርነቱ ዋና ቀስቃሽና ተጠቂ አገራት እነማን ናቸው?» «በጦርነቱ ወቅት የነበራቸው ሚናስ ምን ነበር? የትኛው አገር በማን ተጠቅቷል? ምንስ ጉዳት ደርሶበታል? ለደረሰበት ጉዳትስ የትኛው አገር ማንን ይካስ? የካሳው ዓይነትና መጠንስ ምንና ስንት ይሁን? ከአገራቸው የተሰደዱና ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ዜጎችስ እንዴት ፍትሕ አግኝተው ወደየቄያቸው ይሰባሰቡ? መሰል ጥፋቶችና ውድመቶች ዳግም በዓለማችን ላይ እንዳይፈጠሩ ምን ስልትና ዘዴ ይቀየስ? የሚሉትን ወሳኝ «ፍትሕ ነክ ጉዳዮች» መርምሮ ውሳኔ በመስጠት መንግሥታት ተረጋግተው የፈራረሰውን ሉዓላዊነታቸውን መልሰው እንዲገነቡ ለማገዝ ተወጥኖ የተቋቋመ ዓለም አቀፋዊ የፍትሕ አካል ነበር። ችሎቱ ምን ሠራ? ተልዕኮውን ያጠናቀቀው በምን ውጤት ነበር? ለሚሉት ጥያቄዎች በአገሬ ላይ ወራሪው የኢጣሊያ ፋሽስት የፈጸማቸው ግፎች እንደምን ተድበስብሰው እንዳለፉ ብቻ አስታውሶ ማለፉ ይቀላል።

ውሎ ሲያድር «የሽግግር ፍትሕ» እየተባለ የተዋወቀው ጽንሰ ሃሳብ በአገር ደረጃ ወርዶ እያንዳንዱ አገር በፖለቲካና በሥርዓተ መንግሥታት የሽግግር ወቅት የተለያዩ ችግሮች፤ የእርስ በእርስ ግጭቶችና ጦርነቶች ሲያጋጥሙት በየአገራቱ ዐውድ መሠረት ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ተልዕኮ ገዘፍ ያሉ ጉዳዮችን ለመዳኘት የሽግግር ፍትሕ እንዲተገበር ምክረ ሃሳብ ቀርቦ ተቀባይነት በማግኘቱ በየአገራቱ ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት ተግባር ላይ ሊውል ችሏል።

የሽግግር ፍትሕ አስኳል ግብ በሰብዓዊ መብቶች ላይ የተፈጸሙ ጥሰቶችን መርምሮ ውሳኔ መስጠት ሲሆን፤ መሠረታዊ አእማድ እንደሆኑ የሚታመኑት አላባዊያኑም (ፍሬ ነገሮች) እውነትን ገላልጦ ማሳየት፤ ፍትሕ ሳይሸራረፍ እንዲተገበር ማድረግ፤ የተፈናቀሉና የተሰደዱ ዜጎች ወደ መኖሪያ ቀዬአቸው መመለሳቸውን ማረጋገጥ፤ መሰል ክፉ ድርጊቶች ዳግም እንዳይፈጸሙ መከላከል፤ ለተጎዱት ዜጎችና ቡድኖች ተገቢውን ካሣ መክፈልና ተቋማዊ ሪፎርም በማድረግ አመቺ የፍትሕ ሥርዓት መዘርጋት የሚሰኙት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ኢትዮጵያን ከፊት ለፊቷ ተጋርጠው ከሚጠብቋት ወቅታዊና ወሳኝ የቤት ሥራዎች መካከል አንዱና ምናልባትም ተቀዳሚው ዋና ጉዳይ ይህንን የሽግግር ፍትሕ የመተግበር ኃላፊነት እንደሆነ ታምኖበት እየተሠራ መሆኑን ዕለት በዕለት ዜናውን እየተመገብን አለን።

መቼም እንደ አገር «አለባብሰን አርሰን፤ በአረም የተመለስንባቸው» አገራዊ ታሪኮቻችን ከ እስከ ተብለው ተዘርዝረው የሚያልቁ አይደሉም። የእርስ በእርስ መቆራቆዞችም ሆኑ መረር ያሉ ግጭቶችና ጦርነቶች ለእኛ አገር ብርቅም ድንቅም አይደሉም። እስከነአካቴው ያለ ግጭትና ያለ እርስ በእርስ መገፋፋት አትኑሩ ተብሎ የተፈረደብን እስኪመስል ድረስ በአገራችን ታሪኮች ያላለፍናቸው የፈተና ዓይነቶች አሉ ለማለት አያስደፍርም።

በብዙ አገራት ውስጥ ለተፈጸሙ የእርስ በእርስ ግጭቶችና መመሰቃቀሎች እያንዳንዱ አገር በየራሱ ዐውድ የሽግግር ፍትሕ ለማስፈን በሞከረበት አጋጣሚም የከፊል አገራት ጥረት በክሽፈት ሲጠናቀቅ ለአንዳንድ ልበ ሰፊ አገራትም ዘዴው እንደሠራላቸው ተደጋግሞ ተገልጾልናል። ዝርዝሩን መከለሱ እጅግም አይጠቅምም።

ጉዳዩንከራሳችንአንጻርእነመርምረውናየቆምንበት አብዛኛው የታሪካችን መሠረት ለሽግግር ፍትሕ ባዕድ ከመሆኑ የተነሳ አገራዊ ታሪካችን በአብዛኛው እየተነባበረ ሲለበጥ የኖረው በግፍ ድርጊቶች ነው። የሩቁን ትተን እንኳን የቅርብ ጊዜውን ብናስታውስ ወታደራዊው ደርግ ሥልጣን በያዘበት ማግሥት በግፍ የተጨፈጨፉት የንጉሡ ዘመን ሹማምንት ደም ፍትሕ በመሻት ወደ ፀባኦት ከመጮኽ የታቀበ አይመስልም። የደርግ መንግሥትና እርሱን የሚቃወሙት የፖለቲካ ተብዬ ቡድኖች በደም የተጨማለቀ ታሪክም ዛሬም ድረስ ምዕራፉ የተዘጋ አይመስልም። ወያኔ/ኢህአዴግ ከወታደራዊው መንግሥት ሥልጣን ከነጠቀበት ጊዜ ጀምሮ ሲተገብራቸው የኖሩት የግፍ ዓይነቶችም እንዲሁ በበቀልና በደም የቀለሙ ነበሩ።

እነሆ ዛሬም እንደምናስተውለው ስሙና መለያው ይለያይ ካልሆነ በስተቀር ምድራችንን የተጫነው የግፍ ደመና ይህ ልኩ የሚባል አይደለም። ዱር በቀል ቡድኖች «ንጹሐንን ገደሉና አፈናቀሉ» የሚለው መርዶ አደንዝዞን የምንይዘውንና የምንጨብጠውን አሳጥቶናል። ይሄም አነሰ ተብሎ ያለዋጋ ዜጎችን የገበርንበት የትናንቱ ስም የለሽ ጦርነት ያሸከመን የግፍ ሸክምም ከግምት የገዘፈ የጥቁር ታሪካችን አንዱ ምዕራፍ ነው።

የገበርነው ነፍስና የወደመው ሀብት ግምት እንኳንም መከራ ባደነዘዘው የእኛ አእምሮ ሊሰላ ቀርቶ አሸማቃቂ ታሪካችንን ለምናወርሰው ለመጻኢው ትውልድም ቢሆን ሳይወሳሰብበት የሚቀር አይመስለንም። እህህ ያሰኘን አገራዊ አበሳችንን በሙሉ እንዘርዝር ካልን በቂምና በበቀል ቁርሾ ስለምንሰክር «በሆድ ይፍጀው» ማለፉ ይበጅ ይመስለናል።

የሽግግር ፍትሕ እያልን ነጋ ጠባ ቃሉን በመጥራት እንደ ርሃብ ቀን ሰብል የምንጓጓለት ፍትሕ የማስፈን ሥርዓት በአግባቡ እንዲተገበርልን የምንመኘው ይኼን ሁሉ የታሪካችንን ስብራት ይጠግንልናል፤ ዕለት በዕለት የሚያስለቅሱንን አዳዲስ የግፍ ድርጊቶችም ይገታልን ይሆናል ብለን ተስፋ በማድረግ ነው። ያለምክር ተጸንሶ በጭንገፋ እንደተጠናቀቀው «የእርቀ ሰላም ኮሚሽን» መክኖ እንደማይቀርም እምነታችን ጽኑ ነው።

የሽግግር ፍትሑን ትግበራ በተመለከተ ይህ ጸሐፊ ሰሚ ባገኙሁ ብሎ የሚመኘው አንዳንድ መሻት አለው። «የሌሎችን ተሞክሮ በመቀመር» የሚባልለትን አስተሳሰብ ለጊዜው አቆይተን ስለምን ከራሳችን አገር በቀል እሴቶች አንጀምርም? ከየብሔረሰቡ የከበሩና አንቱታን ያተረፉ ዕድሜ ጠገብ የዕውቀት አባቶችና እናቶች ተሰብስበው በቅድሚያ በነፃነት እንዲመክሩ ዕድል ቢመቻችላቸውስ? ለምሳሌ፡- ደም የተቃቡ ወገኖች ሲታረቁበት የኖሩትን ባህላዊውን «ጉማ - የደም ካሣን» ዘመኑን በዋጀ መልኩ ዐውዱን አስጠብቀው ምክረ ሃሳብ እንዲያቀርቡ ቢደረግ አይጠቅምም? አፈርሳታው፣ አውጫጭኙ ወዘተ. በዘመናችን ልክ እየተሟሸ ቢሞከርስ? በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምሥራቅ በምዕራብና በመካከለኛው የአገሪቱ ክፍል ለሽግግር ፍትሑ የሚጠቅሙን አገር በቀል እውቀቶችንና ጥበቦችን ቀድመን እንፈትሽ። የተቀረውን የባዕዳን ተሞክሮ ከዚያ በኋላ እንደርስበታለን።

ያለበለዚያ ግን የሌሎችን ተሞክሮ ለመቅሰም በሚል ምክንያት ብቻ ባህር ተሻግሮ ለመሄድ ማሰፍሰፉን ለጊዜው ገታ በማድረግ ከራሳችን ባህላዊ ጓዳዎች መፍትሔዎችን መፈለግ ብልህነት ነው። እስከ መቼስ ለትልቅ ለትንሹ፣ ለተቸገርንበትም ላልተቸገርንበትም ጉዳዮች «የሌሎች አገራትን ተሞክሮ» እያልን ወደ ባዕዳን እናንጋጥጣለን? እነርሱስ ከእኛ እንዲማሩ ለምን በተግባር ፈትነን ያተረፍንባቸውን ትሩፋቶቻችንን ቀምረን አናማልላቸውም? እኮ እስከ መቼ አገር በቀል እውቀቶቻችንን «ባይተዋር ቤትኛ» አድርገን የሌሎች አገራትን እንዳንቆለጳጵስን እንኖራለን?። ያለንን አክብረን የሌለንን መዋሱ ላይ መበርታት የአመራር ጥበብ አንዱ መገለጫ ነው። እንምከርበት። ሰላም ለሕዝባችን፤ በጎ ፈቃድ ለዜጎች።

## ተናጋሪው ዶሴ

# ድህነትን ታሪክ ሲያደርጉ ወጥተው ‹‹አተርፍ ባይ አጉዳይ›› የሆኑ ወጣቶች

**አስመረት ብስራት**

በማለዳ የገጠር ከተማዋ ላይ ወጣቶች በብዛት ይታያሉ። በርካታ ኮበሌዎችና ኮረዶች የሚበዙባት የአማራ ክልሏ ሲሪንቃ ከተማ። ቆነጃጅቶቹና ጎበዛዝቱ ወላጆቻቸውን በሥራ ከማገዝ ያለፈ ይህ ነው የሚባል ውጤታማ ሥራ አይሠሩም ነበር። በተለይ አንዳንዶቹ ልባቸው ከአገር የመውጣት አረብ አገር፣ ደቡብ አፍሪካ የመሰደድ ምኞት ተሞልቶ ትምህርቱም ሥራውም አልያዝ አልጨበጥ ብሏቸዋል። ለዚህም ነው ማልደው አደባባይ በመውጣት የደላሎችን ወሬ ማነፍነፍ ምርጫቸው ያደረጉት።

በአካባቢያቸው ሌት ከቀን ሥራ ሳይፈቱ ልብን በሚያሸፍቱ ታሪኮች የሚሞላቸው ደላሎችም በአንፃሩ ሞልተዋል። «እነ እገሌን አታይዋቸውም በሄዱ በአመታቸው እኮ ነው ለቤተሰቦቻቸው እንዲህ ያደረጉት..... ማነው ስሙ ደግሞ....» በማለት መከራዎች ቢደራረቡባቸውም በለሰ ቀንቷቸው የአረብ አገርን መሬት የረገጡት ጥቂት የአገራቸው ልጆች ተሳክቶላቸው ቤተሰቦቻቸውን ሲደግፉ የሚያሳዩ ምሳሌዎችን በመጥቀስ ይበልጥ መነሳሳት ይጨምሩባቸዋል። የማይበላ ተስፋና ስኬት ይሞሏቸዋል። ከዛማ ወሬው ጨዋታው ሁሉ «ካረብ አገር ስሄድ.....» ብሎ ነው የሚጀመረው።

ከእነዚህ ከአገር የመውጣት ጉጉት ሰቅዞ ከያዛቸው ወጣቶች መካከል አንዱ ወጣት ቤተሰቡንም ሆነ እራሱን የመቀየር ህልምን ይዞ ከአገሩ ቢነሳም ሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪ ይሉት ነገር ደርሶበት ከመንገድ ቀርቷል። ህልሙም የሚያጨናግፍ፣ ለሕይወቱ ሁሉ አስጊ ተስፋን አጨላሚ ጉዳይ ገጥሞታል። ጉዳዩ እንዲህ ነው።

### አንደኛው የአጋቾች ሰለባ

ወጣት ወንዴ አድማሱ ውጭ አገር ሄዶ ሠርቶ ለመለወጥ ካለው ፍላጎት በውስጣቸው ከሞላው የአካባቢው ነዋሪዎች አንዱ ነው። ወጣቱ የደላሎችን ጉትጎታ ተቀብሎ የአባቱን ጥማድ በሬ አሸጦ ቤተሰቡን ተሰናብቶና ተመርቆ ከቤቱ ወጣ።

ወጣቱ በጥቅምት ወር 2012 ዓ.ም ከሚኖርበት አካባቢ ከአማራ ክልል ሲሪንቃ ከተማ በመነሳት በወልዲያ አድርጎ አፋር ክልል ደረሰ። ከዚያም በእግር አስቸጋሪውን የበረሃ መንገድ ከውሃ ጥምና ከፀሐይ ሐሩር ጋር በመታገል የተወሰነ መንገድ አቋረጡ። በመቀጠል በመኪና በመጓዝ ጂቡቲ ገብቶ በባህር በጀልባ በመጓዝ የመን አገር ደረሰ። ከሁሉም አስከፊው ውሃ ላይ እየሄዱ ውሃ መጠማቱ እንደሆነ የሚናገርው ወጣት ወንዴ ከላይ የፀሐይ ንዳድ በብዛት በአንድ ጀልባ ላይ የታጨቁትን ወጣቶች ያለርህራሄ ሲቀጠቅጣቸው ከስር ደግሞ የፈላ የጨው ውሃ እየተፈናጠረ ሰውነታቸውን ይጠብሳቸው ጀመር።

ይህን ሁሉ አልፈው መዳረሻቸው ላይ ከደረሱ በኋላ ያልጠበቁት ፈተና ገጠማቸው። በራሱ አገር ቋንቋ የሚናገሩ የእሱ መሳይ ከለር ያላቸው ሰዎች እንደታገቱ ነገሯቸው። ወንዴም ከታጋቾቹ መካከል ነበር። በኋላ አጋቹ ታግቶ 4ሺ 500 ሪያል አምጣ ካልሆነ በሕይወት አትኖርም አሰቃይቼ እገድልሀለሁ በማለት ሲደበድበው ይቆያል።

ወንዴ ግን ምንም ስቃይ ቢበዛበትም ቤተሰቡ ያላቸውን ጥማድ በሬ ሸጠው ለእሱ በመሰጠታቸው እነሱን ከማሳቀቅ ብሞት ይሻላል በማለት የተጠየቀውን ገንዘብ ሳይሰጥ ይቀራል።

### ሌሎቹ ተበዳዮች

ሻንበል ሁሴን፣ ሁሴን ኢብራሂምና መሀመድ ሁሴን የተባሉ ወጣቶችም ልክ እንደ ወንዴ ውጭ አገር ሄዶ ሠርቶ ለመለወጥ ካላቸው ፍላጎት የተነሳ ጀማል ሰኢድ የሚባል ደላላ ጋር ይገናኛሉ። ደላላውም ወጣቶቹ ጉጉት ልባቸውን እንዳነሳሳው ሲያውቅ ወደ ሳዑዲ አረቢያ ለሥራ እልካለሁ በማለት ይነግራቸዋል። ደላላው ወጣቶቹን በአፋር በኩል በየመን በማቋረጥ ሳዑዲ አስገባችኋለሁ በማለት በማሳመን ሳዑዲ አረቢያ ለመሄድ በታኅሣሥ ወር 2012 ዓ.ም ከሚኖሩበት አካባቢ አማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን በመነሳት በኮምቦልቻ አድርገው አፋር ክልል ከዚያም በእግር ጉዞ ይጀምራሉ። ከቀናት የእግር ጉዞ በኋላ 8 ቀን የፈጀ የመኪና ጉዞ ያደርጋሉ። ከዚያ በጀልባ ወደ የመን ከደረሱ በኋላ ለጊዜው ያልተያዙ አህመድ ሰይድ እና አንወር በሚባሉ አጋቾች እጅ ላይ ይወድቃሉ፡፡

በኋላም ወጣት ሻንበል ሁሴንን 30 ሺ ብር አምጣ ብለው በመደብደብና ወደ አባቱ ስልክ በመደወል እኛ በምንሰጥህ የባንክ አካውንት 30 ሺ ብር የማትልክ ከሆነ ልጅህን በሕይወት አታገኘውም ሲሉት ገንዘቡን በሂሳብ ቁጥሩ ለግብረ-አበሮቻቸው የላከ ሲሆን፣ በተመሳሳይ የግል ተበዳይ ሁሴን ኢብራሂምን እና መሀመድ ሁሴንን አግተው 25 ሺ ብር እንዲያመጡ በማስገደድ፣ በመደብደብ እና አግቶ በማቆየት በስተመጨረሻም ወደ አባቶቻቸው ስልክ በመደወል ብሩን አስልከዋል፡፡

### የፖሊስ ምርመራ

ይህን እኩይ ተግባራቸውን ያወቀ ፖሊስም ልጆቻችን ታገቱና ጠፉ የሚል ጥቆማን ተከትሎ ምርመራ ይጀምራል። የሰውና የሰነድ ማስረጃን አጠናክሮ የወንጀል ፈፃሚዎቹን ፎቶ በመያዝ አገር እስኪገቡ ድረስ ይጠባበቅ ጀመር። መቼም ከሞትና ከአገር የሚቀር የለምና አገራቸው ሲመለሱ አድፍጦ የሚጠባበቀው ፖሊስ በቁጥጥር ስር አውሎ ክስ እንዲመሰርት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የተደራጁና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ዐቃቤ ሕግ አስተላልፎ ይሰጣል።

### የክስ አቀራረብ

የዐቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው 1ኛ መለስ ካህሳይ፣ 2ኛ ሀፍቶም ገ/እየሱስ እና 3ኛ ከማል ይማም የተባሉ ተከሳሾች በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና በሰው መነገድና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 3/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በዐቃቤ ሕግ 4 ክሶች ቀርቦባቸዋል፡፡

1ኛ ክስ በሦስቱም ተከሳሾች ላይ ሲሆን ተከሳሾች ካልተያዙት ግብረ-አበሮቻቸው ጋር በመሆን ከኢትዮጵያ ክልል ውጪ ሳዑዲ አረቢያ ድንበር ራዳ ተብሎ ከሚጠራው ቦታ ላይ በሕገ-ወጥ መንገድ ሰዎችን ለማዘዋወር በማሰብ የግል ተበዳይ ወንዴ አድማሱ ውጭ አገር ሄዶ ሠርቶ ለመለወጥ ካለው ፍላጎት የተነሳ በጥቅምት ወር 2012 ዓ.ም ከሚኖርበት አካባቢ ከአማራ ክልል ሲሪንቃ ከተማ በመነሳት በወልዲያ አድርጎ አፋር ክልል ከዚያም በእግርና በመኪና በመጓዝ ጂቡቲ ገብቶ በባህር በጀልባ በመጓዝ የመን አገር ከደረሰ በኋላ ለጊዜው ያልተያዘው ከንዙ በሚባል አጋች ታግቶ 4ሺ 500 ሪያል አምጣ ካልሆነ በሕይወት አትኖርም አሰቃይቼ እገድልሀለሁ በማለት ሲደበድበው ቢቆይም ተበዳይ የተጠየቀውን ገንዘብ አግኝቶ ሊሰጠው አልቻለም፡፡

በኋላም በከንዙ ግብረ-አበሮች ለሁለት ሳምንት በእግርና በመኪና ተጉዞ ሳዑዲ ድንበር ራዳ የሚባል ቦታ ለተከሳሾቹ ተላልፎ የተሰጠ ሲሆን ተከሳሾችም ሳዑዲ ላይ የሚኖር የዘመድ ስልክ ስጠን የማትሰጠን ከሆነ አሰቃይተን እንገድልሃለን፣ በሕይወት አትቆይም በማለት እጅና እግሩን በገመድ አስረው በዱላ እና በኤሌክትሪክ ሽቦ እየተፈራረቁ በመግረፍ እንዲሁም የብረት መጥረቢያ፣ ሽጉጥና ጩቤ በማሳየት ልንገድልህ ነው እያሉ ሲያስፈራሩት የነበሩ እና ተበዳይ የታገተበት ራዳ የተባለው ቦታ በተከሳሾቹ አባሪዎች በጦር መሣሪያ የሚጠበቅ፣ በጣም ጠባብ ቦታ ከመቶ ሰዎች በላይ የሚቆዩበት፣ ሙቀቱ ከፍተኛ የሆነ፣ ሰው በሰው ላይ ተደራርቦ የሚተኛበት እንዲሁም በቂ ምግብና ውሃ በሌለበት ከ2 ወር በላይ አቆዩት፡፡

በኋላም ሳዑዲ አረቢያ የሚኖር ዘመድ ስልክ ቁጥር ባለማግኘቱ ምክንያት በአማራጭ ኢትዮጵያ የሚኖር የቤተሰብ ስልክ ስጠን ሲሉት የወንድሙን ስልክ ሲሰጣቸው ተከሳሾቹም ደውለውለት ወንድምህን አግተነዋል 35 ሺ ብር ካላስገባህ ወንድምህን በሕይወት አታገኘውም እያሉ ሦስቱም ተከሳሾች በተራ እያስጠነቀቁ የነገሩት እና ኢትዮጵያ የሚኖር ሰው አካውንት የሰጡት ሲሆን በአንድ ግለሰብ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 30 ሺ ብር ያስገባ ሲሆን በመሐል የግል ተበዳይ በሳዑዲ ፖሊሶች በቁጥጥር ስር ውሎ ለ11 ወራት ያህል ከታሰረ በኋላ ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ ተደርጎ ወደ ኢትዮጵያ የገባ በመሆኑ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት በሰው የመነገድ ድርጊት ወንጀል ተከሰዋል፡፡

2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ክስ በሦስቱም ተከሳሾች ላይ ሲሆን ተከሳሾች ካልተያዙት ግብረ-አበሮቻቸው ጋር በመሆን ከኢትዮጵያ ክልል ውጪ ሳዑዲ አረቢያ ድንበር ራዳ ተብሎ ከሚጠራው ቦታ ላይ በሕገ-ወጥ መንገድ ሰዎችን ለማዘዋወር በማሰብ ሻንበል ሁሴን፣ ሁሴን ኢብራሂምና መሀመድ ሁሴን የተባሉ የግል ተበዳዮችን ውጭ አገር ሄዶ ሠርቶ ለመለወጥ ካላቸው ፍላጎት የተነሳ ለጊዜው ካልተያዘው ጀማል ሰኢድ የሚባል ደላላ ጋር ሲነጋገሩ ወደ ሳዑዲ አረቢያ ለሥራ እልካለሁ በአፋር በኩል በየመን በማቋረጥ ሳዑዲ አስገባችኋለሁ በማለት በማሳመን ተበዳዮች ሳዑዲ አረቢያ ለመሄድ በታኅሣሥ ወር 2012 ዓ.ም ከሚኖሩበት አካባቢ አማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን በመነሳት በኮምቦልቻ አድርገው አፋር ክልል ከዚያም በእግርና በመኪና ለ8 ቀን በመጓዝ የመን ከደረሱ በኋላ ለጊዜው ያልተያዙ አህመድ ሰይድ እና አንወር በሚባሉ አጋቾች ታግተዋል፡፡

በኋላም የግል ተበዳይ ሻንበል ሁሴንን 30 ሺ ብር አምጣ ብለው በመደብደብና ወደ አባቱ ስልክ በመደወል እኛ በምንሰጥህ የባንክ አካውንት 30 ሺ ብር የማትልክ ከሆነ ልጅህን በሕይወት አታገኘውም ሲሉት ገንዘቡን በሂሳብ ቁጥሩ ለግብረ-አበሮቻቸው የላከ ሲሆን፣ በተመሳሳይ የግል ተበዳይ ሁሴን ኢብራሂምን እና መሀመድ ሁሴንን አግተው 25 ሺ ብር እንዲያመጡ በማስገደድ እና በመደብደብ እና አግቶ በማቆየት በስተመጨረሻም ወደ አባቶቻቸው ስልክ በመደወል ብሩን አስልከዋል፡፡

በኋላም ሌሎች ከታገቱ ሰዎች ጋር በመኪና ተጭነው ሳዑዲ ድንበር ራዳ የሚባል ቦታ ለተከሳሾች ተላልፈው ከተሰጡ በኋላ የግል ተበዳዮችን እያንዳንዳቸው 35 ሺ ብር ቤተሰቦቻቸው እንዲከፍሉ በተከሳሾች ትዕዛዝ ሲሰጣቸው የመን ላይ ከፍለናል በማለታቸው አስገድደው በድጋሜ ለማስከፈል እጅና እግራቸውን በገመድ በማሰር በኤሌክትሪክ ገመድ፣ በዱላ እና በእርግጫ እየተፈራረቁ ደብድበው የቤተሰብ ስልክ ተቀብለው በመደወል ልጅህን አግተነዋል ልንገድለው ነው ብር ላክ በማለት በሂሳብ ቁጥርና በእጅ ገንዘብ እንዲሰጣቸው ያደረጉ እና ከላይ አንደኛ ተበዳይ በቆየበት ቦታ እና ሁኔታ ውስጥ ከቆዩ በኋላ ወደ አገራቸው የተመለሱ በመሆኑ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት በሰው የመነገድ ድርጊት ወንጀል ዐቃቤ ሕግ ክስ መስርቶባቸዋል፡፡

ተከሳሾች የተከሰሱበት ክስ በችሎት ተነቦላቸው የወንጀል ድርጊቱን አልፈፀምንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎቹን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ በዚህም መሠረት ፍርድ ቤቱ ተከሳሾች እንዲከላከሉ ብይን በሰጠው መሠረት ተከሳሾች የመከላከያ ማስረጃ አቅርበው ቢያሰሙም የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ ያላስተባበሉ በመሆኑ በ4ቱም ክሶች ጥፋተኛ ናችሁ ብሏቸዋል፡፡

### ውሳኔ

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራሉ የመጀ መሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ 14ኛ ወንጀል ችሎትም ግራ ቀኙን ተመልክቶ ሌሎች አጥፊዎችን ያርማል ያለውን ውሳኔ አስተላልፏል። 1ኛ ተከሳሽን በ20 ዓመት ጽኑ እስራትና በ160 ሺ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ የተወሰነ ሲሆን 2ኛና 3ኛ ተከሳሾች ደግሞ እያንዳንዳቸው በ18 ዓመት ጽኑ እስራትና በ130 ሺ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኖባቸዋል፡፡



መዝናኛ

## ማረፊያ/ ትዝብት

# ውሃ “ሽኝት” በአዲስ አበባ ጎዳናዎች

**ተስፋ ፈሩ**

አንዳንድ ሆሄያት ይምታቱብኛል። “ን” ለማለት አስቤ “ኝ” ብዬ የምጽፍበት አጋጣሚ ብዙ ነው።ለምሳሌ በዚህ ጽሑፍ ርዕስ ላይ “ሽኝት” ብዬ የጻፍኩት “ሽንት” ለማለት ፈልጌ ነው። ስለዚህ ርዕሱን “ውሃ ሽንት በአዲስ አበባ ጎዳናዎች” ብላችሁ አስተካክላችሁ አንብቡልኝ። አንተ ያወላገድከውን የምናስተካክልበት ምን እዳ አለብን ካላችሁም “ውሃ ሽኝት” ብላችሁ ብታነቡትም ችግር የለውም። ውሃ ሽንት ማለት ያው የጠጣነው ውሃ ሽኝት ስለሆነ የትርጉም ለውጥ አያመጣም።

የሀገራችን ወግ ጸሐፊዎች ተደራሲያቸውን በተባእት ጾታ የማናገር ልማድ አላቸው። ለምን እንደሆነ እንጃ! እኔም ዛሬ እንደዛ ላደርግ ነው። “Who ማይነስ Who” ተብሎ የለም። እነሆ!

ውዱ አንባቢዬ ሆይ ... ለአዲስ አበባ እንግዳ ነህ? ከሆንክ ምክሬ ያስፈልግሃል።ካደርክበት ቤት ስትወጣ መንገድ ላይ ሽንትህ እንዳይመጣ ጸልየህ ውጣ። በተቻለህ መጠን ውሃ አትጠጣ። ጉሮሮህ ደርቆ እረፍት ከነሳህ ግን የታሸገ ውሃ ገዝተህ ጠጣ። ታዲያ የፕላስቲክ ኮዳውን እንዳትጥለው።ይህን ስልህ የአዲስ አበባ ካፌዎች አንድ ብርጭቆ ውሃ ለምነሃቸው ይከለክሉሃል ማለቴ አይደለም። የጠጣሃትን ውሃ እንድትሸኛት ግን ሽንት ቤታቸውን አይከፍቱልህም።

በአብዛኞቹ ካፌዎችና ሬስቶራንቶች ካልተስተናገድክ በቀር መሽናት አትችልም።ባሮችና ላውንጆች ጋርም የተለየ ነገር የለም። እዚያ እንደውም የማያላውሱ ያልተጻፉ ሕጎች ቢያጋጥሙህ አይግረምህ።አንድ ቢራ አዘህ ሁለት ጊዜ መጸዳጃ ቤት መሄድ ልትከለከል ትችላለህ። አይዞህ! የሁለተኛውን ቢራ አንገት ስትጨብጥ ቁልፉን ያስጨብጡሃል።ለቅይጥ አገልግሎት በተገነቡት የከተማችን ሕንፃዎች ላይ የሚገኙት አብዛኞቹ ሽንት ቤቶች በፌስ ቡክ ቋንቋ ሲገለጹ “ኦንሊ ሚ” ናቸው፤ ፐብሊክ የሆኑት ደግሞ ባለቤት አልባ እስኪመስሉ ድረስ “ጽዱ” ናቸው።ለሱቅ ባለቤቶች ብቻ ቁልፍ ሰጥተው ሽንት ቤቶቻቸውን የሚከረችሙ ሞሎች ይበዛሉ። በእርግጥ እኛ ተጠቃሚዎቹ ዘንድም ችግር አለ። ተገቢ ካልሆነ አጠቃቀም እስከ ስርቆት መፈጸም የሚደርሱ ባለንብረቶችን የሚያስቆጡ ጥፋቶች እንፈጽማለን።

ቦታ ሳንመርጥ ዚፖችንን በምንከፍት ወንዶችና ቀሚሳቸውን በሚሰበስቡ ሴቶች ምክንያት አዲስ አበባ ጉድጓድ ሆናለች። እያንዳንዱ ነገር የራሱ የሆነ ጥቅምና ጉዳት አለው አይደል? በከተማችን በተገኘው ቦታ ሁሉ መሽናት ባህል መሆኑን ተከትሎ አንድ መጥፎ ልማድ ተወግዷል። ይሄውም በያጥሩና በየግድግዳው ላይ “መሽናት ክልክል ነው” ብሎ መጻፍ ነው። እንዲህ እንደዛሬው የትኛውም ቦታ ላይ መሽናት መብት ከመሆኑ በፊት፣ በየሃምሳ ሜትሩ ተጽፎ የሚታየው የከተማዋ ሞቶ “መሽናት ክልክል ነው” የሚል ነበር። እዚህም እዚያም ተለቅልቆ ለዓይን ይሸት የነበረው ጽሑፍ ዛሬ ተፈልጎ አይገኝም፡፡

ጽሑፉ በመቅረቱ አብዛኛው የከተማዋ ነዋሪ ደስተኛ ቢሆንም መተዳደሪያቸው ለነበረ ወገኖች ግን ትልቅ ጉዳት ነው።ጽሑፉን በመጻፍ ይተዳደሩ የነበሩት “ሙያተኞች” ዋጋ የሚደራደሩት “በሆሄ ይሄን ያህል ይከፈለን” እያሉ ነበር። ለምሳሌ በአንድ ሆሄ 50 ብር ተከፍሏቸው ለመጻፍ ከተስማሙ በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ የሚገኙት ሆሄያት ቁጥር በ50 ተባዝቶ ይከፈላቸዋል። በዚህ ምክንያት ሆነ ብለው መሽናት እንደማይቻል የሚገልጸው አረፍተ ነገር እንዲረዝም በማድረግ ሕዝቡን ይበዘብዙ ነበር። ከሽንት ሌላ የሚሸና ነገር እንደሌለ ልቦናቸው እያወቀ “መሽናት ክልክል ነው” ከሚለው ሀረግ በፊት “ሽንት” የሚል ቃል ይጨምራሉ።የሚያጽፈው ሰው የመክፈል ችግር የለበትም ብለው ካሰቡ ደግሞ “ሽንት” ከሚለው ቃል ቀድመው “እዚህ ቦታ” የሚል ሀረግ ያስገባሉ። በጣም ስግብግብ የሆኑት አይንአውጣ ጸሐፊዎች “ቦታ” የሚለውን ባለ ሁለት ሆሄ ቃል አስወጥተው “አካባቢ” በሚል ባለአራት ሆሄ ቃል ይተኩታል። በመጨረሻ “መሽናት ክልክል ነው” የሚለው ሀረግ “እዚህ አካባቢ ሽንት መሽናት ክልክል ነው” ተሰኝቶ እጥፍ ክፍያ ያስገኛል።

እያደር “የትም ይመቸኛል” በሚል ሳውንድ ትራክ ታጅቦ ሽንቱን የሚሸናው ሰው ስለጨመረ ከተማዋ ከዚህ አሰልቺ የክልከላ ጽሑፍ ተላቀቀች። ምን ዋጋ አለው! አዲስ አበባ በየትም ይመቸኛል ሙሸመንት ተደናግጣ ለኗሪዎቿ መጸዳጃ ቤት መገንባት ሲገባት ለሌላ አዲስ ወራሪ ኃይል እጇን ሰጠች። ተረኛው ወራሪ ኃይል ባልዲ ሆነ። የአዲስ አበባ ጎዳናዎች በሽንት መሸኛ ባልዲዎች አሸበረቁ። እነዚህን ያዋቂ ፖፖዎች በዋና ዋና መንገዶችና አደባባዮች ላይ አስቀምጠን ስናበቃ ደረታችንን ነፍተን አዲስ አበባ ከተቆረቆረች 137 አመታት አስቆጥራለች እንላለን። ከተማችን ነብስ ካወቀ በኋላ እንደ ልጅነቱ ፖፖ ላይ የሚሸና ጎረምሳ ሆና፣ የኛ ዲስኩር ማለቂያ የለውም። የአፍሪካ መዲና... ሸገር... አዱ ገነት... ፊንፊኔ... በረራ ...!

እነዚህ ባልዲዎች እየሰጡ ያሉትን አገልግሎት እያጣጣልኩ አይደለም። በበኩሌ “አዲስ አበባ የሁሉም ነች” ከሚለው ፖለቲካ በላይ የሚዋጥልኝ፣ የእነዚህ ባልዲዎች የሁሉም መሆን ነው። ምክንያቱም ፈኛው የተወጠረን ሽንተኛ ሁሉ ያለ ልዩነት ያስተናግዳሉ። አዲስ አበቤ ከባልዲ ቀድቶ የጠጣውን ውሃ መልሶ ለባልዲ ማቀበሉን “የቄሳርን ለቄሳር” ብሎ ያልፈዋል እንጂ አያማርርም።

አዲስ አበባ ላይ በኪራይ ቤት ውስጥ የሚኖር ሰው ቋሚ በሽታ የሽንት ቧንቧ ኢንፌክሽን ነው።እንደ ልቡ መሽናት ባለመቻሉ ምክንያት ውሃ መጠጣት የሚፈራ ተከራይ ብዙ ነዋ! ሽንት ቤት ለመሄድ ተሳቆ ቤቱ ውስጥ ባገኘው ፈሳሽ መያዣ ሽንቱን የሚያቁረውን ቤት ይቁጠረው። በየሰፈሩ የሚቀመጡ የቆሻሻ ገንዳዎች ጢም የሚሉት ሽንት በተሞላ የፕላስቲክ ጠርሙስና ጀሪካን ሆኗል። የ19 ሚሊዮን ብሩ ባስ መጸዳጃ ቤት አለው ሲባል ሰምቼ አዲስ አበባ ነጋላት ብዬ ነበር። በኋላ እንዲህ ያለ ወሬ የሚነዙት ቧልተኞች ናቸው ተባለ። ይህ የሚያሳየው የከተማችን አሳሳቢ ችግር ቧልተኞችን ሳይቀር እንዳሳሰባቸው ነው።እውነታቸውን ነውኮ! ችግሩን መቅረፍ ባይቻል እንኳን ለመቀነስ መንቀሳቀስ ይገባ ነበር።ሌላው ቢቀር የሚጠጣ ነገር አምራች ድርጅቶች ላይ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ የሚያደርግ አንዳች ዓይነት ግዴታ በመጣል የተወሰኑ መጸዳጃ ቤቶችን እንዲገነቡ ማድረግ ይቻላል።

ለጉዳዩ ትኩረት ያለመስጠትና ሙሰኝነት እንጂ የሕግ ክፍተት ያለ አይመስለኝም። መጸዳጃ ቤት የሌለው ምግብ ቤት ገጥሞኝ ያውቃል። በእጅ ካልተሄደ በቀር መጸዳጃ ቤት አልባ ምግብ ቤት የንግድ ፈቃድ ሊያገኝ አይችልም።ከ50 አመታት በፊት በቅድሚያ መጸዳጃ ቤት ካልተሟላ ምግብ ቤት ቀርቶ መኖሪያ ቤት እንኳን መገንባት አይፈቀድም ነበር። በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ በታተመ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ያገኘሁት አንድ ጽሑፍ ይህን የሚያረጋግጥ ነው። “በቅድሚያ የመጸዳጃ ቤት ያልሠሩ የቤት መሥሪያ ፈቃድ አይሰጣቸውም” በሚል ርዕስ የወጣው ጽሑፍ እንደሚከተለው ይነበባል።

**በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ወደፊት ቤት የሚሠሩ ሰዎች አስቀድመው የሽንት ቤት ካልሠሩ የቤት መሥሪያ ፈቃድ የማይሰጣቸው መሆኑን የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ባወጣው መግለጫ አስታወቀ።ማንኛውም ቤት ተገቢው የንጽህና ቤት እንዲኖረው አስፈላጊ ነው።በዚህ በኩል ያለውን ችግር ለማሟላት ይረዳ ዘንድ ለወደፊቱ የቤት ሥራ ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ የቤት ውስጥ የንጽህና ቤት ለመሥራት የማይችሉ ከዋናው ቤት ውጪ የሚሠሩትን የንጽህና ቤት ሠርተው መጨረሳቸው ካልተረጋገጠ የቤት ሥራ ፈቃድ አይሰጥም። ይህም ተግባር በጥብቅ ቁጥጥር እንዲደረግበት ለቴክኒክ አገልግሎት ዋና መስሪያ ቤትና ለየክፍል ማዘጋጃ ቤቶች ትዕዛዝ መተላለፉን መግለጫው አስረዳ።በትዕዛዙ መሠረት አነስተኛ ቤተ ሠሪዎች፣ ቤቱን ከመሥራታቸው በፊት ተገቢ የሆነ የንጽህና ቤት እንዲሠሩ ይገደዳሉ። የማዘጋጃ ቤቱም ለሁሉም ቤቶች እንደየአቅማቸው የንጽህና ቤት እንዴት መሥራት እንዳለባቸው ምክርና ፕላን በመስጠት ስለሚረዳ፤ ሕዝቡ በዚህ ተግባር ከማዘጋጃ ቤቱ ጋር እንዲተባበር የፕሬስና የሕዝብ ኅብረት ማስፋፊያ ክፍል ገልጧል፡፡**

እንግዲህ ወደ ኋላ ቀርተናል እንዳንል ኋለኞቻችን በጋዜጣ ያስነገሩት ይህ መግለጫ እጅን በአፍ የሚያስጭን የሥልጣኔ ውሃ ልክ ነው። ወደ ኋላ መመለስም ሆነ ወደፊት መራመድ ተስኖን ቅርቃር ውስጥ ሳንገባ አንቀርም።ምን ተሻለን ?

## ዓለም አቀፍ



ፑቲን እና ዢ

### የቻይናው ፕሬዚዳንት ዢ ወደ ሞስኮ አቅንተው ከቱፒን ጋር ሊወያዩ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የቻይናው ፕሬዚዳንት ዢ ጂንፒንግ በቀጣይ ሳምንት ወደ ሞስኮ አቅንተው ከሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ጋር እንደሚገናኙ ይፋ ተደረገ።

የሩሲያ መንግሥት ፑቲን እና ዢ «በአጠቃላይ አጋርነት እና በስትራቴጂካዊ ትብብር ዙሪያ» ይነጋገራሉ ብሏል።

ጉብኝቱ የሚካሄደው የሩሲያ አጋር የሆነችው ቻይና የዩክሬን ጦርነትን ለማስቆም ላቀረበችው ምክረ ሃሳብ ምዕራባውያን ጀርባቸውን ከሰጡ በኋላ ነው።

ምዕራባውያኑ ቤይጂንግ የጦር መሣሪያዎችን ለሞስኮ ከመስጠት እንድትቆጠብ ሲያስጠነቅቁ ቆይተዋል።

የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ፕሬዚዳንት ዢ በፑቲን ግብዣ ከሰኞ መጋቢት 11 እስከ 13/2015 ዓ.ም. ድረስ በሞስኮ ቆይታ እንደሚያደርጉ አስታውቋል።

«የወዳጅነት እና የሰላም» በተባለው ጉብኝት ሁለቱ መሪዎች ሲገናኙ በርካታ የሁለትዮሽ የትብብር ሰነዶች እንደሚፈረሙ ይጠበቃል።

የቻይና የውጭ ጉዳይ ቃል አቀባይ ሁአ ቹፒንግ አገራቸው በዩክሬን ጦርነት ለየትኛውም ወገን ያላደላ አቋም እንዳላት ገልጸዋል።

ከጥቂት ሳምንታት በፊት የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቭሎድሚር ዜሌንስኪ ጦርነቱን ለማስቆም የቻይና ምክር ሃሳብ ላይ ከዢ ጋር ተገናኝተው መምክር እንደሚፈልጉ ተናግረው ነበር።

«ቻይና ለሩሲያ ጦር መሣሪያ አትሰጥም የሚል የጸና እምነት እንዲኖረኝ ፈልጋለሁ» ብለው ነበር ዜሌንስኪ።

ምንም እንኳ በቻይና ባለሥልጣናት ባይረጋገጥም ዢ የሩሲያ ጉብኝታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ከዜሌንስኪ ጋር በቴሌ ኮንፍረንስ ይገናኛሉ የሚሉ መረጃዎችን የአሜሪካ መገናኛ ብዙኃን እያወጡ ነው።

የዩክሬን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዲሚይትሮ ኩሌባ ፕሬዚዳንት ዜሌንስኪ ከዢ ጋር በስልክ ለመነጋገር ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ኃላፊ አንቶኒ ብሊንከን ሩሲያ በዩክሬን እያደረገች ያለችውን ጦርነት ለመደገፍ ቻይና ጦር መሣሪያ እና ተተኳሽ ለመስጠት እያጤነች ነው ብለው ነበር።

የቻይና ኩባንያዎች ወታደራዊ ያልሆኑ ድጋፎችን ቀድሞውኑ ለሩሲያ እያደረጉ መሆናቸውን ገልጸው፤ አሁን ላይ አሜሪካ ያላት መረጃ ቤይጂንግ ወታደራዊ ድጋፍ ልታደርግ እንደምትችል ነው ብለዋል።

ቻይና ግን ይህን የአሜሪካን ክስ አጥብቃ ተቃውማለች።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ትናንት ሐሙስ መጋቢት 7/2015 ዓ.ም. ኪዬቭ እና ሞስኮ ግጭት ለማቆም ዳግም የሰላም ንግግር በአስቸኳይ መጀመር አለባቸው ብሏል።

የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኪን ጋንግ ከዩክሬኑ አቻቸው ኩሌባ ጋር በነበራቸው የስልክ ንግግር ሁለቱም ወገኖች እራሳቸውን ከግጭት ቆጥበው በአፋጣኝ የሰላም ንግግር ማድረግ አለባቸው ተብሏል።

ኩሌባ ከቻይናው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር በነበራቸው የስልክ ንግግር በግዛት አንድነት መርህ መከበር አስፈላጊነት ላይ መምከራቸውን ገልጸዋል።

### ሙሴቬኒ ምዕራባውያን በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን መብት ዙሪያ ‘ጊዜ እያባከኑ ነው’ አሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



የኡጋንዳ ፕሬዚዳንት ዩዌሪ ሙሴቪኒ

የኡጋንዳ ፕሬዚዳንት ዩዌሪ ሙሴቬኒ ምዕራባውያን አገራት የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎችን መብቶች በአፍሪካ አገራት ላይ በኃይል ለመጫን እየጣሩ ነው ሲሉ ወቀሱ።

ሙሴቬኒ ይህን ያሉት አገራቸው የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነትን በተመለከተ አዲስ ሕግ እያረቀቀች ባለችበት ወቅት ነው።

የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት ወንጀል በሆነባት ኡጋንዳ እየተረቀቀ ያለው ሕግ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ላይ የበለጠ ጠንካራ ቅጣት የሚጥል ነው።

ይሁን እንጂ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች አዲሱን ረቂቅ የኡጋንዳ ሕግን እየተቹ ይገኛሉ።

ፕሬዚዳንት ሙሴቬኒ መጋቢት 07/2015 ዓ.ም. በአገሪቱ ፓርላማ ቀርበው ንግግር ሲያደርጉ፣ የምዕራባውያን «እንግዳ የሆነ ባህል» ያሉትን የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት እንድንፈቅድ ማዕቀብ በመጣል ጫና ያሳድራሉ ብለዋል።

«ምዕራባውያን የራሳቸውን አሠራር በሌሎች ላይ ለመጫን የሚያባክኑትን ጊዜ ማቆም አለባቸው» ብለዋል።

አውሮፓውያኑ የአጎት እና የአክስት ልጅ ጋር ትዳር ይመሰርታሉ ያሉት ሙሴቬኒ፤ «እዚህ [ኡጋንዳ] የአንድ ጎሳ አባልን ማግባት ነውር ነው። እነሱ የቅርብ ዘመድ እንዳያገቡ ማዕቀብ እንጣል? ይህ የእኛ ሥራ አይደለም» ሲሉ ፕሬዚዳንት ሙሴቬኒ ተናግረዋል።

ሙሴቬኒ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያንን አፈንጋጭ ብለው የገለጿቸው ሲሆን፣ በጉዳዩ ላይ ብዙ ምክክር መደረግ አለበት ብለዋል።

ኡጋንዳ አሁን ላይ እያረቀቀች ባለችው ሕግ መሠረት በተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት ውስጥ ያለ ወይም እራሱን የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት አፍቃሪ ብሎ የሚገልጽ ሰው እስከ 10 ዓመታት የእስር ጊዜን እንዲያሳልፍ ያዛል።

የኡጋንዳ መንግሥት በአገሪቱ የሚንቀሳቀሱ የውጭ አገራት መንግሥታት ተቋማት እና ምዕራባውያን ኤጀንሲዎች የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነትን እያስተዋወቁ ነው በማለት ይከሳል።

ኡጋንዳ ምንም እንኳ ፀረ የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት ሕግ ቢኖራትም፣ በቅርብ ዓመታት በፍላጎት ላይ በተመሠረተ የተመሳሳይ ጾታ ግንኙት ምክንያት የተቀጣ ሰው የለም።

# መጋቢ አዕምሮ

# ጭፍን ፍረጃ፣ ጥላቻንና አግላይነትን እንዴት ማስወገድ ይቻላል?

አስናቀ ፀጋዬ

የማህበራዊ ሥነ-ልቦና ሳይንስ አንድ ሰው በሌሎች ኑሮ ምክንያት የሚደርስበትን ተፅእኖ ወይም የእርሱ ኑሮ በሌሎች ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ ያጠናል። ይህም በማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ በሚፈጠር ግንኙነት የተነሳ አንዱ ሌላው ላይ ወይም ሌላው አንዱ ላይ የሚያደርሱትን ተፅእኖ ያጠቃልላል። በዚህ ተፅእኖ ምክንያትም ሌሎች ሰዎችን የምናይበት መንገድ የተለያየ ይሆናል። ማህበራዊ እይታ ደግሞ በሌሎች ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ላይ ያለን አመለካከት ሲሆን ከዚህ በመነሳት ሌሎች ሰዎች እንዲህ ናቸው ፤ እንዲያ ናቸው እያልን እንመድባቸዋለን ወይም እንፈርጃቸዋለን።

አንዳንድ ጊዜ ምደባችን ወይም ፍረጃችን በተጨባጭ መረጃ ላይ ያልተመሰረተና በምክንያት ያልተደገፈ፣ በደፈናው ፊት ለፊት ካገኘነው ነገር በመነሳት የሚሰጥ ሊሆን ይችላል። ጭፍን ፍረጃ ወይም /stereotype/ ስለ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን በተወሰነ አካላዊ አቀማመጥ ወይም ሌላ እውነታ ላይ የተመሰረተ አመለካከት ነው የሚባለውም ለዚህ ነው። ለምሳሌ የቆዳ ቀለምን፣ የቋንቋ አጠቃቀምን ወይም የሚያሳየውን ባህሪይ በማየት ስለ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን የሚኖር አመለካከት ጭፍን ፍረጃ ነው።

ጭፍን ፍረጃን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል። የመጀመሪያው ግለሰብ ተኮር ፍረጃ ሲሆን ይህ የፍረጃ አይነት በግለሰብ ላይ ያነጣጠረ ነው። ለምሳሌ የሰዎች መጠሪያ ስም ላይ ተንተርሶ የሚኖር አመለካከት ግለሰብ ተኮር ፍረጃ ሊባል ይችላል። በ1973 እ.ኤ.አ በውጤት አሰጣጥ ላይ በተሰራ ጥናት በጣም ሳቢ ስም ያላቸው ተማሪዎች ሳቢ ስም ከሌላቸው ተማሪዎች የተሻለ ማርክ ተሰጥቷቸዋል። በሌላ በኩል ግለሰባዊ ፍረጃ አካላዊ አቋምን በማየት የሚደረግ ነው። በዚህም እ.ኤ.አ በ1967 በተሰራ አንድ ጥናት ቆንጆ መልክና ቁመና ያላቸው ሰዎች ከሌላቸው ሰዎች ይልቅ ደስተኞች፣ ጥሩዎችና ጎበዝ ተወዳዳሪዎች ናቸው የሚል የተሳሳተ ፍረጃ ተሰጥቷቸው ነበር።

ሁለተኛው ፍረጃ የቡድን ተኮር ፍረጃ ሲሆን እንዲህ አይነቱ ፍረጃ የሚመነጨው አንድ ግለሰብ የሆነ ቡድን አባል በመሆኑ ምክንያት የተነሳ የሚኖር የተዛባ አመለካከት ነው። ይህም በአብዛኛው ከጭፍን ጥላቻ ጋር የመመሳሰል ሁኔታ አለው። ካዝና ብራል የተባሉ ተመራማሪ እ.ኤ.አ በ1933 በብሄርተኝነት ላይ ጥናት ለማድረግ መላ ዘይደው ነበር። በዚህም ለጥናቱ ተሳታፊዎች የተለያዩ የብሄር ቡድኖችን ለአብነትም አሜሪካውያንና አይሁዶችን እንዲሁም 84 የስብእና መገለጫ ቃላቶችን አቅርበውላቸው ነበር። ከዚህ በኋላ የጥናቱ ተሳታፊዎች አምስት ወይም ስደስት የስብእና መገለጫ ቃላቶችን ለየብሄሮቹ እንዲሰጡና እንዲገልፁ ተነገራቸው።

ይህ ጥናት በወቅቱ ያሳየው እነዚህ ተሳታፊዎች በተወሰኑ ብሄሮች ላይ ጭፍን የሆነ ፍረጃ ወይም ጥላቻ እንዳለባቸው ነበር። ይኸው ጥናት እ.ኤ.አ በ1951 እና በ1967 ሲደገም ፍረጃውና ጥላቻው በፊት ከነበረው ቀንሶ ታይቷል።

ጭፍን ጥላቻ ወይም /prejudice/ የጭፍን ፍረጃ ወይም /stereotype/ ፅንፍ ወይም ጥግ ነው። ከላይ በተቀመጡት የአመለካከት ክፍሎች መሰረት ጭፍን ፈረጃ አስተሳሰባዊ፣ ጭፍን ጥላቻ ስሜታዊ፣ እንዲሁም አግላይነት ባህሪያዊ ይሆናል። የጭፍን ጥላቻ ስሜት የሚያድግና የሚጎለብት ነው። እንደ እውቁ የማህበረሰብ ሥነ-ልቦና ባለሙያ ጎርደን አልፖርት ይህ የጭፍን ጥላቻ እድገት በአምስት ደረጃዎች ይከፈላል።

አንደኛው አጉል ቀልድ ወይም የጥላቻ ንግግር ነው። አጉል ቀልድ ወይም የጥላቻ ንግግር ስለ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን በፌዝ፣ በቀልድ፣ በስላቅ፣ በሃሜት ወይም በማሾፍ የሚደረግ አሉታዊ ንግግር ነው። ለምሳሌ አጥንት የሚሰብር ንግግር ተናገረኝ እንደሚባለው አይነት ንግግርና በብሄር ወይም በአካል ጉዳት ላይ የተመሰረተ ቀልድን ጨምሮ ማለት ነው። ይህ ሁኔታ እንደቀልድ ስለሚቆጠር በግለሰቡ ወይም በቡድኑ ላይ ምንም አይነት ጉዳት እንደማያመጣ ይቆጠራል። ነገር ግን እንዲህ አይነቱ ንግግር የሰዎችን ስብእና ከመንካትም አልፎ በራስ መተማመንን የሚያወርድና ስለራስ የሚኖር ምስልን ዝቅ የሚያደርግ ነው።

ሁለተኛው መነጠል ወይም መለየት ነው። ይህ የጭፍን ጥላቻ እድገት በአንድ ቡድን ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በሌላ ቡድን ከሚገኙ ጋር ይለያሉ ወይም ይነጠላሉ እንደማለት ነው። በዚህ ጊዜ አደጋው የበዛ ይሆናል። ሌሎች ከቡድናቸው ውጪ ያሉ ቡድኖችን ወይም ሰዎችን የመፍራት ዝንባሌ ያሳያሉ። ለምሳሌ መጤ ጠል ወይም /xenophobia/ ይከሰታል። ይህም መገለልን ያስከትላል።

ሶስተኛው አግላይነት ነው። አግላይነት አንድ ቡድን ሌላውን ቡድን እኩልነት በማሳጣት፣ ፍትህ በመንፈግና በመሳሰሉት መንገዶች ይገለፃል። ይኸውም የተለያዩ አገልግሎቶችን በመንፈግ፣ በመከልከል እንዲሁም እኩል አገልግሎት እንዳያገኙ ማድረግን ይጨምራል። በዚህም የተገለለ ቡድን ስራ፣ ትምህርት፣ ህክምናና ሌሎች አገልግሎቶችን እንዳያገኙ ክልከላ ይደረግባቸዋል። በዚህ የአግላይነት ዘውግ ስር የሥልጣን ተዋረድን በመጠቀም የሚደረግ አግላይነት ሲሆን ይህም እውቀትን፣ እድሜን ወይም ፆታንና ባህሪን መሰረት በማድረግ የተወሰኑ ቡድኖች እንዲገለሉ የሚደረግበት ነው።

አራተኛው አካላዊ ጥቃት ሲሆን በአብዛኛው የጥላቻ ጥቃት በመባል ይታወቃል። በዚህም የተወሰኑ የቡድን አባላትን ለይቶ ማጥቃት፣ ንበረታቸውን ማቃጠል ወይም ግለሰቦቹን በመንጋ ማጥቃትና ጅምላ ጭፍጨፋ ማድረግን ያጠቃልላል።

አምስተኛውና የመጨረሻው የጭፍን ጥላቻ እድገት አይነት ጭፍጨፋ ማካሄድ ሲሆን የዘር ማጥፋት፣ የብሄር ማፅዳትንና የመሳሰሉትን ያካትታል። ጎርደን አልፖርት እንደሚገልፀው ጭፍን ጥላቻ በተሳሳተ መንገድ በተወሰኑ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች የሆነ ቡድን አባል በመሆናቸው ብቻ እነርሱ ላይ ያነጣጠረ ተለዋዋጭና ተጣጣፊ የሆነ ጥቅል መገለጫ ነው። እዚህ ጋር ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ግን ጭፍን ጥላቻ እንዴት ሊኖር ቻለ? የሚለው ነው።

ስለ ጭፍን ጥላቻ መኖርና አለመኖር ጥናት የማያስፈልገው ቢሆንም በዚህ ጉዳይ ዙሪያ በርካታ ጥናቶች ተሰርተዋል። ለምሳሌ አሮንሰንና ኦሽሮው ጃን ኦልዌት የምትባል አስተማሪን አሳትፈው ተማሪዎቿን ቡናማ የአይን ቀለም ያላቸው ሰማያዊ የአይን ቀለም ካላቸው ልጆች የተሻለ ጎበዝ ናቸው ብላ እንድትነግርላቸው ካደረጉ በኋላ በውጤቱ ሰማያዊ የአይን ቀለም ያላቸው ልጆች ቡናማ የአይን ቀለም ካላቸው ልጆች ያነሰ ውጤት ማስመዝገብ ጀምረው ነበር። ምክንያቱም ቡናማ የአይን ቀለም ያላቸው ልጆች ይህ ንግግር ከተነገራቸው በኋላ አግልለዋቸው ስለነበር ነው።

በአብዛኛው ጭፍን ጥላቻ እንዴት ለብዙ ጊዜ በውስጣችን ይቆያል የሚል ጥያቄ ይነሳል። በመሰረቱ ጭፍን ጥላቻ ሳይናወጥ ለብዙ ጊዜ መቆየት የሚችል ነው። ይህም ማለት አንድ ጊዜ በውስጣችን ካለ በነበረበት ሁኔታ ለብዙ ጊዜ ይቆያል ማለት ነው። ምክንያቱም አብዛኛዎቹ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሰዎች ስለ ጭፍን ፍረጃ የነበሩ እውነታዎችን ከሌሎቹ ይልቅ በተሻለ ያስታውሳሉ። ጭፍን ፍረጃ ያልተለመዱ ወይም ወጣ ያሉ ሁኔታዎችን ስለሚያደርግ አንድ ጊዜ በጣም ከፍ ካለ ለማውረድ ከባድ ይሆናል።

ሌላው ነገሮችን እውነት አድርጎ መቀበል ነው። ሰዎች ብዙውን ጊዜ ለተደረገባቸው ፍረጃና ጥላቻ በምላሹ እነርሱም ያደርጉታል። ይህ ጥላቻን በጥላቻ የመመለስ ሂደት ጥላቻን ይበልጥ ያባብሰዋል እንጂ አይቀንሰውም። የሆነው ሆኖ ጭፍን ጥላቻን በተመለከተ ምሁራን የተለያዩ አስተያየቶችን ይሰነዝራሉ። ከነዚህም ውስጥ ሁለቱ ይጠቀሳሉ።

> **አንደኛው የምሁራን ወገን ጭፍን ጥላቻ በተፈጥሮ አብሮን የሚወለድ ነው ሲል ሌላኛው ወገን ደግሞ ጭፍን ጥላቻ ከማህረሰብ ግንባታ ጋር የሚመጣ እንጂ በተፈጥሮ የሚገኝ አይደለም ሲል ይሞግታል። ይህ ክርክር ጭፍን ጥላቻን ማስወገድ እንችላለን ወይስ አንችልም የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ መነሻ የሚሆን ነው**

አንደኛው የምሁራን ወገን ጭፍን ጥላቻ በተፈጥሮ አብሮን የሚወለድ ነው ሲል ሌላኛው ወገን ደግሞ ጭፍን ጥላቻ ከማህረሰብ ግንባታ ጋር የሚመጣ እንጂ በተፈጥሮ የሚገኝ አይደለም ሲል ይሞግታል። ይህ ክርክር ጭፍን ጥላቻን ማስወገድ እንችላለን ወይስ አንችልም የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ መነሻ የሚሆን ነው። በዚህም ላይ እንደተጠቀሰው ጭፍን ጥላቻ በተፈጥሮ የሚመጣ ነገር ከሆነ ማስወገድ ከባድ ነው የሚለውን ምላሽ ሲሰጥ በማህረሰብ ግንባታ ወቅት የሚመጣ ከሆነ ደግሞ የማህረሰቡን አተያይ በተለያየ መንገድ በመቀየር ማስወገድ ይቻላል ወደሚለው መደምደሚያ ይወስደናል።

**ከላይ የተቀመጡትን ክርክሮች በመውሰድ ሥነ ልቦናዊ አስተያየቶች እንዲህ ይላሉ፡-**

ቀደም ብሎ እንደተቀመጠው በተፈጥሮም ይሁን በማህበረሰብ የመጣን ጭፍን ጥላቻ በቀላሉ ለማስወገድ በጣም አስቸጋሪና ከባድ ነው። የሚያስቸግርበት አንዱ ምክንያት ጭፍን ጥላቻ አስተሳሰባዊና ስሜታዊ ክስተት በመሆኑ ነው። እናም ጭፍን ጥላቻ ከዚህ የሚፈልቅ አመለካከት ነው። አመለካከት ደግሞ በውስጡ በርካታ ነገሮችን ያቅፋል። አመለካከት ካለን እውቀትና ልምድ የተነሳ ይመጣል። ይህም የምናየውን ብቻ እንድንረዳ ያደርገናል። ሌላው አመለካከት ሌሎች ከሚሰጡን ጥሩ ወይም መጥፎ አስተያየት ጋር ይገናኛል። ይህም ማለት ሌሎች ሰዎች ያላቸው አመለካከት እኛ ካለን አመላካከት ጋር ከተመሳሰለና ያንን የምንጋራ ከሆነ ለነዛ ሰዎች ወይም ቡድኖች ያለን አመለካከት የተለየ እንዲሆን ያነሳሳናል።

በሌላ በኩል ደግሞ አመለካከት ስለራሳችን ያለንን ዋጋ ከፍ እንዲል የማድረግ ስራ ይሰራል። ይህም የሆነ አይነት አመለካከትን ማዳበር ለራሳችን የሚኖረንን ዋጋ ከፍ እንዳርጋለን፤ በመጨረሻም አመለካከት ራሳችንን ካላስፈላጊ ትችት የመከላከል ሥራ ይሰራል። በዚህም ጭፍን ጥላቻ ያለምንም በቂ ምክንያት በሌሎች የተገለሉ ቡድኖች ላይ የበላይነትን የማሳየት ዝንባሌ እንዲይዝ ያደርጋል።

እውቁ የሥነ- ልቦና ምሁር ሲግመንድ ፍሮይድ እንደሚለው ሰዎች ጠበኝነታቸውንና ፍርሃታቸውን በትክክለኛው ምክንያት ላይ ንዴታቸውን ከመገለፅ ይልቅ በሌላ ነገር ላይ ያስወጡታል። በሌላ በኩል በዚህ የፍርሃት ጠበኝነት አዙሪት ውስጥ መግባታቸው ሰዎች ፍርሃታቸውንና ጠበኝነታቸውን እንደምክንያትና ውጤት ይጠቀሙበታል። ይህም ማለት ፍርሃት ለጠበኝነት መንስኤ፤ እንዲሁም ጠበኝነት እንደገና ፍርሃትን ይወልዳል።

ሌላው ጭፍን ጥላቻን ከውስጣችን እንዳይወገድ ከባድ ከሚያደርጉ ሥነ - ልቦናዊ መላምቶች የታችፌልና ተርነር ማህበረሰብ ማንነት መላ ምት ነው። ይህ ማለት ሰዎች በተፈጥሮ ለራሳቸው መልካም ገፅታ ለመገንባት ይታገላሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ ማህበራዊ ማንነት ሰዎችን ቡድን ውስጥና ከቡድን ውጪ በሚል በመከፋፈል ይገለፃል። ይህ ማህበራዊ ማንነትን የመገንባት ሂደት ጭፍን ጥላቻ እንዲፈጠር ያደርጋል።

ሰዎች ለራሳቸው መልካም ግምትን በመገንባት ሂደት ውስጥ ሁለት አይነት ገፅታዎች ይኖራሉ። አንደኛው የግላዊ ማንነትን መገንባት ሲሆን ሌላኛው ማህበራዊ ማንትን መገንባት ነው። በሌላ በኩል አዶርኖ የተባለ ተመራማሪ በበኩሉ ጭፍን ጥላቻን ሊፈጥር የሚችል ማግነናዊ ስብዕና አለ ብሎ ይከራከራል። ይህ የስብዕና አይነት ዝቅተኛ የማህበረሰብ ክፍሎች ወይም ቡድኖችን የመናቅና ዝቅ አድርጎ የመመልከት እንዲሁም ከፍ ያሉ ማህበረሰቦችን የማጉላትና ለእነሱ የማጎብደድ የስብዕና አይነት ሲሆን ይህ አይነት ስብዕና ያላቸው ሰዎች እጅግ ግትርና የማይተጣጠፉ ናቸው ይላል።

አዶርኖ እንደሚለው ይህ የስብዕና አይነት ከአስተዳደግ ችግርና ከማህበረሰብ ጫና የሚመጣ ነው። ይህም ማለት በአስተዳደግ ወቅት ቤተሰቦቻቸው በጣም ወግ አጥባቂ፣ ሃይለኛና ከፍተኛ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ልጆች በወላጆቻቸው ላይ እልህና ቁጭት ውስጥ ይገባሉ። ነገር ግን በወቅቱ ስለማያወጡት ተደብቆ ይቆይና ኋላ ላይ በነዚህ ዝቅተኛ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ያወጡታል። ዋናው ጥያቄ ጭፍን ጥላቻን ለመቀነስ ምን ይደረግ? የሚለው ነው።

ከዚህ በፊት ጭፍን ጥላቻን ፈፅሞ ለማሰወገድ በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ አይተናል። ነገር ግን ማስወገድ እንችላለን ብለን ካሰብን የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ያስፈልጋል። በዘርፉ ምርምር ያደረጉ ሰዎችም የሚከተሉትን እርምጃዎች በመውሰድ ጭፍን ጥላቻን ማስወገድ እንችላለን ይላሉ።

1ኛ. በቡድን በተደራጁና ባልተደራጁ ወይም በሌላ ቡድን ውስጥ ባሉ መካከል ምንም አይነት የተወዳዳሪነት መንፈስ እንዳይኖር በማድረግና እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ።

2ኛ. በሁለቱም የቡድን አባላት የሚሰራና መሳካት የሚችል የጋራ ዓላማ ማቀድና ለዛም በእኩልነት እንዲሰሩ ማድረግ።

ከላይ የተጠቀሱት መንገዶች ጭፍን ጥላቻን ማስወገድ የሚችሉ ቢሆንም በተለያዩ ሀገራት እስካሁን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ባይቻልም በመቀነሱ ረገድ ግን መልካም ውጤት ተመዝግቧል። በተለይ የጋራ ዓላማ ላይ መስራት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ተሰምሮበታል። በዚህም ከተለያዩ የቡድን አባላት የመጡ ሰዎችን በመቀየጥና በጋራ ለሚመዘን ውጤት እንዲሰሩ በማድረግ ከፍተኛ ለውጥ አምጥቷል።

# ሙዳራባህ የኢንቨስትመንት ሒሳብ

## ከ67 - 99 በመቶ ትርፍ የሚጋሩበት



## የሙዳራባህ ኢንቨስትመንት ሒሳብ ንቅናቄ ከየካቲት 8 - ሚያዝያ 7 ቀን 2015 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሲቢኢ ኑር ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት የተቀማጭ ሒሳብ አገልግሎቶች አንዱ የሆነውን ሙዳራባህ የኢንቨስትመንት ሒሳብ የሚያስተዋውቅ የንቅናቄ መርሃ ግብር ከየካቲት 8 እስከ ሚያዝያ 7 ቀን 2015 ዓ.ም እያካሄደ መሆኑን ስንገልፅ በደስታ ነው።

በሙዳራባህ ኢንቨስትመንት ሒሳብ አገልግሎት የገንዘብ፡ ዕውቀት፡ ጉልበት እና ጊዜ አስተዋፅኦዎች ተቀናጅተው የትብብር ኢንቨስትመንት ይካሄዳል። ገንዘብ አቅራቢው የተቀማጭ ሒሳቡ ባለቤት ሲሆን፡ ገንዘቡን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችለውን የዕውቀት፡ የጉልበት እና የጊዜ አስተዋፅኦ የሚያደርገው ደግሞ ባንኩ ይሆናል፡፡

በዚህ መሠረት ፡ ደንበኞች በሙዳራባህ የኢንቨስትመንት ሒሳብ የቆጠቡትን ገንዘብ ባንኩ በማንኛውም አዋጭ በሆነ እና በሸሪዓ በተፈቀደ የሥራ ዘርፍ ላይ አውሎ፡ ከሚገኘው ትርፍ ሁለቱም አስቀድመው በተዋዋሉት የትርፍ ክፍፍል ቀመር መሠረት ትርፍ የሚጋሩ ይሆናል።

ባንካችን አገልግሎቶቹን በሙዳራባህ የኢንቨስትመንት ሒሳብ እና በሙዳራባህ የጊዜ ገደብ ኢንቨስትመንት ሒሳብ እየሰጠ ይገኛል።

- ይምጡና ይጎብኙን!
- የሙዳራባህ የኢንቨስትመንት ሒሳብ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ይሆኑ !
- በሁሉም የባንካችን ቅርንጫፎች በሙዳራባህ መርህ የተዘጋጁ በርካታ ሙዳራባህ የቁጠባ ኢንቨስትመንት ሒሳቦችን አቅርበንልዎታል።

### የትርፍ ክፍፍል ድርሻ መጠን

| ሙዳራባህ የቁጠባ ኢንቨስትመንት ሒሳብ | የደንበኞች የትርፍ ክፍፍል ድርሻ % | የባንኩ የትርፍ ክፍፍል ድርሻ % |
|---|---|---|
| ሙዳራባህ መደበኛ የኢንቨስትመንት ሒሳብ | 67 | 33 |
| ሙዳራባህ የሴቶች የኢንቨስትመንትሒሳብ | 73 | 27 |
| ሙዳራባህ ኒካህ የኢንቨስትመንት ሒሳብ | 70 | 30 |
| ሙዳራባህ ዒድ የኢንቨስትመንት ሒሳብ | 70 | 30 |
| ሙዳራባህ የትምህርት የኢንቨስትመንት ሒሳብ | 70 | 30 |
| ሙዳራባህ የወጣቶች የኢንቨስትመንት ሒሳብ | 70 | 30 |
| ሙዳራባህ የታዳጊዎች የኢንቨስትመንት ሒሳብ | 70 | 30 |
| ሙዳራባህ ለበይክ የኢንቨስትመንት ሒሳብ | 70 | 30 |
| ሙዳራባህ ቀዲም የኢንቨስትመንት ሒሳብ | 67 - 70 | 33-30 |
| ሙዳራባህ የውጭ የሐዋላ የኢንቨስትመንት ሒሳብ | 99 | 1 |
| ሙዳራባህ ሪህላ የኢንቨስትመንት ሒሳብ | 67 | 33 |

ሲቢኢ ኑር
CBE NOOR

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopia

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## አፈጻጸሙ እየተሻሻለ የመጣው
## ባለ 20 ወለሉ የትራንስፖርት ዘርፍ ዋና መስሪያ ቤት ሕንፃ ግንባታ

መላኩ ኤሮሴ

አዲስ አበባ ከተማ የትናንት ታሪካዊነቷን ጠብቃ፣ ዛሬ ለነዋሪዎቿ ምቹ እንድትሆን፣ ነገ ደግሞ ከዛሬ የተሻለች ምቹና ውብ ከተማ ለማድረግ በከተማዋ ቢሊዮን ብሮች የተመደቡላቸው የበርካታ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ እየተካሄደ ይገኛል። ከፕሮጀክቶቹ መካከል የአንዳንዶቹ ግንባታ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፤ ከእነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል አብርሆት ቤተመጽሐፍት፣ የአንድነት የመኪና ማቆሚያ ፓርክ፣ የመስቀል አደባባይ ፕሮጀክት፣ የአንድነት፣ የእንጦጦ የወዳጅነትና የእንጦጦ ፓርኮች ይጠቀሳሉ፡፡

ከእነዚህ ፕሮጀክቶች አንዳንዶቹ በከተማዋ አስተዳደር የተገነቡ ናቸው። የከተማ አስተዳደሩ አሁንም ሌሎች ግዙፍ ፕሮጀክቶችን እየገነባ ይገኛል። ከእነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል አንዳንዶቹ የተጠናቀቁ ሲሆን ግንባታቸው እየተካሄደ ያለ ፕሮጀክቶችም ብዙ ናቸው።

የከተማ አስተዳደሩ ያልተጠናቀቁትን ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ እና ለአገልግሎት እንዲበቁ ለማስቻል ርብርብ እየተደረገ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት በግንባታ ላይ ከሚገኙት ትላልቅ ፕሮጀክቶች መካከል የከተማዋ የትራንስፖርት ዘርፍ ዋና መስሪያ ቤት፣ ዓድዋ ሙዚየም፣ የአመራር አካዳሚ፣ የየካ መኪና ማቆሚያ፣ የግብርና ምርቶች ማዕከላት፣ የኢንዱስትሪ ማዕከል፣ የአዲስ አፍሪካ ኤግዚቢሽን እና ኮንቬንሽን ማዕከል፣ የለሚ ኩራ ፓርክ ፕሮጀክቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የዛሬው የመሠረተ ልማት አምዳችን የትራንስፖርት ዘርፍ ዋና መስሪያ ቤት ግንባታ ዙሪያ ላይ የሚያጠነጥን ይሆናል። በትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽሕፈት ቤት ባለቤትነት እየተገነባ ያለው ይህ የትራንስፖርት ዘርፍ ዋና መስሪያ ቤት መገኛ መገናኛ አካባቢ እየተገነባ ነው። በ4 ሺህ 300 ካሬ ሜትር ላይ እየተገነባ የሚገኘው መስሪያ ቤቱ፤ ከ1 ነጥብ 575 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ የሚጠይቅ ሲሆን፣ ግንባታው ሲጠናቀቅ አምስት ቢሮዎችን በጋራ እንዲይዝ ታስቧል፡፡

በትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽሕፈት ቤት የትራንስፖርት ዘርፍ ዋና መስሪያ ቤት የባለቤት ተወካይ ኢንጂነር ታደለ ደንደና እንደሚሉት፤ ፕሮጀክቱ ከመሬት በታች ሦስት ወለል፣ ከመሬት በላይ ደግሞ 20 ወለሎች ይኖሩታል። ግንባታው ሲጠናቀቅ መስሪያ ቤቱ የከተማ አስተዳደሩን የትራንስፖርት ዘርፍ ቢሮዎችን አቅፎ ይይዛል። መስሪያ ቤቱ ለሕዝብ ትራንስፖርት ባለስልጣን፣ ለአሽከርካሪዎች እና የተፈቀደላቸው ተሽከርካሪዎች ማረጋገጫ ባለስልጣን፣ ለአዲስ አበባ መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ እና ለትራንስፖርት ፕሮግራም አስተዳደር ቢሮ አገልግሎት ይውላል፡፡

ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ለ3ሺህ የሴክተር ባለስልጣን ሠራተኞች ቢሮዎች፣ ጂምናዚየም፣ ስፓ፣ ለሕፃናት ማቆያ ቦታ፣ ለትራንስፖርት ዘርፍ ሙዚየም፣ ለምስል ማሳያዎች፣ ለሕዝብ ምግብ ቤት እና ለሠራተኛ ካፊቴሪያ እንደሚኖሩት የጠቆሙት ኢንጂነር ታደለ፤ የመሬት ወለልን ጨምሮ ወደ ታች ያሉት ወለሎች 210 ተሽከርካሪዎችን በአንድ ጊዜ ማቆም እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡

እንደ ኢንጂነር ታደለ ማብራሪያ፤ መስሪያ ቤቱ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የሚገነባ ሲሆን፤ የተለያዩ አገልግሎቶች መስጫዎችንም ያካትታል።ለመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና እርዳታ መስጫ፣ ዲጂታል ቤተመጽሐፍት ለእያንዳንዱ ሴክተር ቢሮ፣ ስድስት ትናንሽ መሰብሰቢያ አዳራሾች እና አራት የስልጠና ማዕከላት፣ አንድ መካከለኛ የኮምፒዩተር ማዕከል እና ለአምስት ሴክተር መስሪያ ቤቶች የጋራ ቦታ ይኖሩታል፡፡



የሕንፃ ፕሮጀክቱ ምድር ውስጥ ሦስት ከምድር በላይ 20 ወለሎች እንዲኖሩት ተደርጎ እየተገነባ ነው፤ ግንባታው አሁን 12ኛ ወለል ላይ ደርሷል፤

በአሁኑ ወቅት ከትራንስፖርት ጋር ተያያዥነት ያለው አንድ ጉዳይ ለማስፈጸም የተለያዩ የትራንስፖርት ዘርፍ ቢሮዎች መመላለስ የግድ እንደሆነ የሚጠቅሱት እንጂነር ታደለ፤ አንድ ጉዳይ ለማስጨረስ የተለያዩ ቢሮዎች መመላለስ እና ጉዳይ ማስፈጸም ብዙ ቀናትን ሊወስድ እንደሚችል ጠቁመዋል። እየተገነባ ያለው የዘርፉ ሕንፃ ሲጠናቀቅ ይህን የደንበኞች እንግልት ማስቀረት እና ትክክለኛ አገልግሎት መስጠት እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡

ሕንፃው የደንበኞችን እንግልት ከማስቀረት ባሻገር ኢኮኖሚያዊ ፋይዳውም ከፍ ያለ መሆኑን የሚጠቁሙት ኢንጂነር ታደለ፤ በአሁኑ ወቅት አብዛኞቹ ተቋማት ቢሮዎችን ተከራይተው አገል ግሎት እንደሚሰጡ ተናግረዋል፤ ግንባታው ሲጠናቀቅ ለኪራይ የሚውለውን ወጪ ለሌሎች አገልግሎቶች ማዋል እንደሚቻልም ተናግረዋል፡፡

ቢሮዎቹ በአንድ ላይ መሰብሰባቸው ለመንግሥት ሌላ ራሱን የቻለ ጥቅም እንደሚያስገኝም ይገልጻሉ። ሕዝቡ አገልግሎቶችን በአንድ ቦታ ማግኘት መቻሉ የሕዝብን እርካታ ከፍ እንደሚያደርገው ኢንጂነር ታደለ ጠቁመዋል፡፡

እንደ ኢንጂነር ታደለ ማብራሪያ፤ የፕሮጀክቱ ግንባታ በ2012 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን፣ ይጠናቀቃል ተብሎ ከታሰበው ጊዜ በላይ ፈጅቷል።ፕሮጀክቱ በተለያዩ ምክንያቶች ተጓትቷል። የፕሮጀክቱ ግንባታ ሲጀመር የዲዛይን እና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ በባለቤትነት ሲያስገነባ የነበረ ሲሆን፤ በ2012 ዓ.ም ትላልቅ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤት ሲቋቋም እና ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ የሆኑ ፕሮጀክቶችን የሜጋ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤት በባለቤትነት እንዲያስገነባ አቅጣጫ መቀመጡን ተከትሎ ወደ ጽሕፈት ቤቱ ተሸጋግሯል፡፡

ጽሕፈት ቤቱ ፕሮጀክቱን በባለቤትነት ለማስገ ንባት ሲወስደው ከነችግሩ ነው ያሉት ኢንጂነር ታደለ፤ ከችግሮቹ መካከል በዲዛይን እና ስፔሲፊኬሽን ላይ የነበረው የአለመጣጣም ችግር አንዱ ነው ይላሉ። ይህንን ችግር ለመፍታት አራት ወር አካባቢ እንደወሰደ ይገልጻሉ።

እርሳቸው እንዳሉት፤ የዲዛይን እና ስፔሲፊኬሽን ችግር ከተፈታ በኋላም ሥራው አልጋ በአልጋ አልሆነም። እንደገና ሌላ ችግር አጋጥሟል። የግንባታ ዕቃዎች ዋጋ መናር ትልቁ ችግር ሆነ። በዋጋ መናር ምክንያት ኮንትራክተሩ የዋጋ ማሻሻያ እንዲደረግ ሀሳብ አቀረበ። ሀሳብ በማቅረብ ብቻ አላቆመም፤ ግንባታውንም አቆመ። ይህ ችግርም የከተማው ካቢኔ ባስተላለፈው ውሳኔ ተፈታ። ግንባታውም ከተወሰነ ቆይታ በኋላ ዳግም ሊጀምር ችሏል፡፡

ፕሮጀክቱ ለሦስተኛ ጊዜ ችግር አጋጥሞት በቅርቡ ግንባታው ተቋርጦም ነበር። በዋጋ ንረትና የውጭ ምንዛሬ እየጨመረ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ ለሦስተኛ ጊዜ ተቋርጦ ግንባታው እንደገና ከተጀመረ በኋላ አሁን ሥራው ከበፊቱ በተሻለ ፍጥነት እየተሠራ ነው። ኮንትራክተሩም ዳግም ግንባታውን ላለማቆም ቃል ገብቷል፡፡

እንደ ኢንጂነር ታደለ ማብራሪያ፤ በተለያዩ ወቅቶች ካጋጠሙት ተደጋጋሚ ችግሮች ተላቆ ፕሮጀክቱ በአሁኑ ወቅት በፍጥነት እየተገነባ ነው።54 ነጥብ 38 በመቶ ላይ ደርሷል። በአሁኑ ወቅት የ12ኛ ወለል ግንባታ በመካሄድ ላይ ይገኛል። እስከ ሐምሌ ድረስ የመዋቅሩ (ስትራክቸራል) ሥራ ያልቃል።ሙሉ በሙሉ የማጠናቀቂያውን ሥራ ጭምር ግን በቀጣይ አንድ ዓመት ተኩል ውስጥ ለማጠናቀቅ እቅድ ተይዟል። ከበላይ አመራር ጀምሮ በየደረጃ ያለው አመራር ለፕሮጀክቱ ድጋፍ እና ክትትል እየተደረገለት ነው፡፡

ፕሮጀክቱ ሜጋ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ባለቤትነት የሚገነባ እንደመሆኑ በቴክኖሎጂ የታገዘ የግንባታ ሥራ እየተሠራ መሆኑን የሚጠቁሙት ኢንጂነር ታደለ ደንደና፤ በፕሮጀክቱ ላይ የሚሳተፉ ሠራተኞች ልምድ፣ እውቀትና ሙያ እንዲቀስሙ ትልቅ ዕድል እየፈጠረላቸው መሆኑን አስታውቀዋል። ሠራተኞቹ ስልጠናዎችንም እንዲያገኙ እየተደረገ በመሆኑ በቀጣይ የሙያ ባለቤት የሚያደርጋቸው መሆኑን ነው ያመለከቱት፡፡

ይሁን እንጂ አሁንም የሲሚንቶ እጥረት ለፕሮጀክቱ እንቅፋት መሆኑን ቀጥሏል የሚሉት ኢንጂነር ታደለ፣ ችግሩ ሥራዎችን በተያዘው እቅድ መሠረት ለማከናወን እንቅፋት እየሆነ ይገኛል ይላሉ። አንድ ወለል በ15 ቀን ለመሙላት እቅድ ተይዞ እንደነበር አስታውሰው፣ በሲሚንቶ እጥረት ምክንያት በ30 ቀን ለመሙላት እየታሰበ መሆኑን አንስተዋል።

መንግሥት ለፕሮጀክቶቹ ሲሚንቶ ለማቅረብ የሚያደርገውን ጥረት በማጠናከር ግንባታው እንዲፋጠን ሊያደርግ ይገባል ሲሉ አስታውቀው፣ ሲሚንቶ የማይቀርብ ከሆነ ፕሮጀክቱ ተጨማሪ ጊዜ እና ተጨማሪ ሀብት ሊጠይቅ እንደሚችል ጠቁመዋል። ሲሚንቶ አምራች ፋብሪካዎችን ማገዝ የሚያስፈልግ ከሆነም አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጎ በብዛት እንዲያመርቱ እና በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለው ክፍተት እንዲጠብ ሊደረግ ይገባል ይላሉ፡፡

የሲሚንቶ ችግር የምርት እጥረት ብቻ እንዳልሆነም ጠቅሰው፣ የሲሚንቶ ዋጋ እንዲንር ብሎም የሲሚንቶ እጥረት እንዲከሰት የሚያደርጉ ደላሎች መኖራቸውን ጠቁመዋል። ደላሎችን ከገበያው ለማስወጣት አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቱን የማማከር ሥራ የኢትዮጵያ ኮንስት



ራክሽን ዲዛይን፣ ሱፐርቪዥን ሥራዎች ኮርፖሬሽን በማከናወን ላይ ነው። ኢንጂነር እናውጋው አለማየሁ አማካሪ ተቋሙ የመደባቸው የፕሮጀክቱ ተቆጣጣሪ መሐንዲስ ናቸው። ኢንጂነሩ ሥራው ሁለት ሦስት ጊዜ በመቋረጡ እና በተለያዩ ችግሮች ምክንያት መዘግየት ያጋጠመ ቢሆንም፣ በአሁኑ ወቅት ፕሮጀክቱ በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ነው። በተለይም ካለፉት ሁለት ወራት ወዲህ መልካም የሚባል እንቅስቃሴ እየታየ ነው ይላሉ።

ጥራት ላይ አንዳች ችግር እንዳይፈጠር ከፍተኛ ጥንቃቄ እየተደረገ ነው የሚሉት ኢንጂነር እናውጋው፤ ከብረት እና ሲሚንቶ ጋር የሚገናኙ እያንዳንዱ ዕቃዎች በገቡ ቁጥር ምርመራ እየተደረገ ጥቅም ላይ እንደሚውል አስታውቀዋል። በግንባታ ዘርፍ ሥራ ላይ ጫና የሚያሳድሩ የተለያዩ ውጫዊ ነገሮች እንደተጠበቁ ሆነው ፕሮጀክቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያሳየ ባለው መሻሻል መሠረት በአንድ ዓመት ተኩል ውስጥ ሊጠናቀቅ እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡

ፕሮጀክቱን በተያዘለት የጊዜ ገደብ ለማጠናቀቅ ባለቤት ተቋሙ፣ ኮንትራክተሩ እና አማካሪው በጋራ ርብርብ እያደረጉ ናቸው የሚሉት ኢንጂነር እናውጋው፤ በባለድርሻ አካላት መካከል ያለው መናበብ ፕሮጀክቱ ከነበረበት ችግር ወጥቶ ግንባታው በፍጥነት እንዲከናወን እያስቻለ ነው ብለዋል። ተቋማቸውን ወክለው እንደአማካሪ ተቋም ኮንትራክተሩን እና ባለቤት ተቋሙን የማማከር እና ሥራው ጥራቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን ከፍተኛ ርብርብ እያደረጉ መሆናቸውን ጠቁመዋል። ሦስቱ ተቋማት እጅና ጓንት ሆነው እየሠሩ ነው። በራሳቸው አቅም የሚፈቱ ችግሮች ወዲያው እንዲፈቱ በማድረግ እና ከአቅማቸው በላይ የሆኑ ችግሮች ደግሞ በበላይ አመራሩ እንዲፈቱ እያደረጉ መሆናቸውን ነው የጠቆሙት፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የክፉ ቀን ደራሽነታችንን በተግባር እናስመስክር!

የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት (ኢትዮጵያ ፣ ኬንያ ፣ ኤርትራ፣ ጅቡቲ እና ሶማሊያ ዑጋንዳ) በተደጋጋሚ በድርቅ ከሚጠቁ አካባቢዎች ዋነኞቹ ናቸው። ዓመታት እየጠበቀ የሚከሰተው ይኸው ድርቅ በሀገራቱ ከተንሰራፋው ድህነት ጋር ተዳምሮ በሕዝቦቻቸው ላይ ከፍተኛ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጥፋት እያስከተለ ይገኛል።

አንድም በሀገራቱ ያለው የግብርናው ዘርፍ በዝናብ ውሃ ላይ ጥገኛ መሆኑ ፣ ከዚያም ባለፈ ዘርፉ አሁንም ኋላቀር በሆነ የአመራረት ሥርዓት የሚመራ ፤ እራሱን ለማዘመን የሚያስችል አቅምና መነቃቃት ያጣ መሆኑ ፤ ለሀገራቱ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" ሆኖባቸው ድርቅ በተከሰተ ቁጥር እጆቻቸውን ለልመና እንዲዘረጉ ዳርጓቸዋል።

ይህ እውነታ ዛሬም ቢሆን ለሀገራቱ ትልቅ ፈተና ሆኗል። ዓለም አቀፍ ተቋማት እያወጡት ባለው መረጃ መሰረት ፤ በአካባቢው ለአምስት ተከታታይ የዝናብ ወቅቶች ዝናብ ባለመጣሉ ምክንያት በአሁኑ ወቅት በእነዚህ ሀገራት ወደ 60 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ ለከፍተኛ የምግብ እህል እጥረት ተጋልጧል ። ፈጥኖ እርዳታ ሊደርስለት ካልተቻለም ለከፋ አደጋ ይጋለጣል።

ችግሩ በኛም ሀገር (በኢትዮጵያ) በስፋት የታየ ሲሆን፤ በኦሮሚያ ፣ በሶማሊ እና በደቡብ ክልሎች በሚገኙ የተለያዩ ዞኖች ተከስቶ ጥፋት እያስከተለ ይገኛል ። ከችግሩ ጋር በተያያዘ 11 ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች በምግብ እህል እጥረት ውስጥ ናቸው። 23 ሚሊዮን ዜጎች ደግሞ ለድርቅ ተጋላጭ እንዲሁም ተጎጂ በሆኑ አካባቢዎች ይኖራሉ። ከዚህም ባለፈ ስድስት ነጥብ 85 ሚሊዮን የቤት እንስሳት በድርቁ ምክንያት ሞተዋል።

ይሄን ችግር ለመቋቋም የሚያስችሉ ርምጃዎች የተጀመሩ እና ድጋፍም እየተደረገ ሲሆን፤ ለአብነትም በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን የተከሰተውን ድርቅ እና እያስከተለ ያለውን አደጋ ለመከላከል መላው ሕዝብ በስፋት እየተንቀሳቀሰና ተስፋ ሰጪ ውጤቶች እየተመዘገበ ነው። በአካባቢው ያለውን ነዋሪ / አርብቶ አደር ሕይወት ለመታደግ የሚደረጉ የነፍስ አድን ስራዎች ውጤታማ በመሆናቸው እስካሁን በሰው ሕይወት ላይ ጥፋት አልደረሰም ።

የአርብቶ አደሩን የሕይወት መሰረት የሆኑ የቤት እንስሳቱን ለመታደግ የሚደረጉ ጥረቶች በሚፈለገው ደረጃ ስኬታማ ባይሆኑም ፤ አሁንም እንስሳቱን ለመታደግ የሚደረጉ ርብርቦች የሚበረታቱና አርብቶ አደሩን ነገ ላይ መልሶ /ለማቋቋም ለሚደረግ ጥረት ትልቅ አቅም ሊሆን እንደሚችል ይታመናል ።

ይህ መልካም የመተባበርና ለወገን የመድረስ ከፍታን የሚያሳይ እንደመሆኑ አሁን ባለው ሁኔታም በደቡብ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን እንዲሁም በሶማሊ ክልል አብዛኞቹ ዞኖች ለተከሰተው ድርቅና እያስከተለ ላለው ችግር ለቦረና ዞን የተሰጠውን ያህል በቂ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። በተለይም ድርቁ በአካባቢው አርብቶአደር ሕይወት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጥፋት ለመታደግ የተሰሩት ሥራዎች መልካም ቢሆኑም፤ የቤት እንስሳቱን ከጥፋት ለመታደግ ፈጥኖ መንቀሳቀስ ይገባል።

በሀገር ውስጥ ሆነ በውጭ ያለውን ሕዝባችንን ጨምሮ ፣ ዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ በማስተባበር እንደሀገር የተደቀነብንን ይህንን ፈተና ለመሻገር የሚመለከታቸው አካላት ድርቁ በአካባቢው ባሉ ዜጎቻችን ላይ እያስከተለ ያለውን ጥፋት የሚያሳዩ መረጃዎችን ፈጥኖ በማሰራጨት ችግሩ ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኝ በትጋት መስራት ይጠበቅባቸዋል።

የፌዴራልም ሆነ የክልል መንግሥታት በበኩላቸው ችግሩ ከሁሉም በላይ የራሳችን በመሆኑ፤ የችግሩን ስፋትና ጥልቀት በአግባቡ በማስገንዘብ ዜጎቻችን በያሉበት ባላቸው አቅም በችግር ውስጥ ላሉ ወገኖቻቸው የሚችሉትን የሚያበረክቱበትን ምቹ ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል።

ዜጎችም "ለወገን ደራሽ ወገን ነው" በሚለው ሀገራዊ ብሂል በመነሳት ፣ መጠኑንና ብዛቱን ሳይሆን ለወገን መድረስን ማዕከል በማድረግ በሚቻላቸው ሁሉ የአቅማቸውን በማበርከት ለወገኖቻቸው የክፉ ቀን ደራሽነታቸውን በተጨባጭ ማስመስከር ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ የማንንም ውትወታ ባለመጠበቅ ለወገን ደራሽ ወገን መሆናችንን በተግባር ማሳየት ይኖርባቸዋል!

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

## ‹‹ኢትዮጵያ ውሃን ማዕከል...

ከ7ኛው ገጽ የዞረ

ወደአፍሪካ ይመለስ በሚል መወሰኑ የሚታወስ ነው። ይሁንና ግብጾች ድሉ የእኛ ነው ሲሉ ነበር። ምክንያት ሲባሉ ደግሞ የተባበሩት መንግሥታት የሕዳሴን ጉዳይ አጀንዳ እንዲያደርገው ችለናል ሲሉ ይመልሳሉ። ግብጾች ቢችሉ በሁሉም ቦታ ጉዳዩ አጀንዳ እንዲሆን ማድረግ ነው። የትኛውም ዲፕሎማት ይሁን በማንኛውም ደረጃ ያለ ባለሥልጣን ሀገራቸው ሲመጣ ኢትዮጵያ በሕዳሴ ግድቡ ላይ እያደረገች ያለው ሁኔታ ሳይነገረው አይወጣም። ይህን የሚያደርጉበት ዋናው ነገር በፖለቲካ አጀንዳ ካልሆነ በስተቀር በሕግና በሥርዓት ውሃውን መቆጣጠር ስለማይችሉ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የግብፆች አካሄድ ቀደም ብሎ የተቀመጠውን ‹‹ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ‹‹ የሚለውን መርህ የሚጻረር አይሆንም?**

**ዶክተር በለጠ፡-** ኢትዮጵያ በአባይ ግድብ ላይ ፍትሃዊ የሆነ አጠቃቀም እስከተጠቀምን ድረስ ሌላ ነገር አያስፈልግም ስትል ነበር። ግብጻውያኑ ግን አይሆንም በሚል ነው እስከ ተባበሩት መንግሥታት ድረስ ጉዳዩን የወሰዱት። ኢትዮጵያ ግን የአፍሪካ ህብረት ‹‹የአፍሪካን ችግር በአፍሪካ መፍታት›› የሚል መርህ ስላለው በእዛ መሰረት እንፍታ ስትል ነው የተናገረችው። ግብጾች በአረብ ሊግ ቋሚ አጀንዳ ይሁን ብለው እንዳስደረጉት አይነት የተባበሩት መንግሥታትን እንደፈለጉት መቆጣጠር ግን አልቻሉም፤ የአፍሪካ ህብረትም የሆነባቸው እንደዚያ ነው። ስለዚህ የአፍሪካ ህብረቱን መርህ ለማክበር ፍላጎታቸው የቀነሰ ነው።

በነገራችን ላይ ግብጻውያን በናይል ጉዳይ መርህም ሕግም የሚሉት ነገር የላቸውም። የትኛውንም ሕግም ሆነ መርህ ተከትለው መኖር አይፈልጉም። አንድ እና አንድ የሆነ ፍላጎታቸው ውሃውን ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥሮ መኖር ነው። መርህ ብቻ ሳይሆን ሳይንስን ራሱ መቀየር የሚፈልጉ ናቸው። በዓለም አቀፍ ጆርናል ላይ የሚታተም ጽሑፍን ለማስቀየር ድረስ የሚሄዱ ናቸው። ሌላው ቀርቶ ግድቡ የመሬት መንቀጥቀጥ ያስጋዋል የሚል ከእውነት የራቀ ሐሳብ እስከመሰንዘር የደረሱ ናቸው። ይህ እንዳልሆነ ደግሞ ራሳቸው የፈረሙት ሰነድ ተሰንዶ ተቀምጧል።

እንዲያውም የአስዋን ግድብ ካለው ጤናማ ኢንቫይሮንመንት በላይ የሕዳሴ ግድብ የተሰራበትም ቴክኖሎጂ ሆነ ያለበት ሁኔታ ከመሬት መንቀጥቀጥ አደጋዎች ነጻ መሆኑ በተጠናው የጥናት ውጤት ላይ ራሳቸው ግብጻውያኑ ፈርመዋል። ይህን መፈረማቸውን እያወቁ በግድቡ ላይ ችግር ለማስመዝገብ ሲሉ የተጣመመ ትንታኔ ሁሉ ሲጽፉ ይታያሉ።

**አዲስ ዘመን፡- በሀገራቱ መካከል ያለውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ያለው አማራጭ ምንድን ነው?**

**ዶክተር በለጠ፡-** ሁሌም የሚባለው ነው። ዘለቄታዊ መፍትሄ የሚሆነው ሀገራቱ በአንድነት ተቀምጠው ፍትሃዊና ምክንያታዊ የሆነ የመሬት ውሃ አጠቃቀም ሥርዓት ምን ይሁን ብለው መወሰን ነው። ቢቻላቸው ከዚያም በላይ ይህን የውሃ መከፋፈል ትተው በጋራ ውሃውን እንዴት እናልማው ብሎ መሥራት አዋጭ ነው። በተፈጥሮ እየመጣ ያለው የአየር ንብረት ለውጥ፣ የመሬት መከላት እና የተፋሰሱ አለመልማት እየፈጠረ ያለው ተጽዕኖ በጋራ መቀየር የምንችለው እንዴት ነው ብለው መምከር አለባቸው፤ ይህን ማድረግ ከቻሉ መፍትሄ ይመጣል።

ኢትዮጵያ ደጋግማ የምታነሳው ቢቻል የጋራ ኮሚሽን ኖሮን የጋራ ራዕይ፣ የጋራ ስትራቴጂ እና ዓላማ ቀርፀን ውሃውን በጋራ እናልማ የሚል ነው። ኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ ከናይል ቤዚን ኢንሼቲቭ ጋር በመሆን የጋራ ዘርፈ ብዙ ተግባር የሚል ቀርጸው ብዙ ታግላለች። የትብብር ማዕቀፉ እንዲፈረም ብዙ ዓመታት ተደራድራለች። ይህ ሁሉ ጥረት አጠቃላይ የተፋሰሱን ውሃ ፍትሃዊና ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ለተፋሰሱ ሀገራት ጥቅም ላይ እንዲውል ማስቻል ነው። ውሃ ደግሞ ለሰው ልጅ ኑሮ አስፈላጊ ነው። ሁሉም ሀገር ፍትሃዊና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ውሃውን መጠቀም አለበት። ትልቁ ችግር ግብጻውያን በዋናነት እዚህ ሐሳብ ላይ መድረስ አልቻሉም። ለዚህ ነው ኢትዮጵያ መግፋት ያለባት። ኢትዮጵያ አብዝታ ማልማት ስትጀምር ሁሉም ወዲህ ይመጣሉ። ከአስር ዓመታት በላይ በህዳሴው ግድብ ላይ ድርድር የተካሄደው ልማቱ ስለተጀመረ ነው። ልማቱ ባይጀመር ኖሮ እዚህ ሁሉ ድርድር እና የፖለቲካ ቁርጠኝነት ውስጥ አይገቡም ነበር። ምክንያቱም ኢትዮጵያ እስካልለማች ድረስ ውሃው ፈስሶ እነርሱ ዘንድ ይደርሳል። እንደ መርህ ውጤታማ የሚሆነው ፍትሃዊና ምክንያታዊ የአጠቃቀም ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ ነው። ይህን በድርድርና በሕግ ማምጣት ከተቻለ እሰየው ነው። ወደዚህ የማይመጡ ከሆነና ኢትዮጵያንም ውጤታማ የሚያደርገው እነርሱንም ወደ ፍትሃዊና ምክንያታዊ የአጠቃቀም አጀንዳ ውስጥ እንዲገቡ የሚደርጋቸው የኢትዮጵያ ጠንካራ ልማት ነው። አሁን ኢትዮጵያ ከህዳሴ ግድብ ባሻገር ሌሎች ልማቶቿን ማከናወን አለባት። የተጠኑ ጥናቶች አሉ። እነርሱን መተግበር አለባት። ለምሳሌ ባሮ አኮቦ ላይ የተጠና ጥናት አለ። ዓባይ ላይም ከላይ የተጠኑ ጥናቶች አሉ። ከዚህም ከፍ ያለና ሎሉችም አማራጮች እየታዩ ወደ ሌሎች ጠንካራ ልማት ውስጥ መግባት ይገባል። ግብጽን ወደ ሥርዓቱ ለማምጣት ከህዳሴ ግድብ በሻገር ማየት መጀመር አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት ሁለቱ ተርባይኖች በመሥራታቸው ብንጠቀምም የህዳሴ ግድብ ግንባታ ከተጀመረ 12 ዓመታት ተቆጥረዋል። መነሻው በአምስት ዓመት ውስጥ ይጠናቀቃል የሚል ነበር። በእርስዎ እይታ ይህን እንዴት ይረዱታል?**

**ዶክተር በለጠ፡-** እውነት ለመናገር ጊዜው አልበዛም። በመጀመሪያም እንደዚህ ዓይነት ትልቅ ልማት ሲጀመር የሚያነሳሳ ሃሳብ ይፈልጋል። ትልቅ ልማት ነውና 20 እና 30 ዓመት ይወስዳል ብለን ብንነሳ የመነሳሳት አቅማችን ደካማ ነው የሚሆነው። ስለዚህ በአጭር ጊዜ ታጥቀን በዘመቻ በአምስት ዓመት እንጨርሰዋለን ብሎ መነሳት የጋራ መነሳሻ አጀንዳ ይሆናል እንጂ እንደ አንድ ትልቅ ፕሮጀክት በአምስት ዓመት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ እናጠናቅቀዋለን ብሎ መነሳት ከባድ ነው። በጣም ከባድ ከመሆኑ የተነሳ ተሞክሮውም የለም።

በዓለማችን አሉ የምንላቸው ትልልቅ ግድቦች ስንወስድ እንዲያውም አሁን የህዳሴ ግድብ 90 ነጥብ 7 በመቶ መድረስ ዓመቱ በዛ የሚያስብል አይደለም። በዓለም የተገነቡ ትልልቅ ግድቦችም ስንመለከት ከ15 ዓመት ቀድሞ የተጠናቀቀ የለም። ስለዚህ እኛ ጥሩ እምርታ ላይ ነን። በፕሮግራማችን መሰረት በፈረንጆች አቆጣጠር 2024 ላይ ሙሉ ለሙሉ ግድቡን እናጠናቅቃለን። በእርግጥ የኤሌክትሮ መካኒካል ሥራው ብዙ ነገር የሚፈልግ ነው። አንድ ተርባይን ከማኑፋክቸሪንግ ወጥቶ፣ ሳይት ደርሶ ገጥሞና ሞክሮ ለመጨረስ ጥናቶች የሚያሳዩትና እኛም እያየን ያለነው ከ8 እስከ 9 ወር ይፈጃል። ስለዚህ 11 ስናደርጋቸው ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል።

ህዳሴውን በተመለከተም አንዱ ከሌላው የመቅደም ሁኔታ ሊኖር ይችላል። የሁለተኛው ተርባይን ስንገጥም የመጀመሪውን ከገጠምነው ጊዜ ያነሰ ነው። ሦስተኛው ሲገጠም ደግሞ የተሻለ ይሆናል። እንዲህ እያለ የሚፈጥንበት ሁኔታ አለ። በእርግጠኝነት ግን ሲቪል ሥራው በተባለው ጊዜ ይጠናቀቃል። ከአንድ አመት በኋላም ሙሌቱ ይጠናቀቃል። በሚቀጥለው ሃምሌ ወርም የተወሰነ እንሞላለን፤ እየሄድንም ያለነው በመርህም ነው። እዚህ ላይ ትልቁ ነገር ኢትዮጵያ በየትኛው ዓለም አቀፍ ተቋም አቤቱታ ቢቀርብባትም አቤቱታውን ያለፈችው መርህን ተከትላ በመሄዷ ነው። የሙሌት መርህ አስቀምጣለች፤ ለእነርሱም በሥምምነት አቅርባለች። በግልጽ ባይስማሙበትም ውስጣቸው ተስማምተውበት ተቀብለዋል፤ ኢትዮጵያ የምትሄደው ይህን ተከትላ ነው። ዓረብ ሊግ ላይ ራሱ ኢትዮጵያ ብቻዋን ተነጥላ ውሃው ሞላች የሚለው በራሱ አግባብ አይደለም።

ሁለተኛው ስለዚህ ግድብ ለየት ባለ መንገድ መረዳት የሚገባን በትይዩ እያለማ ነው። ለምሳሌ ወደኋላ ተመልሰን የሌሎች ሀገራትን ስንመለከት በዓለማችን ውስጥ እያስገባ ያለው አዲስ ልምድ ነው። አዲሱ ልምድ መሰል ግድቦች ወደ ምርት የሚሄዱት ሙሉ ግንባታቸውና የውሃ ሙሌታቸውን ጨርሰው ነው። ስለዚህ 10ም ሆነ 20 ዓመት የወሰዱት ያለምርት ነው። ህዳሴ ግድብ ግን ይህን እሳቤ ቀይሮታል። በመሆኑም የታቀደበት መንገድ ለዓለማችን ትልቅ ትምህርት ነው። ሦስተኛው ሁሌም የምናነሳው ለእኛ ትልቅ አቅም የሚሆን ነው። ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም መነሳሻ የሆነው በራስ አቅም መልማት ይቻላል የሚለው ነው። ካሰብንበትና ከተስማማንበት እርዳታ ላይ ያልተመሰረተና ትልልቅ ልማቶችን መሥራት ይቻላል። በመሆኑም ህዝብም መንግስትም ቁርጠኛ መሆን አለብን። በራስ አቅም ለመልማት ይህ ግድብ ማሳያ ነው።

በተፋሰሱ ሀገራት ስብሰባ ላይ ስንመለከት ሀገራት እየጠየቁ ነው። እኛም ልክ እንደ ኢትዮጵያ በራሳችን በጀት ማልማት አለብን እያሉ ነው። ትልቁ እዚህ ውስጥ ያስገባን የግብፆቹ አካሄድ ነው። የትኛውንም ፋይናንስ ድጋፍ የሚያደርገውን አካል ልትጎዱን ነው ወይ በሚል ስለሚከላከሉ ነው። አብዛኞቹ የናይል ተፋሰስ ሀገራት ልማታቸው የተገደበበት ምክንያት አንዱ ይህ ነው። ስለዚህ የህዳሴ ግድብ በዚህ ደረጃ መሠራት ለእኛም ለሌሎችም በራስ አቅም ተነሳስቶ በየደረጃው አቅምን ሳይገዳደር መስራት ያስችላል። እኛ 750 ሜጋ ዋት ኃይል እያመነጨን ግድብ መስራት ቀላል ነገር አይደለም። አሁን ካሉን ሁሉም ግድቦች ከጊቤ ሦስት በስተቀር በሁለቱ ተርባይኖች የሚመረተው ከሁሉም ይበልጣል። ስለዚህ እነዚህ እመርታዎች አሉን።

**አዲስ ዘመን፡- ለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ ከልብ ሳመሰግንዎ እወዳለሁ።**

**ዶክተር በለጠ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፋታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስለአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።



## ማጣት መንጣትን በምስጋና

መልካምሥራ አፈወርቅ

የዘንድሮን ነገር አልቻሉም። የኑሮ ውድነቱ ያንገዳግዳቸው ይዟል። ዛሬን እንደነገሩ ቢያልፉ ነገ ፈጥኖ ይተካል። ገበያው ከአቅማቸው በላይ ሆኗል። እንደ እጃቸው ልግዛ፣ ልሸምት ቢሉ አልሆነም። የጓዳ፣ የቤታቸው ችግር አላስተኛቸውም። ‹‹ሞላሁት›› ሲሉ ይጎድላል። ‹‹አገኘሁ›› ሲሉት ይጠፋል። ሆድ ይሉት ጣጣ ርሃብ ድካም አስከትሎ እያናወዛቸው ነው። ተጨንቀዋል።

ወይዘሮ ሙሉ ዲንቃ ዛሬ እንደትናንቱ አይደሉም። ዕድሜያቸው ገፍቷል። አቅማቸው ጠፍቷል። ቀድሞ ጉልበታቸው ሳለ ለስራ አይቦዝኑም። ከንግዳቸው ውለው፣ ከገበያው ሸምተው ይገባሉ። የዛኔ በወጉ ልጆቻችውን አሳድገው፣ ድረዋል፣ ኩለዋል። ትናንት ያለፉበት መንገድ አሁን ህልም ይመስላቸው ከያዘ ቆይቷል።

ዓመታትን የቆጠረው ህመማቸው ከብዷቸዋል። ‹‹ራሴን..›› ማለት ከጀመሩ ወዲህ ነገሮች ተቀይረዋል። ብዙ ለማውራት ፣ ርቆ ለመሄድ አልቻሉም። አንዳንዴ የውስጣቸው ችግር ቀናቸውን ይዞት ይውላል። ይህኔ ይጨነቃሉ፣ ያስባሉ፣ ጓዳቸው ከተራቆተ፣ እጃቸው ከነጣ ቆይቷል። አንዳች ማድረግ አልቻሉም። ራሳቸውን ደግፈው፣ አንገታቸውን ደፍተው ሲተክዙ ይውላሉ።

ወይዘሮዋ ውልደታቸው ከወሊሶ ነው። አዲስ አበባ የገቡት በአፍላ ዕድሜቻያቸው ነውና ቁንጅናቸው ብዙዎችን ያማልል ነበር። የዛኔ ገጠር ሳሉ ተድረው ሁለት ልጆች ወልደዋል። ሙሉ ውሎ አድሮ የሕይወት ለውጥ አሰኛቸው። የልጅነት ልባቸው ለመንገድ ፈጥኖ ተነሳ።

ርቀው መሄድ ፈለጉ። ከተማን ደግመው ደጋግመው እያሰቡ ነው። ሲባል እንደሰሙት በዚያ ስፍራ ሁሉ ነገር ይለያል። ጥሩ መልበስ፣ ጥሩ መብላት ፣ አምሮ መታየት፣ ድምቆ መዋብ ሁሉ። የማያውቁት አገር ናፈቃቸው። ገጠሩን ሲያዩት ፣ ሊኖሩበት ጠሉት። ከፍ አድርገው አለሙ። ጥቂት ቆይቶ ልባቸው ቀረት ሲል ተሰማቸው። ሚስጥሩን ያውቁታል። ደነገጡ፣ ልጆቻቸውን አስታወሱ።

ልጆች ይዞ በሰው ቤት እንግድነት አይሆንም። እያወጡ እያወረዱ። ከራሳቸው ተጨቃጨቁ። ቀናት ወስደው አሰቡ። ውስጣቸው ቀድሞ ካቀደው ሌላ አዲስ ነገር አላላቸውም። አዎ ! ብቻቸውን፣ ሌጣቸውን መሄድ አለባቸው። በቃ ወሰኑ። ይህን ሲወስኑ የእናትነት አንጀት አልተዋቸውም። ይፈትናቸው ያዘ። ልሂድ? ልቅር ? ሲሉ ከረሙ።

አንድ ቀን የከራሞታቸው ሚስጥር በቁርጥ ሃሳብ ተቋጨ። ይህ ስሜት ቢያሸንፍ እንደዋዛ ቤታቸውን ተዉት። ሁለት ልጆቻቸውን ስመው አገር ቀዬውን ለቀው ወጡ። አገር ቤት የተዋቸው ሁለት እንቦቃቅላዎች በድንገት ከእናታቸው ተለዩ።

ህፃናቱ ውስጣቸው እንደ እሳቸው የሆነ አይመስልም። ምናልባትም እናት ገበያ ሄደው ፣ እንደወትሮው አረፋፍደው ይመለሱ መስሏቸዋል። ሙሉ ወሰኑ፣ ልባቸውን አረጋጉ። በልጅነት ዕድሜያቸው የወለዷቸውን ልጆች አገርቤት አስቀምጠው አዲስአበባ ገቡ።

### አዲስ አበባ

የዛኔ የከተማ ሕይወት አልከበዳቸውም። ከሚሄዱበት አካባቢ የቅርቦቹን ጨምሮ በርከት ያለ ዘመድ አላቸው። ካሰቡት ሲደርሱ እንግድነታቸውን የሚሹ ሁሉ ስለእሳቸው መልካም ሆኑ። ቀድመው አዲስ አበባ የገቡ እህት ወንድሞቻቸው እንደብርቅ አይተው ተቀበሏቸው። ሙሉ ከገጠሩ ኑሮ የከተማው ሕይወት ተመቻቸው። ውበት ጨመሩ። ፈገግታቸው ደምቆ ፊታቸው ፈክቶ ታየ።

ወይዘሮ ሙሉ ኑሮን በአዲስ አበባ ቀጠሉ። ገጠር ያሉ ልጆቻቸው በሌሎች እጅ እያደጉ ነው። ለእነሱ ቤት ያፈራው አይጠፋም። ወተት ዳቦው ከማጀት፣ እሸት ጥንቅሹ ከማሳው ሞልቷል። የገጠሯ ጉብል አሁን ከተሜ ሊሆኑ ነው። የሰውን ባህርይ፣ የአካባቢውን ሁኔታ መልመድ ይዘዋል። ለመኖር ሕይወትን ለመምራት ደግሞ ከስራ ትግል ይዘዋል። ያሉበት አካባቢ ሮጦ ለማደር ፣ ሰርቶ ለመግባት ያመቻል። ሙሉ የልጅነት ዕድሜያቸው ለዚህ አላነሰም። ያሻቸውን ሰርተው ለማደር አገዛቸው።

ሕይወት በአዲስ አበባ እንደቀጠለ ነው። ሙሉና የልጅነት ዕድሜ ተግባብተዋል። በዘመድ እጅ ናቸውና የቸገራቸው የለም። ያገኙትን እየሰሩ፣ በሰሩት ልክ

ማጣት መንጣትን... ወደ ገጽ 17 ዞሯል

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን
Ethiopian Intellectual Property Authority

ማሳሰቢያ

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 320/1995 ከተሰጠው ስልጣንና ሃላፊነት መካከል፤ በኢትዮጵያ የአእምሯዊ ንብረት ህጎችንና ደንቦችን ስራ ላይ ማዋልና መከታተል ይገኝበታል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ ባለስልጣኑ የሚደርሱ መረጃዎችና ጥቆማዎች እንደሚያመለክቱት፤ በቅጂና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 410/1996 ስር የህግ ጥበቃ የተደረገላቸው የቅጅና ተዛማጅ መብቶች በተለይም የቴሌቪዥን ድራማዎች፣ ፊልሞችና ሌሎች ፕሮግራሞች በተለያዩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ተቀርፀው በኢንተርኔትና በማህበራዊ ሚዲያዎች በተለይም በዩቲዩብ እና ቴሌግራም ላይ እየተጫኑና ህገወጥ በሆነ መንገድ እየተሰራጩ እንደሚገኙ ለማወቅ ችለናል፡፡

ይህ ተግባርም ከላይ የተጠቀሰውን የሀገሪቱን የቅጅና ተዛማጅ መብቶች አዋጅን በቀጥታ የሚጥስ ከመሆኑ ባሻገር ከፍተኛ መዋዕለንዋይ በማፍሰስ የተለያዩ ይዘቶችን እያቀረቡ ለሚገኙ የመገናኛ ብዙሀን እና የፈጠራ መብት ባለሙያዎች የሚሰሩ የፕሮዳክሽን ኩባንያዎችና የስራ እድል በመፍጠር በስራቸው ለሚያስተዳድሯቸው ዜጎችም ዘርፈ ብዙ ጫና እያሳደረ ይገኛል፡፡

ይህን መሰል ድርጊት በሚፈጽሙ አካላት ላይ በአዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀፅ 34 እና 36 መሰረት ለደረሰ ቁሳዊ ጉዳት ካሳ የመክፈል፣ ሆነ ተብሎ የሚፈጸም የመብት ጥሰት ከ5 እስከ 10 ዓመት ፣ ከፍ ባለ ቸልተኝነት የተፈጸመ እንደሆነ ደግሞ ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እንደዚሁም በማሻሻያ አዋጁ 872/2007 መሰረት ለተፈጸመው ወንጀል የገንዘብ ቅጣት እንደሚያስከትል በህጉ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም በዚህ ህገወጥ ድርጊት ላይ የተሰማራችሁ ግለሰቦችና ድርጅቶች በአዋጁ ጥበቃ የተደረገላቸውን መብቶች መጣስ የፍትሐብሔርና የወንጀል ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል ተገንዝባችሁ ከዚህ ድርጊት በአስቸኳይ እንድትቆጠቡ ባለስልጣኑ ያሳስባል፡፡

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን

# ማጣት መንጣትን...

ይኖራሉ:: ስለነገው ተስፋቸው ብሩህ ነው:: መልክ ቁመናቸው ያምራል፣ ያስተዋሏቸው በርካቶችን ይማርካል::

### ሕይወት ከልጆች ጋር

ወይዘሮ ሙሉ ዓመታትን በአዲስ አበባ አሳለፉ፣ በትዳር ሕይወትም ልጆች ወልደው ሳሙ:: ልጆቻቸውን ለማሳደግ፣ ቤታቸውን ለመምራት ጠንክረው መስራት ነበራቸው:: የሚኖሩበት ቤት የቀበሌ በመሆኑ ለኪራይ አልተቸገሩም:: ሙሉ ስድስት ልጆች አላቸው:: እነሱን ለማሳደግ ደፋ ቀናውን ይዘዋል::

ኑሮ ቀላል አልሆነም:: የአቅማቸውን እየሮጡ፣ የእጃቸውን ያስገባሉ:: ስራቸው ከዕለት የማያልፍ አነስተኛ የንግድ ውሎ ነው:: እንዲያም ሆኖ ለጎጇቸው አላነሱም:: የትዳር ሕይወታቸው በጎ ቢሆንም ፈተና በዛበት:: ልጆቹ በወጉ ሳያድጉ፣ ከቁምነገር ሳይደርሱ ባለቤታቸው በሞት ተለዩ::

ለእማዋራዋ ይህ አጋጣሚ ቀላል የሚባል አልሆነም:: ያለ አጋር ልጆችን ማሳደግ፣ ቤተሰብን መምራት ይከብድ ነበር:: ሙሉ ገጠር ያሉትን ሁለት ልጆች ጨምሮ ቀሪዎቹን ያለአባት ሊያሳድጉ ግድ ሆነ:: ባለቤታቸው በሞት ሲለዩ ሸክሙ በእሳቸው ጫንቃ ወደቀ:: በአንድ እጅ የቆመው የቤት ምሰሶ ሲያጋድል፣ እሱን ሊያቃኑ መሮጥ ያዙ:: አንዳንዴ ጎጇቸው የሞላ በመሰላቸው ጊዜ በእፎይታ ጥቂት ያርፋሉ::

ጠንካራዋ ሙሉ እንዲህም እንዲያም እያሉ ሕይወትን ገፉ:: እንደ እናት ስለ ልጆቻቸው ነገ ያስባሉ፣ ይጨነቃሉ:: የዛሬው ልፋታቸው ዋጋ የሚኖረው እነሱ አድገው፣ ቁምነገር ሲደርሱ ነው:: ይህ እንዲሆን ውስጣቸው በምኞት ይሞላል፣ በተስፋ ነገን ያስባሉ::

ሙሉ እናትነታቸው ከተማ ላሉት ልጆች ብቻ አይደለም:: በልጅነት ገጠር ለተውዋቸው ሁለት ልጆችም ይጨነቃሉ:: ከቀናት በአንዱ ግን ከዚህ ስሜት በላይ የሆነ መከራ አገኛቸው:: ከሁለቱ የገጠር ልጆች አንደኛው መሞቱን አወቁ:: ልባቸው ክፉኛ ተሰበረ:: የእናትነት አንጀታቸው በብሶት ተንሰፈሰፈ::

ቀናት አለፉ:: ወራት ተተኩ:: ዓመታትም በሂደት ተፈራረቁ:: ጠንካራዋ ሙሉ የውስጣቸውን ኀዘን በልባቸው ይዘው ለሌሎቹ ልጆች መኖር ታገሉ:: ሕይወት እንደቀድሞው ቀጠለ:: ልጆች ማደግ ፣ መማር ጀመሩ:: ከፍ ያሉት ትዳር ይዘው ጎጆ ቀለሱ:: የእናት ሸክም በግማሽ ቀለለ:: በመጠኑ ‹‹እሰይ፣ እፎይ›› አሉ::

### ሴላው ፈተና

ዳግም የሙሉን ብርታት የሚገዳደር ክፉ አጋጣሚ ድንገት ተከሰተ:: አሁንም የመጣው ችግር አላለፋቸውም :: ገጠር የነበረው ሁለተኛ ልጅ መሞቱን ሰሙ:: ለእሳቸው ይህ መርዶ በእጅጉ ከባድ ነበር:: ፀፀት፣ ቁጭትና ተስፋ መቁረጥ በልባቸው ደምቆ ታተመ:: ሁሉም ስሜት በውስጣቸው ውሎ አድሮ ማንነታቸውን፣ አንገዳገደ::

ሙሉ ገጠር የተዋቸውን ሁለቱን ልጆች ካጡ በኋላ ውስጣቸው ናወዘ:: ምንነቱን በውል የማይለዩት ከባድ ስሜት ያስጨንቃቸው ያዘ:: ደጋግመው ‹‹ራሴን››ይላሉ:: ብዙዎች ቀርበው ይጠይቋቸዋል:: እሳቸው ህመማቸውን በቃላት ሊያስረዱ ይሞክራሉ:: እሳቸው የሚያማቸው ውስጥ ራሳቸውን እንጂ የተለመደው ራስ ምታት አለመሆኑን ይናገራሉ::

የሕይወት ትግሉ ቀጥሏል:: ፤ያለ አባት ያደጉት የሙሉ ልጆች የራሳቸውን ሕይወት ይዘዋል:: ሁሉም የሆነው በጠንካራዋ እናታቸው ብርታት ነው:: አሁን እናት አቅማቸው እየደከመ፣ ዕድሜያቸው እየገፋ ነው:: እንደወጉ ማረፍ፣ ጊዜ መውሰድ አለባቸው:: ሁሉም ነገር እንደታሰበው አልሆነም:: ከወይዘሮዋ ቤት ኀዘን አልወጣም:: በተለያዩ ጊዜያት ሶስት ልጆቻውን በሞት ተነጠቁ::

### ሕይወት ከድካም ጋር

የወይዘሮ ሙሉ የሕይወት ውጣ ውረድ ከእፎይታው አልደረሰም፤ አሁንም በልጆች ሞት እየተፈተነ ትግሉን ቀጥሏል:: ሙሉ በመጦሪያ ጊዜያቸው የልጅ ልጆች አሳዳጊ ሆነዋል:: ዛሬ እንደቀድሞ ሮጦ የሚያድር፣ ጉልበት የላቸውም:: አሁንም ልጅ ከማሳደግ፣ አርቀው ከማሰብ አልወጡም:: ከሚያሳድጓቸው ልጆች ገሚሶቹ እናት አባት የላቸውም:: ሁለቱንም በሞት የተነጠቁት በጠዋቱ ነው:: እነሱን አሳድጎ ቁምነገር ለማድረስ አቅም ያስፈልጋል፣ ገቢያቸው እንደቀድሞው አይደለም:: ‹‹ከእጅ ወደአፍ›› ነውና ኑሯቸው፣ ጓዳቸው ያሳስባል::

በሕይወት ያለው አንድ ልጃቸው የራሱ ልጆች አሉት:: የእሱን ልጆች ሳይቀር የሚንከባከቡት እንደአያት ብቻ አይደለም:: እንደእናት ጭምር ነው:: እንዲህ መሆኑ ለዕድሜ ጠገቧ ወይዘሮ ሕይወትን አከብዷል:: በጓዳቸው ሁሉ አይገኝም፣ ከማጀታቸው ይጎድላል፣ ከሞሰባቸው ይታጣል::

ወይዘሮ ሙሉ ያለፉበት የሕይወት መንገድ በከፋ ኀዘን የተሞላ ነው:: ሁሉን መለስ ብለው ሲያስቡ ውስጣቸው ይከፋል:: እየደጋገሙ ‹‹ምንዋጋአለው?›› ይላሉ:: ተስፋ ይቆርጣሉ፣ አንገታቸውን ደፍተው ያዝናሉ:: አሁን ደግሞ ኑሮው ተወደዷል:: ችግሩ ጠንቷል:: የጤፍ ዘይቱ ዋጋ ሽቅብ ንሯል:: የሽሮ በርበሬው ነገር አይቀመስም::

እሳቸውን ጨምሮ የልጅ ልጆቻቸው በልተው ማደር አለባቸው:: በየቀኑ የጎደለውን መሙላት ይከብዳል:: በእነ ወይዘሮ ሙሉ ቤት እንደፊቱ ከቁርስ እስከ እራት ምን ይሰራ? ምን ይበላ ? የሚባልበት አይደለም:: ሁሉ ነገር ይቸግራል:: ሁሉም ጉዳይ ያስጨንቃል:: ግን አሁንም ሕይወት በቤቱ ቀጥሏል:: መኖር ከተባለ ደግሞ እማወራዋም ከነቤተሰባቸው እየኖሩ ነው::

ወይዘሮ ሙሉ ጮክ ብሎ ማውራት፣ ደጋግሞ መናገር ያስጨንቃቸው ይዟል:: አሁንም ‹‹ራሴን ያመኛል›› ይላሉ:: ዛሬም ቀርበው ለሚጠይቋቸው የተለመደው ራስ ምታት እንዳልሆነ ያስረዳሉ:: ብቻ ‹‹ራሴን ያመኛል›› ይሉት ቃል ከአፋቸው አይጠፋም:: እንደምንም ከሀኪም ቀርበው ችግራቸውን ሊያስረዱ ሞክረዋል:: ደጋግመው ስላልታከሙ መፍትሄ አላገኙም::

አንዳንዴ ሙሉ ከቤታቸው ወጥተው ለመግባት መንገድ ይጠፋቸዋል:: ያሉበትን ለማስታወስ፣ በመጡበት ለመመለስ ይቸገራሉ:: ከሰፈር መውጣታቸውን እንጂ ወዴት እንደሚሄዱ የማያውቁበት ጊዜ ይበረከታል:: ይህ እውነት ስጋት ቢሆናቸው ከቤታቸው ርቀው አይሄዱም:: ይህ ህመማቸው በአንድ ወቅት ከአንድ ወር በላይ ራሳቸውን አስቶ ካልጋ አውሏቸው ነበር:: ዛሬ ቆመው በመሄዳቸው ፈጣሪን ያመሰግናሉ:: እንዲያም ሆኖ አሁንም ስጋቱ ከእሳቸው ጋር ቀጥሏል::

ሁለቱ የልጅ ልጆቻቸው የአንደኛው ሟች ልጃቸው ፍሬዎች ናቸው:: እነሱ እናት አባታቸውን ያጡት ገና በህፃንነታቸው ነው :: የዛኔ ይኖሩበት ከነበረው ጅማ ድረስ ተጉዘው ያመጧቸው አያታቸው ሙሉ ነበሩ:: ሁለቱ ልጆች ይማራሉ:: ትምህርት ውለው ሲመጡ ለአያታቸው የአቅማቸውን በማድረግ ያግዛሉ::

ወይዘሮ ሙሉ ዛሬ የዕድሜ መግፋት፣ ከኀዘን ተደርቦ እያንገላታቸው ነው:: ከአምስት ዓመታት በፊት የጀመራቸው የራስ ህመም ከበርካታ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች አግዷቸዋል:: አሁን አጠገባቸው ሁነኛ ሰው ከሌለ ከቤት መውጣት አይደፍሩም:: ደጋግሞ የሚያስጨንቃቸውን ህመም ደጋግመው ያስባሉ::

ወይዘሮ ሙሉን ያገኘኋቸው ልደታ አካባቢ ከተገነባው የምገባ ማዕከል ውስጥ ነበር:: ገና ሳያቸው የእናትነት ወዘናቸውን ወደድኩት:: ዛሬም ቆንጆ የሚባሉ ሴት ናቸው:: ሲያወሩ ቀስ እያሉ ነው:: ርጋታቸው አስደነቀኝ :: አረፍ እያሉ ያጫውቱኝ ያዙ:: የሚሉትን በጥንቃቄ እየሰማሁ ጥያቄ አቀረብኩላቸው::

‹‹በተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል›› የተገኙት እሳቸውን ለመሰሉ ወገኖች ግልጋሎት እንደሚሰጥ ሰምተው ነው:: ይህን ባወቁ ጊዜ ዓይናቸውን አላሹም:: ደስ እያላቸው የሚያውቋቸውን ሰዎች ተከትለው መጡ:: የሰሙት ሁሉ እንደተባለው ሆኖ አገኙት::

እማማ ሙሉ ባመጡት ባዶ ሰሀን የሚሰጣቸውን ትኩስ ምግብ ቋጥረው ይወስዳሉ:: ቤት ሲገቡ የልጅ ልጆቻቸው በናፍቆት ይጠብቋቸዋል:: የእጃቸውን አቅርበው፣ ቤት ካፈራው ዘንቀው በጋራ ማዕድ ይቆርሳሉ:: ሙሉ ትናንት የእሳቸው ዓለም ሌላ ነበር:: ሰርተው፣ ሸምተው፣ ነጭ ከጥቁር ጋግረው በልተዋል:: በአውደዓመት፣ በዝክሩ፣ ሙክት ከዶሮ አርደው ዘመድ ጎረቤት ጠርተዋል::

ዛሬ ደግሞ ታሪካቸው ተቀይሯል:: ልጆቻቸውን ሞት ነጥቆ፣ ጤናቸውን ህመም ይዞ፣ የሰው እንጀራን እያዩ ነው:: ወይዘሮዋ ትናንትና የሆነባቸውን አይረሱም:: ዛሬ በሕይወት ቆመው የሆነላቸውን ሲያስቡት ደግሞ ፈጣሪን አያማርሩም:: ደግመው ደጋገመው ‹‹ተመስገን›› ይላሉ:: ‹‹ተመስገን...››

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ፓግሪክ ኢትዮጵያ ሀ/የተ/የግ/ማ የሠሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A39887 የተሽከርካሪው ዓይነት አውቶሞቢል የሻንሲው ቁጥር LCN64ED55G0096493 ሞዴል LF6430 የሞተር ቁጥር LFB479Q*160800550* የሊብሬ ቁጥር 453979 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ6/7/2015 ዓ.ም አመልክተዋል:: ሠሌዳው ወድቆ ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

አመልካች ወ/ት ረድኤት ወንድወሰን አለነ ተጠሪ ወ/ሮ ፅጌረዳ ጥበቡ ገብረመስቀል ላይ የመጥፋት ውሳኔ ይሰጠኝ ሲሉ አመልክተዋል። ስለሆነም ተጠሪ ወ/ሮ ፅጌረዳ ጥበቡ ገብረመስቀል ያሉበትን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ መጋቢት 15/2015 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ አዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል::

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**
**የየካ ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም የቀበሌ 17/18 ካዛንችስ የሸማቾች ኃላ/የተ/ህ/ስ/ማህበር የሠሌዳ ቁጥር አአ 05-01-02432 የተሽከርካሪው ዓይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JALK6A13XE7104370 ሞዴል FSR6MF የሞተር ቁጥር 6HH1-479259 የሊብሬ ቁጥር 439856 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ29/6/2015 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አብረሃም ለማ ንጉሴ የሠሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A44389 የተሽከርካሪው ዓይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JAAKP34HXG7P36023 ሞዴል NPR6SN የሞተር ቁጥር 4HG1-544606 የሊብሬ ቁጥር 522160 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ22/6/2015 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ጉለሌ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ዮናስ ስዩም ኤፍሬም የሠሌዳ ቁጥር አአ 02-01-C05844 የተሽከርካሪ ዓይነት አውቶሞቢል የሻንሲው ቁጥር SALZA2BT2NH161913 ሞዴል LANDROVER P300E የሞተር ቁጥር *CJTR*21015C0110PT153 የሊብሬ ቁጥር 426720/426774 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪው ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ1/7/2015 ዓ.ም አመልክተዋል:: ሠሌዳው ወድቆ ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ዑመር መሀመድ አሊ የሠሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A56635 የተሽከርካሪው ዓይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JAAKP34H3H7P07769 ሞዴል NPR6SN የሞተር ቁጥር 4HG1-655260 የሊብሬ ቁጥር 586995 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ የፊት እና የኋላ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ1/7/2015 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ /ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ጀማል አብደልራህማን አህመድ የሠሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A06746 የተሽከርካሪው ዓይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር AHTFR29GX07039541 ሞዴል KUN25L-PRMSHW የሞተር ቁጥር 2KD-A329030 የሊብሬ ቁጥር 301007 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪው ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ1/7/2015 ዓ.ም አመልክተዋል:: ሠሌዳው ወድቆ ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ንፋስ ስልክ ላፍቶቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ፍቅርተ አለማየሁ ደረሱ የሠሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A69261 የተሽከርካሪው ዓይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲው ቁጥር NKR66E-7488521 ሞዴል NPR66E የሞተር ቁጥር 4HF1 439511 የሊብሬ ቁጥር 006786/254483 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ1/7/2015 ዓ.ም አመልክተዋል:: ሠሌዳው ወድቆ ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አራዳ ቅ/ጽ/ቤት**

በከሣሽ ወ/ሮ ቤተልሔም ደመቀ እና በተከሳሽ ወ/ሮ ሰሎሜ ሽፈራው መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉለሌ ምድብ 2ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እየታየ መሆኑን አውቀው መልስዎን በፅሁፍ ለ18/07/2015 ዓም. በ8፡00 ሰዓት እንዲያቀርቡ ካልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን አውቀው እንዲቀርቡ ታዟል::

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**
**የጉለሌ ምድብ ችሎት**

በከሣሽ ሀርቡ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አክ/ማ እና በተከሳሾች እነ ወ/ሪት አዜብ ጌታቸው መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 1ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ የጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልስዎን በጽሁፍ በ18/07/2015 ዓ.ም. በ4፡00 ሰዓት ችሎት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል::

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ/አመልካች ወ/ሮ ሊዲያ ፍቃዱ እና በተከሳሽ/ተጠሪ አቶ ቴዎድሮስ መሰለ ሰይፉ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቃቂ ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ20/07/2015 ዓ.ም. በ4፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል::

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

አመልካች ወ/ሮ ፈትያ ከድር በሽር እና ተጠሪ አቶ ሰክቲኒ ቢረዳ አርዋጋ መካከል ባለው የባልና ሚስት የፍች ክርክር ጉዳይ ተጠሪ በ18/07/2015 ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት 2ኛ ፍትሐብሔር ችሎት በ3፡00 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል::

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት**

# የኑሮ ሸክምን በሥራ ትጋት ያሸነፉ ተምሳሌት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የዕለቱ የስኬት እንግዳችን በአዲስ አበባና በክልል በተለያዩ የንግድና የኢንቨስትመንት መስኮች ተሰማርተው ውጤታማ የሆኑት የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢና ጊዳቦ የተቀናጀ ግብርና ድርጅት መስራችና ባለቤት አቶ ሰይድ ሀሰን ናቸው። አቶ ሰይድ ከቤተሰብ ጋር በጀመሩት የንግድ ሥራ በተለይም በግንባታ ግብዓት አቅራቢነት የረጅም ጊዜ ልምድ አላቸው። በሪልስቴት ዘርፍም እንዲሁ በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ቦታዎች ግንባታ እያከናወኑ ይገኛሉ። በግብርናው ዘርፍም ወደፊት እየመጡ ካሉ ባለሀብቶች መካከል አንዱ በመሆን አትክልትና ፍራፍሬዎችን እያለሙ ለገበያ ያቀርባሉ።

አቶ ሰይድ በደቡብ ክልል ጋሞ ጎፋ ዞን ትንሿ መንደር ቡልቄ ከተማ ተወልደው በሳውላ ከተማ ነው ያደጉት። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ጎፋ ቦትሬ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እስከ 10ኛ ክፍል ጎፋ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትለዋል። ከቤተሰብ ጋር ወደ አዲስ አበባ በማቅናት የ11ኛ እና 12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመድኃኒዓለም አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አጠናቀዋል።

የ11ኛ ክፍል ተማሪ እያሉ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ያቀኑት አቶ ሰይድ፣ የከፍተኛ ትምህርታቸውንም የተከታተሉት በእዚችው ከተማ ነው። ሕይወት ሁሌም አልጋ በአልጋ አይደለችምና የከፍተኛ ትምህርታቸውን ቢያጠናቀቁም በሕይወት መንገድ ውስጥ ብዙ ውጣ ውረዶችን አሳልፈዋል። ከዝቅታው ዝቅ ብለው ከትልቁ የገበያ ማዕከል መርካቶ ላይ የሸክም ሥራ እስከ መሥራት ደርሰዋል፣ ይህንንም በኩራት ይጠቅሱታል።

‹‹ሰው ከለፋና ጥረት ካደረገ ካሰበበት መድረሱ አይቀርም›› የሚሉት አቶ ሰይድ፣ ከብዙ ልፋትና ጥረት በኋላ ዛሬ ላይ ስለመድረሳቸው ይናገራሉ። በቀጣይ ብዙ የሚጠብቋቸው የቤት ሥራዎች እንዳሉባቸውም ለአፍታም አይዘነጉም።

እስከ ሁለተኛ ዲግሪ የተማሩት አቶ ሰይድ፣ የሕይወትን አባጣ ጎርባጣ ሸክም የበዛበት መንገድ ለማቅለል ቁልፉ ትምህርት ነው የሚል እምነት ነበራቸው። እናም ቀን ቀን መርካቶ ላይ የሸክም ሥራ እየሠሩ በማታው ክፍለ ጊዜ በማርኬቲንግ ትምህርት ከአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ እንዲሁም ከዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪ አግኝተዋል። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ በኤክስኪዩቲቭ ቢዝነስ አድሚንስትሬሽን የማስተርስ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል።

ወደ ሥራው ዓለም ሲገቡ ሀዋሳ ከተማ ኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ በተባለ ድርጅት በወር ስድስት መቶ ብር እየተከፈላቸው መሥራታቸውን ያስታውሳሉ። የስድስት መቶ ብር ደመወዝ ወር አላደርስ አላቸው። ሥራውን ትተው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱም ወንድሞቻቸው መርካቶ ውስጥ ተቀጥረው በመሥራት የተሻለ ገቢ ሲያገኙ ተመለከቱ።

ይህን ጊዜ ‹‹የኔ መማር ትርጉሙ ምንድን ነው?›› ሲሉ ራሳቸውን ጠየቁ። ለጥያቄያቸው ያገኙት መልስም ልክ ያልሆነ ቦታ ላይ መቆማቸውን አመለከታቸው። ከዚያም ወደ መርካቶ በማቅናት ወንድሞቻቸውን ተቀላቀሉ። አቶ ሰይድ ዛሬ የተለያዩ ድርጅቶችን ከመምራት ባለፈ በሁሉም ድርጅቶቻቸው 1000 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል።

ለትምህርት ካላቸው ትልቅ ስፍራ በተጨማሪ ለሥራ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጡት አቶ ሰይድ፣ የሥራ ክቡርነትን ከወላጅ እናታቸው እንደተማሩም ይናገራሉ። እሳቸው እንዳሉት፣ ወላጅ እናታቸው እጅግ ፈታኝ የሆነ የሕይወት መንገድን አሳልፈው ነው ያሳደጓቸው። እናታቸው እርሳቸውን ጨምሮ ስምንት ወንድሞችና እህቶቻቸውን ሲያሳድጉም የተለያዩ የንግድ ሥራዎችን ሲሠሩ እንደነበር ያስታውሳሉ። ይህን እያዩ ያደጉት አቶ ሰይድ፣ እሳቸውም የንግድ ሥራውን ለመቀላቀል ይወስናሉ። ደስ እያላቸው የተማሩት የማርኬቲንግ ትምህርትም እንደሚያግዛቸው በመተማመን በንግድ ሥራ ውጤታማ ለመሆን ቆርጠው ተነሱ።


አቶ ሰይድ ሀሰን

በወቅቱ መርካቶ ተቀጥረው የሚሠሩት ወንድሞቻቸው አስር ሺ ብር ያህል ማጠራቀም ችለው ነበር። አቶ ሰይድም ይህንኑ ብር ይዘው አነስተኛ ንግድ ሲጀምሩ ወንድሞቻቸው እዛው ተቀጥረው መሥራታቸውን ቀጠሉ። የንግድ ሥራቸውን በሕንፃ መሣሪያ ሽያጭ የጀመሩት አቶ ሰይድ፣ ይህም በግንባታ ዕቃዎች አቅራቢነት እንዲሰማሩ በር ከፍቶላቸዋል።

ዛሬ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተሰማርተው ውጤታማ መሆን ቢችሉም የመጀመሪያው ድርጅታቸው «ሀስት ኢንተርፕራይዝ» እንደሆነና የተለያዩ የብረታብረት ውጤቶችን በማምረት ቀዳሚው እንደሆነ ይናገራሉ። ቀጥሎም በሪልስቴት ዘርፍ ተሰማሩ፣ ዋይድ ቢዝነስ ግሩፕ ሪልስቴት የተሰኘው ድርጅታቸው በከተማዋ አራት ቦታዎች ላይ ቅይጥ (የተለያየ አገልግሎት) አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ግንባታዎችን እየገነባ ይገኛል። ለአብነትም አምስተኛ፣ ሀያት፣ ልደታና አምባሳደር የሚገኙ ግንባታዎችን ማንሳት ይቻላል።

ከግንባታ ግብዓቶች አቅራቢነትና ከሪልስቴት ግንባታ ሥራቸው በተጨማሪ ወደ ግብርናውም አዘነበሉ። አቶ ሰይድ ባያስታውሱም ገና ልጅ እያሉ አርሰው ስለሚያገኙት ምርትና በትራክተር ስለማረስ አብዝተው ይናገሩ እንደነበር ከወላጅ እናታቸው ሰምተዋል። የልጅነት ትዝታቸውን ጨምረው ትናንትናቸውን ከጋሞ ጎፋ የሚመዙት አቶ ሰይድ፣ ከልጅነት እስከ ዕውቀት በሚያውቋት ጋሞ ጎፋ ከእኩዮቻቸው ጋር በአካባቢው ባህልና ወግ መሠረት ተጫውተው አድገዋል። ጎበዝ ተማሪ እንደነበሩና አንደኛ ሆነው ሲያልፉም ያስታውሳሉ።

በሕይወታቸው ከሚቆጯቸው ነገሮች መካከል ኢትዮጵያ ያላትን ዘርፈ ብዙ እምቅ አቅም በልኩ መጠቀም ሳትችል መቅረቷ አልፎም ተርፎ ተረጂ መሆኗ ነበር። ለዚህም ነው ‹‹ከመውቀስ ይልቅ እኔም የድርሻዬን በመወጣት እልህና ቁጭቴን ልወጣ›› በሚል መነሻ ወደ ግብርናው ዘርፍ የገቡት። ግብርናን ሲያስቡም በቀጥታ የሄዱት ከትውልድ መንደራቸው ጎፋ ነው። እናትና አባታቸው ከወሎ ይሁኑ እንጂ እርሳቸው መነሻዬ፣ የትውልድ መንደሬ፣ የእኔነቴ መገለጫ ኩራቴ ብለው የሚያውቋትና የሚያምኗት የደቡብ ክልሏን ጎፋን ነው። ለግብርና ሥራቸውም ጎፋን ምርጫቸው ማድረጋቸውም ለዚሁ ነው።

የእርሻ መሬት ለመጠየቅ ወደ ደቡብ ክልል ያቀኑት አቶ ሰይድ፣ እስከ ደቡብ ኦሞ ድረስ ያለውን አካባቢ ተዘዋውረው ቃኝተዋል። በቅኝታቸውም ኢትዮጵያ ውስጥ ገና ያልተነኩ ለእርሻ ሥራ ምቹ የሆኑ በርካታ ቦታዎች ስለመኖራቸው አረጋግጠዋል። ከዚህም ባለፈ ኢትዮጵያ ይህን ያህል መሬትና ውሃ እያላት እርዳታ መጠበቋ ይበልጥ እንዲያስቆጫቸው ሆኗል።

ይሁንና አቶ ሰይድ፣ ጎፋ ላይ የእርሻ መሬት ማግኘት ባለመቻላቸው ሲዳማ ክልል ሄደው ከሀዋሳ 85 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ሎካ አባያ ወረዳ ቡኪቶ ቡራ ቀበሌ አባያ ሀይቅ አጠገብ 428 ሄክታር መሬት የእርሻ ቦታ አግኝተው ወደ ልማቱ ከገቡ ከአስር ዓመታት በላይ አስቆጥረዋል።

አካባቢው ምንም ዓይነት መሠረተ ልማት ያልነበረው በመሆኑ 30 ኪሎ ሜትር የሚደርስ መንገድ ከመሥራት ጀምሮ ድልድይ፣ ትምህርት ቤት፣ የጤና ተቋም፣ ፖሊስ ጣቢያና ቀበሌ ጭምር ገንብተዋል። የግብርና ሥራ እጅግ ፈታኝና አድካሚ ቢሆንም፣ ውጤቱ አስደሳችና እርካታን የሚያጎናጽፍ ነው የሚሉት አቶ ሰይድ፣ በርካታ ችግሮችን ተቋቁመው አካባቢውን በማልማት ጊዳቦ የተቀናጀ ግብርና ድርጅትን ዛሬ ላይ አድርሰዋል።

መጀመሪያ የዘሩት በቆሎ እንደነበርም ያስታውሳሉ። ይሁንና ቡቃያው በጥሩ እድገት ላይ እያለ ሙሉ ለሙሉ በፀሐይ ይወድምባቸዋል። ይህ ጉዳት ግን ሌላ መላ እንዲያስቡ አደረጋቸው። ከጊዳቦ ወንዝ ውሃ ጠልፈው ወደ እርሻቸው እንዲገባ ለማድረግ ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ በማውጣት ውሃውን መጠቀም የሚያስችል ግድብ ሠሩ። ግድቡን የሠሩት 1500 ሄክታር መሬት እንዲያለማ አስበው ቢሆንም፣ በቅድሚያ የተፈቀደላቸው 400 ሄክታር መሬት ነበር። እሱን ማልማት ሲችሉ ተጨማሪ 700 ሄክታር ማስፋፊያ አግኝተው በአሁኑ ወቅት ጊዳቦ የተቀናጀ የግብርና ድርጅት በእንድ ሺ 128 ሄክታር መሬት ላይ አትክልትና ፍራፍሬዎችን እያለማ ይገኛል።

ጊዳቦ የተቀናጀ የግብርና ድርጅት ብቻ 300 ለሚደርሱ የአካባቢው ነዋሪዎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ትኩረቱን በቋሚ ሰብሎች ላይ አድርጎ እየሠራ ይገኛል። ቀደም ሲል በአካባቢው ምንም ዓይነት የፍራፍሬ ዛፍ የማይታይበት የጊዳቦ አካባቢ፣ በአሁኑ ወቅት ግን ማህበረሰቡ የፍራፍሬ ችግኞችን በመትከል እያለማ ነው።

ወደ ሥራው ሲገቡ በአካባቢው ምንም ዓይነት መረጃ ያልነበራቸው አቶ ሰይድ፣ በዚህ የተነሳም ትልቅ ድካምና ከፍተኛ ኪሳራ ደርሶባቸውም ነበር። ይሁንና እልህ አስጨራሽ ከሆነ ከፍተኛ ጥረትና ትግል በኋላ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ መጠን ያለው አትክልትና ፍራፍሬ በማምረት ከአገር ውስጥ ገበያ ባለፈ ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ ጭምር እየተዘጋጁ ይገኛሉ።

‹‹ወደ ሥራው ስገባ በአካባቢው ምንም ዓይነት መነሻ ባለመኖሩ መሞከሪያ አይጥ ሆኜ ነበር›› ያሉት አቶ ሰይድ፣ አሁን ግን በርካታ ባለሀብቶች ገብተው እያለሙ እንደሆነና ጥሩ ቦታ እንደሆነም ተናግረዋል። በቋሚ ሰብል በተለይም ለኤክስፖርት ተፈላጊ በሆኑ ምርቶች ላይ ትኩረት አድርገው እያለሙ መሆናቸውንም ጠቅሰው፣ በውጭው ዓለም በከፍተኛ ደረጃ ተፈላጊ የሆኑትን አቦካዶ፣ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ፓፓያና ሌሎችንም ያለማሉ።

በ200 ሄክታር መሬት ላይ እያለሙ ያሉትን ሙዝ ለአገር ውስጥ ገበያ በተለይም በኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ሥር ለሚገኘው የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ወይም ለኢትፍሩት እንደሚያቀርቡም ገልጸው፣በሌላ 200 ሄክታር መሬት ላይ ማንጎና ብርቱካን እንዲሁም ፓፓያ እያለሙ መሆናቸውን ያብራራሉ።

ምርጥ ዘርን ተጠቅመው በ300 ሄክታር መሬት ላይ አቦካዶን የማልማት እቅድ እንዳላቸው፣ በአሁኑ ወቅትም በ50 ሄክታር መሬት ላይ የለማው አቦካዶ በቀጣይ ዓመት ለገበያ እንደሚቀርብም ይጠቁማሉ። ሙዙን በማንሳትም አቦካዶ እንደሚተክሉ ነው ያመለከቱት።

የግብርና ሥራ እጅግ አድካሚና ፈታኝ በመሆኑ ሁሉን ነገር ወስዶ ምርት መስጠት ቢችል እንኳ ምርቱን ለማውጣት ፈታኝ የሚሆንበት አጋጣሚ ይፈጠራል። ያም ቢሆን ግን ውጤቱ ያስደስተኛል የሚሉት አቶ ሰይድ፣ በተለይም አካባቢው ቀድሞ ከነበረው ገጽታ ወጥቶ አሁን ያለውን ገጽታ እንዲኖረው በማድረጋቸውና ምርት ከውስጡ መውጣት በመቻሉ ትልቅ እርካታ እንደሰጣቸው ነው ያጫወቱን።

ኢትዮጵያ ለግብርና ሥራም ይሁን ለሌላ ምቹ መሆኗን የጠቀሱት አቶ ሰይድ፣ በተለይም የግብርና ሥራ ገና ያልተነካ ነውና ልንሠራበት ይገባል ሲሉ ያስገነዝባሉ። ኬንያን ለአብነት በመጥቀስም ኬንያ በአቦካዶ ምርት ብቻ ኢትዮጵያ በአበባ ምርት የምታገኘውን ገቢ ያህል እንደምታገኝ ነው የሚናገሩት። ኢትዮጵያም አቦካዶን ለማምረት ከኬንያ ያላነሰ አቅም እንዳላትና የአየር ንብረቱም ለአቦካዶ የተመቸ መሆኑን ተናግረዋል። ለዚህም መንግሥት ለቡና የሰጠውን ትኩረት በተለይም ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ቢሰጥ ዘርፉ ለውጭ ምንዛሪ ገቢ ከፍተኛ ምንጭ መሆን ይችላል ብለዋል።

በከፍተኛ ፈተና ውስጥ አልፈው የግብርና ሥራቸውን ፍሬያማ ያደረጉት አቶ ሰይድ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ሰፊ ቦታ የማይፈልግና በአነስተኛ ቦታ ላይ ምርታማ መሆን የሚያስችል መሆኑን ይጠቁማሉ፣ አስፈላጊውን ግብዓት በማሟላት ሊሠራበት እንደሚገባም ይመክራሉ።

አቶ ሰይድ ለኢንቨስትመንት ሥራ የአገር ሰላም ወሳኝ መሆኑንም ይጠቁማሉ። በተለይም የእርሻ ሥራ ፍጹም ሰላም እንደሚፈልግ ተናግረው፣ አንዱ ነገር ከተነካ ሁሉም ነገር ይናጋል። ስለዚህም ተረጋግቶና በአንድ ልብ ሆኖ ለመሥራት ዘላቂ ሰላም ወሳኝ ነው ይላሉ።

በቀጣይም እርሻው ላይ ትኩረት አድርጎ የመሥራት ሰፊ ዕቅድ ያላቸው አቶ ሰይድ፣ ፍራፍሬዎችን ኤክስፖርት የማድረግ ዓላማ ይዘው እርሻውን በመስኖ፣ በግሪን ሃውስ ቴክኖሎጂ አጠናክሮ የመቀጠል ዕቅድ አላቸው። በምርምር ሥራዎችም እንዲሁ ከዲላ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን የምርምር ሥራ በመሥራት የተለያዩ ዝርያዎችን የማራባት፣ የማዳቀልና ምርጥ ዘሮችን በማዳበር ለአካባቢው አርሶ አደር ተደራሽ የማድረግ ዕቅድ አላቸው። ለሁሉም ግን ዋናው ነገር ሰላም መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያ ሰላም ትሁን በማለት ሀሳባቸውን ቋጭተዋል።

# ስፖርት





## አበበ ቢቂላ በነገው ሮም ማራቶን ሲዘከር

ብርሃን ፈይሳ

የሮም ማራቶን ነገ ይካሄዳል። በዚህ ውድድር ላይ ታዲያ አንድ ለየት ያለ ተወዳዳሪ ብቅ ይላል ተብሎ ይጠበቃል። 15 ሺ ያህል ሰዎች በሚሳተፉበት በዚህ ውድድር ላይ ኢትዮጵያዊው ኤርሚያስ አየለ ሙሉውን ማራቶን በባዶ እግሩ እንደሚሮጥ ተረጋግጧል። የ45 ዓመቱ የቀድሞው የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ዋና ዳይሬክተር ኤርሚያስ አየለ ይህንን የሚያደርገው ታላቁን የማራቶን ጀግና አበበ ቢቂላን ታሪክ በሰራባቸው የሮም ጎዳናዎች ላይ ለመዘከር በማሰብ ነው። ለዚህም ዝግጅቱን ማጠናቀቁን አስታውቋል። ውድድሩን ከ3፡30-4፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ያሰበው ኤርሚያስ በመቀጠልም በአቴንስ፣ ቶኪዮና ፓሪስ ማራቶኖች ላይ በተመሳሳይ በባዶ እግሩ በመሮጥ አበበ ቢቂላን እንደሚዘክር ገልጿል። ከዚህ ቀደም በዳይሬክተርነት ይመራው በነበረው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ሁለት ጊዜ እንደዚሁም በሃዋሳ ግማሽ ማራቶን አንድ ጊዜ በተመሳሳይ በባዶ እግሩ ተወዳድሯል። ሙሉ ማራቶን በባዶ እግሩ ለመሮጥ ሲዘጋጅ ግን ይህ የመጀመሪያው ነው።

አበበ ዘመን የማይሽረውን የሮም ኦሊምፒክ የማራቶን ገድል ከፈጸመ ከ63 ዓመት በኋላ ነገ በሚካሄደው የሮም ማራቶን ከኤርሚያስ በተጨማሪ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ መሰናዳታቸውም ተሰምቷል። አበበ ቢቂላ ከኢትዮጵያ ባሻገር የጥቁር ሕዝቦች የመጀመሪያውን የኦሊምፒክ ማራቶን የወርቅ ሜዳሊያ ካጠለቀ ከስድስት አስርት ዓመታት በኋላ የአገሩ ልጆች ልክ እንደሱ በባዶ እግራቸው አርባ ሁለት ኪሎ ሜትርን በመሮጥ ሊዘክሩት መዘጋጀታቸው የአለም መገናኛ ብዙሃንን ትኩረት ስቧል።

የጀግናውን አትሌት ገድል ለማስታወስና ሃሳቡን በተግባር ለማሳየት የተዘጋጀው ኤርሚያስ ‹‹አበበ ቢቂላ የስኬትን መንገድ




ኢትዮጵያዊው አትሌት ፍቅሬ በቀለ በነገው የሮም ማራቶን የዓምናውን ድል ለመድገም ተዘጋጅቷል፣

የቀየሰው ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካውያንም ጭምር ነው። እሱ የመጀመሪያውን የኦሊምፒክ ወርቅ ሜዳሊያ ያጠለቀ የመጀመሪያው ጥቁር አትሌት ነው። ይሁንና የሚገባውን ያህል ክብር አግኝቷል ብዬ አላስብም። ታሪኩ ሁሌም ስለሚደንቀኝም እሱ ታሪክ በሰራበት ስፍራ ላይ እሱ እንዳደረገው ባዶ እግሬን ለመሮጥ አሰብኩ። በዚህም እሱ ለኢትዮጵያ እና ለአትሌቲክስ ያበረከተውን አስተዋጽኦ ማሳየት እፈልጋለሁ›› በማለት ተናግሯል።

በእርግጥ በሮም ማራቶን ተካፋይ መሆን የታሪክ አካል መሆን ብቻም አይደለም። ስለሩጫው የሚያውቁ በሮም ማራቶን መሮጥ ‹‹ሙዚየም ውስጥ እንደመሮጥ ነው›› በማለት ብዙዎች ይናገራሉ። ምክንያቱ ደግሞ በጥንታዊቷና ውቧ ከተማ መሮጥ ከፉክክር ባለፈ በርካታ አስደሳች ጉዳዮች ስላሉት ነው። ለ41 ዓመታት በቆየው በዚህ ተወዳጅ ውድድርም በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ተካፍተለውበታል። ነገ በሚካሄደው የዘንድሮው ውድድርም 15ሺ ሯጮች የሚካፈሉበት ሲሆን፤ እንደቀደሙት ዓመታት በድምቀት ለማካሄድም ዝግጅቱ ተጠናቋል። ለሩጫው ድምቀት የሚሆኑት ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም የሩጫውን ቀን ብቻ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ።

በወንዶች በኩል ያለፈው ዓመት በዚሁ ውድድር ተካፍሎ የቦታውን ክብረወሰን በመስበር አሸናፊ የነበረው ኢትዮጵያዊው አትሌት ፍቅሬ በቀለ በዚህ ዓመትም ድሉን ለመድገም መዘጋጀቱ ተረጋግጧል። ከሁለት ደቂቃ በላይ በማሻሻል 2:06:48 ሰአት በመሮጥ የሮም ማራቶን ባለ ፈጣን ሰዓት አትሌት የሆነው ፍቅሬ በዚህ ውድድርም በተመሳሳይ አሸናፊነቱ ከእጁ ሊወጣ እንደማይችል ተገምቷል። በርካታ አፍሪካውያን አትሌቶች እንደሚሮጡ በታወቀበት በዚህ ውድድር ሰዓታቸው ከ2፡00 ሰዓት ከ 10 ደቂቃ በታች የሆኑ በርካቶች ሲሆኑ፤ ሶስት የሚሆኑት ደግሞ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ናቸው።

ህም ለፍቅሬ ፉክክሩን ፈታኝ ሊያደርግበት የሚችል እንደሆነ ቢታወቅም በዚያው ዓመት በሊዝበን ማራቶን ተካፍሎ ያለውን ፈጣን ሰዓት በ32 ሰከንዶች ማሻሻል መቻሉ አትሌቱ ያለውን አቅም የሚያስገነዝብ ነው። አትሌቱ ፍራንክፈርትን ጨምሮ በተለያዩ ማራቶኖች በመሮጥ ያዳበረውን የዓመታት ልምዱን በመጠቀም በተከታታይ አሸናፊ ሊሆን እንደሚችልም ቅድመ ግምቱን አግኝቷል። አትሌት አለሙ ገመቹ፣ ብርሃኑ ሃዩ እና ሲሳይ ፍቃዱ ደግሞ በኢትዮጵያ በኩል ተሳታፊ የሚሆኑና ለአሸናፊነትም ግምት ያገኙ አትሌቶች ናቸው።

ሴቶች በኩልም በተመሳሳይ አፍሪካውያን አትሌቶች በብዛት ተሳታፊዎች ሲሆኑ፤ አትሌት ዝናሽ ደበበ ደግሞ ለአሸናፊነቱ ተጠባቂ ሆናለች። በዚህ ውድድር በተለይ ሴት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ስኬታማ ናቸው። ዝናሽ እአአ በ2018 የጉዋንዡ ማራቶንን የፈጸመችበት 2፡27፡15 የሆነ ሰዓት የግሏ እንዲሁም በውድድሩ ከሚካፈሉ አትሌቶች ፈጣን ነው። ይህም አትሌቷ አሸናፊ ልትሆን ትችላለች በሚል እንድትገመት አድርጓል። ፎዚያ አሚድ እንዲሁም እጸገነት እገዘው የተባሉ ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም ተሳታፊዎች ናቸው።

በዚህ ውድድር በሁለቱም ጾታዎች ክብረወሰን የተያዘው በኢትዮጵያውያን አትሌቶች ሲሆን፤ በወንዶች ፍቅሬ በቀለ እንዲሁም በሴቶች መገርቱ አለሙ እአአ በ2019 የተመዘገበው 2:22:52 የሆነ ሰዓት ነው።


## የድሬዳዋ አስተዳደር

አመልካች ሚስራ አህመድ በቀበሌ 08 ክልል ውስጥ የሚገኘው የመኖሪያ ቤት ካርታ ቁጥሩ 3880 የሆነ ይዞታ ማረጋገጫ /ካርታ/ የጠፋብኝ ስለሆነ በምትኩ ይሰጠኝ ሲሉ አመልክተዋል። ይህንኑ ካርታ በዕዳ ይዤዋለሁ ወይም ወድቆ አግኝቼዋለሁ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ በወጣ በ30 ቀናት ውስጥ ይቅረብ።

**የድሬዳዋ አስተዳደር የይዞታ አገልግሎቶች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር**

### ማስታወቂያ

ሻጭ ፡ 1. ወ/ሮ ሸዋይነሽ ጣዕመ ገዛኸኝ ዜግነት ኢትዮጵያዊ የአቶ አለም ብርሃኔ ህጋዊ ወኪል
አድራሻ፡- አ/አ ክ/ከ ለሚኩራ ወረዳ 13 የቤት ቁ. አዲስ
ገዢ፡- ወ/ሮ ሀኒሳ ምነዋር ሽፋ ዜግነት ኢትዮጵያዊ
አድራሻ፡- አ/አ ክ/ከ ኮ/ቀራንዮ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር 2411
በአዲስ ከተማ ክ/ከ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር 107 የሚገኘው በቲን ቁጥር 0004021117 የንግድ ምዝገባ ቁጥር AA/AK/01/3/1/0000555/2006 የንግድ ፈቃድ ቁጥር 14/671/789222/2006 የንግድ ድርጅት ስለገዛኋቸው ተቃዋሚ ካለ በ15 ቀን ውስጥ አዲስ ከተማ ክ/ከ ወረዳ 01 የንግድና ኢንዱስትሪ እንዲቀርብ እንጠይቃለን።

**ሀኒሳ ምነዋር**

### የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 635/ረ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0051897964 አስቴር ተክለብርሃን ገብረሕይወት በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት የካ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የእጅ በእጅ ሽያጭ ተጨማሪ እሴት ታክስ/ቫት/ ደረሰኝ ውስጥ ከቁጥር 001 እስከ 4750 የተሰራበትና ያልተሰራበት እንዲሁም Cash Payment ደረሰኝ ከ001 እስከ 500 የታተመው እንዲሁም ከተለያሉ ቦታዎች ግዥ የፈፀምንባቸው ደረሰኞች በሙሉ በእሳት ቃጠሎ ምክንያት ስለወደመብኝ እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል።ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት የካ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ።

**የግብር ከፋይ ስም አስቴር ተክለብርሃን ገብረሕይወት**

### የጨረታ ማስታወቂያ

**(የጨረታ ቁጥር ፋማዳ/ግሥአቡ 011/2015)**

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በበጀት ዓመቱ ለሠራተኞች የሚያሰራጨው ከታች የተገለጸውን የደንብ ልብስ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል።

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|
| 1. | ካፖርት | 730 |
| 2 | የደህንነት ጫማ (Safety Sheos) | 400 |

ስለሆነም ከዚህ በታች የተገለጹትን መስፈርቶች የሚያሟሉ አቅራቢዎች በጨረታው እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል።

1. በጨረታው የሚወዳደሩ ተጫራቾች ሕጋዊ የታደሰ የንግድ ሥራ ፍቃድ ያላቸውና በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ለመ መዝገባቸው ከድረገጹ (website) አትመው ከጨረታ ሰነዱ ጋር ማያያዝ ይኖርባቸዋል።
2. ተጫራቾች በተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/ ከፋይነት የተመዘገቡና የግብር መለያ ሠርተፍኬት ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ አለባቸው።
3. የደህንነት ጫማ ላይ የሚወዳደሩት አምራቾች ብቻ ይሆናሉ።
4. ተጫራቾች ብር 55,000.00 (ሃምሳ አምስት ሺ) የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ ክፍያ ማዘዣ (CPO) ወይም ለዘጠና ቀናት የሚቆይ ቅድመ ሁኔታ ያላስቀመጠ የባንክ ዋስትና ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው።
5. ተጫራቾች የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል የጨረታ ሰነዱን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለገሐር በሚገኘው የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 108 ድረስ በመቅረብ መግዛት ይችላሉ።
6. ተጫራቾች መወዳደሪያ ሰነዳቸውን በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ለገሐር በሚገኘው የድርጅቱ ዋና መ/ቤት 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 108 በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ መጋቢት 29 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ 8፡00 ሰዓት ድረስ ማስገባት ይኖርባቸዋል። ጨረታው ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በፋሲሊቲ ማኔጅመንት የስብሰባ አዳራሽ በዚሁ ዕለት ማለትም መጋቢት 29 ቀን 2015 ዓ.ም ከቀኑ 8፡45 ይከፈታል፤
7. መሥሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
8. ለተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ ቁጥር 011-5512400
   የውስጥ መሥመር 237/262 ወይም በቀጥታ 011-5504931 መጠየቅ ይቻላል።

**የኢትዮጵያ መድን ድርጅት**